በቃልህ ደስ አለኝ።
163ሐሰትን እጠላለሁ፤ እጸየፉለሁ፤
ሕግህን ግን ወደድሁ።
164ጻድቅ ስለ ሆነው ሕግህ፤
በቀን ሰባት ጊዜ አመሰግንሃለሁ።
165ሕግህን የሚወዱ ብዙ ሰላም አላቸው፤
ዕንቅፋትም የለባቸውም።
166*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ማዳንህን ተስፋ
አደርጋለሁ፤
ትእዛዝህንም እፈጽማለሁ።
167ነፍሴ ምስክርነትህን ትጠብቃለች፤
እጅግ እወድዋለሁና።
168መንገዴ ሁሉ በፊትህ ግልጽ ነውና፣
ሕግህንና ምስክርነትህን እጠብቃለሁ።

*ኀ ታው*

169*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጩኸቴ ከፊትህ
ይድረስ፤
እንደ ቃልህም ማስተዋልን ስጠኝ።
170ልመናዬ ከፊትህ ይድረስ፤
እንደ ቃልህም ታደገኝ።
171ሥርዐትህን አስተምረኸኛልና፣
ከንፈሮቼ ምስጋናን አፈለቁ።
172ትእዛዛትህ ሁሉ የጽድቅ ትእዛዛት
ናቸውና፣
አንደበቴ ስለ ቃልህ ይዘምር።
173ትእዛዝህን መርጫለሁና፣
እጅህ እኔን ለመርዳት ዝግጁ ይሁን።
174*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ማዳንህን ናፈቅሁ፤
ሕግህም ደስታዬ ነው።
175አመስግንህ ዘንድ በሕይወት ልኑር፤
ሕግህም ይርዳኝ።
176እንደ ጠፋ በግ ተቅበዘበዝሁ፤
ትእዛዛትህን አልረሳሁምና፣
ባሪያህን ፈልገው።

## መዝሙር 120

### የሰላም ፀሮች

*መዝሙረ መዓርግ*

1በተጨነቅሁ ጊዜ ወደ *እግዚአብሔር*
ተጣራሁ፤
እርሱም መለሰልኝ።
2*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከሐሰተኛ ከንፈር፣
ከአታላይ ምላስም አድነኝ።
3ሐሰተኛ አንደበት ሆይ፤ ምን ይከፈልህ?
ከዚህስ የባሰ ምን ይደረግብህ?
4በተሳለ የጦረኛ ቀስት፣
በግራር ከሰል ፍም ይቀጣሃል።
5በሜሼክ እኖራለሁና፣
በቄዳር ድንኳኖች መካከል እቀመጣለሁና
ወዮልኝ!
6ሰላምን በሚጠሉ መካከል፣
ነፍሴ እጅግ ብዙ ጊዜ ኖረች።
7እኔ ሰላም ፈላጊ ነኝ፤
እነርሱ ግን በተናገርሁ ጊዜ ጠብ ይሻሉ።

119፥163 ቍ47፡128
119፥164 ቍ7፡160
119፥165 ቍ11፤ መዝ37፥11፡24፤ ኢሳ26፥3፡12፤27፥5፤32፥17፤57፥19፤66፥12፤1ዮሐ2፥10
119፥166 ቍ81
119፥167 ቍ47
119፥168 ቍ2፡22፡56፡88፤ኢዮ10፥4፤23፥10፤መዝ139፥3፤ምሳ5፥21
119፥169 ቍ9፡34፤ኢዮ16፥18
119፥170 ቍ41፤1ነገ8፥30፤2ዜና6፥24፤መዝ3፥7፤22፥20፤28፥2፤59፥1፤140፥6፤143፥1
119፥171 መዝ51፥15፤63፥3፤94፥12፤ኢሳ2፥3፤ሚክ4፥2
119፥172 ቍ7፡75፤መዝ51፥14
119፥173 ኢሱ24፥22፤መዝ37፥24፤73፥23፤ኢሳ41፥10
119፥174 ቍ16፡24፡166
119፥175 ቍ116፡159፤ኢሳ55፥3
119፥176 ቍ10፤መዝ44፥17፤95፥10፤ኤር50፥17፤ሕዝ34፥11፤ሉቃ15፥4
120፥1 2ሳሙ22፥7፤መዝ18፥6፤118፥5
120፥2 መዝ31፥18፤52፥4 120፥4 ዘዳ32፥23
120፥5 ዘፍ25፥13፤ኤር2፥10

119፥163 *እጠላለሁ፤* የቍ53 ማብ ይመ። *ሐሰትን፤* ወይም "መንገዳቸው አታላይ" የሆነ ማለት ነው (ቍ29 እና ማብ ይመ)።

119፥164 *ሰባት፤* ፍጹምነትን የሚያመለክት ቃል ነው፤ መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ቀኑን ሙሉ ሲያመሰግነውና ሲያወድሰው ይውላል፤ ያድራል።

119፥165 *ብዙ ሰላም፤* የሚያስጋ ነገር የሌለበት ፍጹም አስተማማኝና ዋስትና ያለው ማለት ነው።

*119፥169-176፤* የቍ145-152 ማብ ይመ።

119፥171 *ምስጋናን አፈለቁ፤* ታድገኸኛልና ዘወትር አመሰግንሃለሁ ማለቱ ነው።

119፥172 *የጽድቅ፤* የቍ7 ማብ ይመ።

*119፥174-176፤* የመዝሙሩ መደምደሚያ ነው።

119፥176 *ተቅበዘበዝሁ፤* ኢሳ53፥6 ይመ። መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር ሕግ ለመገዛት ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሣ፣ ደግሞ ደጋግሞ በሐሰተኛ (በአታላይ) መንገድ እንደ ጠፋም በግ የባዘነ መሆኑንና በስማያዊው እረኛ ተፈልጎ መገኘትና ወደ እግዚአብሔርም መመለስ እንዳለበት በግልጽ ይናገራል። የእግዚአብሔርን ሕግ የሕይወቱ መመሪያና ለሕይወቱም እንደ ዕንቍ ለቈጠረው ሰው የዚህ መዝሙር የመጨረሻ ቃል ንስሓና ጸሎት ነው።

*መዝ120፤* ከሐሰተኛ ከሳሾች እግዚአብሔር እንዲታደገው ያቀረበው ጸሎት ነው። ቍጥር 7 የመዝሙሩ ባለቤት ንጉሥ እንደ ሆነ ይጠቍማል፤ እንዲህ ከሆነ የንጉሡ ከሳሾች ንጉሡን በሕዝቡ ፊት ለማሳጣት የፈለጉ ወይም ባዕዳን ነገሥታት በንጉሡ ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርባቸው ለማድረግ ተንኰል የሸረቡ ይመስላል። ነገር ግን "ጦርነት" የተለዋዋጭ ዘይቤ ይዘት አለው የምንል ከሆነ መዝሙሩ በሐሜተኞች የተከበበ አንድ ሰው የተናገረው ነው ማለት ይቻላል።

120ርእስ፤ *መዓርግ፤* አንዳንድ ሰዎች ይህ ቃል የሚያመለክተው ወደ ቤተ መቅደሱ የሚያወጣውን ደረጃ ነው ይላሉ፤ ከዚህ የተነሣም መዝሙሩን "የደረጃ መዝሙር" ብለውታል፤ ይህ መዝሙር በቤተ መቅደሱ ውስጥ በተሰጥዎ መልክ (ምናልባት በዳስ በዓል ጊዜ) የሚዘመር ነው። ብዙዎች እንደሚናገሩት ግን ይህ ሐረግ ("የደረጃ መዝሙር") የሚያመለክተው፣ ተሳላሚዎች በየዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የሚዘምሩት ነው (84፥5-7፤ ዘፀ 23፥14-17፤ ዘዳ16፥6፤ ሚክ4፥2፤ ዘካ14፥6 ይመ) ይላሉ፤ ይህ አባባል ግን መዝሙሩ በቤተ መቅደሱ ውስጥ በተሰጥዎ መልክ የሚዘመር ነው የሚለውን ቁርሽ አያደርግም። ይህ ርእስ በመዝ121-134 ሁሉ ላይ የሚገኝ ርእስ ሲሆን መዝሙሩ በመጀመሪያ ሲጻፍ የነበረውን መሠረታዊ ዐላማ ሳይሆን ከምርኮ በኋላ የነበረውን ሁኔታ እንደሚያመለክት ምንም ጥርጥር የለውም፤ እንዲሁም ርእሱ ከመዝ 120-134 ድረስ ያሉት መዝሙሮች አሁን ያላቸውን መልክ የያዙት ከምርኮ በኋላ መሆኑን ያሳያል። ይህ መዝሙር ከመዝ 135-136 ጋር በአይሁድ የተሰጥዎ ዝማሬ ውስጥ "ታላቁ የሃሌ ሉያ መዝሙር" በመባል ይታወቃል (እንዲህ የሚል ስያሜ የተሰጠው "የግብፃውያን ሃሌ ሉያ መዝሙር" ከሚለው ለመለየት ነው፤ የመዝ113 መግቢያ ይመ)። ይህን መዝሙር የመዝ 84 መንፈስ ከብቦታል (መዝ42-43 ይመ)።

120፥2 *ከሐሰተኛ ከንፈርና ከአታላይ ምላስም፤* የ5፥9 ማብ ይመ።

*120፥3-4፤* እግዚአብሔር ጣልቃ እንደሚገባ የሚገልጽ ማረጋገጫ ነው (6፥8-10 እና የ3፥8 ማብ ይመ)።

120፥3 *ከዚህስ የባሰ፤* የተለመደውን የመሐላ ቃል የሚያስታውስ ሲሆን (1ሳሙ3፥17 እና ማብ ይመ)፣ ይህም እግዚአብሔር በሕዝቡ ጠላቶች ላይ ፍርዱን እንደሚያመጣ በመዝሙረኛው በኩል በእርግጠኝነት ይናገራል።

120፥4 *በተሳለ ... ቀስት፤* ምላስ እንደ ሹል ቀስት ሁሉ የሚወጋ (ምሳ25፥18፤ ኤር9፥8 ይመ፤ እንዲሁም 57፥4፤ 64፥3 ይመ)፤ እንደ እሳት የሚፈጅ (ምሳ16፥27፤ ያዕ3፥6 ይመ) እንደ ሆነ ሁሉ የእግዚአብሔርም ፍርድ ልክ እንደዚሁ ነው (7፥11-13፤ 11፥6፤ 64፥7 ይመ)። ለተፈጸመ በደል ተገቢ ቅጣት እንደሚሰጥ በ63፥9-10፤ 64፥7-8 እና ማብ ይመ። *በግራር፤* በበረሓ የሚበቅል ሲሆን አንዳንድ ጊዜ እንደ ጥላ ያገለግላል።

*120፥5-7፤* በጠላቶቹ መካከል ለረጅም ጊዜ በመቀመጡ የተሰማውን ሐዘን የገለጸበት ክፍል ነው።

120፥5 *በሜሼክ ... በቄዳር፤* የመጀመሪያው ተከል በመካከለኛው ትንሹ እስያ የሚገኝ ሲሆን (የዘፍ10፥2 ማብ ይመ)፣ ሁለተኛው ደግሞ በዐረብ አገር ይገኛል (የኢሳ21፥16 ማብ ይመ)። መዝሙረኛው ራሱን የሚመለከተው በሐሜተኞችና በአምላክ የለሾች እንደ ተከበበ አድርጎ ነው።

## መዝሙር 121

### የእስራኤል ጠባቂ

*መዝሙረ መዓርግ*

1 ዐይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ፤
  ረድኤቴ ከወዴት ይመጣል?
2 ረድኤቴ ሰማይንና ምድርን ከፈጠረ፣
  *ከእግዚአብሔር* ዘንድ ይመጣል።

3 እግርህ እንዲሸራተት አይፈቅድም፤
  የሚጠብቅህም አይተኛም።
4 እነሆ፤ እስራኤልን የሚጠብቅ፣
  አይተኛም፤ አያንቀላፋምም።

5 *እግዚአብሔር* ይጠብቅሃል፤
  *እግዚአብሔር* በቀኝህ በኩል ይከልልሃል።
6 ፀሓይ በቀን አያቃጥልህም፤
  ጨረቃም በሌሊት ጒዳት አታመጣብህም።

7 *እግዚአብሔር* ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፤
  ነፍስህንም ይንከባከባታል።
8 *እግዚአብሔር* ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፣
  መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል።

## መዝሙር 122

### ኢየሩሳሌም እልል በዪ!

*የዳዊት መዝሙረ መዓርግ*

1 “ወደ *እግዚአብሔር* ቤት እንሂድ”
  ባሉኝ ጊዜ፣
  ደስ አለኝ።
2 ኢየሩሳሌም ሆይ፤
  እግሮቻችን ከደጆችሽ ውስጥ ቆመዋል።
3 ኢየሩሳሌም እጅግ እንደ ተጠጋጋች፣
  ከተማ ሆና ተሠርታለች።
4 ለእስራኤል በተሰጠው ሥርዐት መሠረት፣
  *የእግዚአብሔርን* ስም ለማመስገን፣
*የእግዚአብሔር* ነገዶች፣
  ወደዚያ ይመጣሉ።
5 በዚያም የፍርድ ዙፋኖች የሆኑት፣
  የዳዊት ቤት ዙፋኖች ተዘርግተዋል።

6 እንዲህ ብላችሁ ለኢየሩሳሌም ሰላም

121፥2 ዘፍ1፥1፤ መዝ104፥5
121፥4 መዝ127፥1
121፥5 መዝ1፥6
121፥6 ኢሳ49፥10
121፥7 መዝ9፥9
121፥8 ዘዳ28፥6
122፥6 መዝ26፥8

*መዝ121፤* የኑዛዜና የዋስትና ቃለ ምልልስ ነው (ይህ ምናልባት የተሰጥዎ ዜማ ሊሆን ይችላል)። መዝሙሩ የተሳላሚዎች ዜማ በመሆኑ ለምን አገልግሎት እንደሚውል ከዚሁ መረዳት ይቻላል። ቃለ ምልልሱ አንድ ሰው ከራሱ ጋር ያደረገው (ከመዝ 42-43 አዝማቾች ጋር ያነጻጽሩ) ይሁን ወይም በጒዞ ላይ ያሉ ተሳላሚዎች እርስ በርስ ያደረጉት ይሁን ይህን ያህል የጐላ ልዩነት አያመጣም፤ ምክንያቱም ሁለቱም ወገኖች ተመሳሳይ እምነት አላቸው። በመዝሙሩ ውስጥ የተነገሩት የማጽናኛ ቃሎች (መዝ33 ይመ) ወደ ኢየሩሳሌም ለሚሄዱ ተሳላሚዎችም ሆነ ወደ “ክብሩ” ለሚገቡ ታማኝ የሕይወት ተሳላሚዎች ተገቢ ቃሎች ናቸው (የ49፥15፤ የ73፥24 ማብ ይመ)። መዝሙሩ በአራት ቤት የተዋቀረ ሲሆን እያንዳንዱ ቤት የራሱ የሆነ መግቢያ ስንኝ አለው፤ “እግዚአብሔር” እና “ይጠብቅሃል” የሚሉት ቃላት ቍልፍ ቃላት ሲሆኑ አምስት አምስት ጊዜ ተወሥተዋል።

121 *ርእስ፤* የመዝ120 ማብ ይመ።

*121፥1-2፤* በእግዚአብሔር ላይ ያለውን መታመን በግልጽ የተናገረበት ክፍል ነው።

121፥1 *ተራሮች፤* በኢየሩሳሌም ዙሪያ የሚገኙ ኰረብታዎች ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ወይም የጽዮን ተራራ ነው (125፥2)፤ ወይም ደግሞ ብዙው ቍጥር የሚያመለክተው (በዕብራይስጡ በ87፥1፤ በ133፥3 ላይ እንደ ተጠቀሰው) ግርማን ከሆነ መዝሙረኛው የተናገረው ስለ ጽዮን ተራራ ነው።

121፥2 *ሰማይንና ምድርን ከፈጠረ፤* የፍጥረት ሁሉ ንጉሥ (124፥8፤134፥3 ይመ። እንዲሁም 33፥6፤ 89፥11-13፤ 96፥4-5፤ 104፥2-9፤ 136፥4-9 ይመ) የሆነውን አንዱን እውነተኛ አምላክ ነው።

*121፥3-4፤* እስራኤልን ስለሚጠብቀው የማይተኛ አምላክ የተነገረ ቃል ነው።

121፥3 *እግርህ እንዲንሸራተት፤* መንገዱ የሚያዳልጥ መንገድ ቢሆንም እንኳ ከቶ እንድትወድቅ አያደርግም ማለት ነው። *አይተኛም፤* እንደ አሕዛብ አምላክ እንደ በዓል የእስራኤል አምላክ አይተኛም (1ነገ18፥27 ይመ)።

121፥4 *እስራኤልን የሚጠብቅ፤* ይህ የእስራኤል ጠባቂ የፍጥረት ሁሉ ጌታ፣ እስራኤልን ተግቶ የሚጠብቅና ታማኞች ዘወትር የሚተማመኑበት ነው።

*121፥5-6፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ የማያቋርጥ ጥበቃ እንደሚያደርግ የሚያረጋግጥ ቃል ነው።

121፥5 *ይከልልሃል፤* 91፥1 (“መጠጊያ”) የሚለውንና የ17፥8 ማብ ይመ። *በቀኝህ በኩል፤* 16፥8 እና ማብ ይመ።

121፥6 *ፀሓይ ... ጨረቃም፤* እዚህ ላይ “ከለላ” ከሚለው ተለዋጭ ዘይቤ ጋር ይስማማል፤ እነዚህ ቃላት ቀንም ሆነ ሌሊት ለሚያስጨንቁና ለሚያስፈሩ ነገሮች እንደ ምሳሌ ሆነው ያገለግላሉ (ኢሳ4፥6፤ 25፥4-5፤ 49፥10፤ ዮና4፥8 ይመ)።

*121፥7-8፤* መላ ሕይወቱን እንደሚጠብቅለት የተነገረ ማረጋገጫ ነው።

121፥8 *መውጣትህንና መግባትህን፤* ባጭሩ እንቅስቃሴህን ሁሉ ማለት ነው።

*መዝ122፤* ስለ ኢየሩሳሌም የተነገረ የደስታ መዝሙር ነው (መዝ42-43፤ 46፤ 48፤ 84፤ 87፤137 እና መግቢያዎቻቸውን ይመ)። መዝሙሩ ወደ ኢየሩሳሌም በሚጓዙ ተሳላሚዎች (ምናልባት በየዓመቱ ከሚከበሩ ሦስት በዓላት በአንዱ ላይ የሚዘመር ነው፤ ዘዳ16፥16) የሚዘመር ነው፤ መዝሙረኛው በከተማዋ የተሰማውን ጥልቅ ደስታና ስለ ከተማዋ ደኅንነት ያቀረበው ጸሎት ይህንኑ ይገልጻል። ይህ መዝሙር ሦስተኛ የተሳላሚዎች መዝሙር እንደ መሆኑ መጠን (የመዝ120 መግቢያ ይመ) ከመዝ132 ጋር የሚጋራው በርካታ ዐበይት ፍሬ ሐሳቦች አሉት። በአወቃቀር ረገድ ሲታይ መዝሙሩ የተቀነበበው “የእግዚአብሔር ቤት” (ቍ1:9) በሚለው ሐረግ ነው።

122 *ርእስ፤ የምዕራግ፤* የመዝ120 ማብ ይመ። *የዳዊት፤* ቃሉ በጥንት ጽሑፎች ላይ አይገኝም፤ ምናልባት ከጊዜ በኋላ የተጨመረ ሳይሆን አይቀርም (የቍ1 ማብ ይመ)።

*122፥1-2፤* መዝሙረኛው ወደ ኢየሩሳሌም ከሚሄዱ ተሳላሚዎች ጋር አብሮ ለመሄድ በመታደሉ ደስታውን ይገልጻል።

122፥1 *ወደ እግዚአብሔር ቤት፤* ቤተ መቅደሱ ነው (2ሳሙ7፥5:13፤ 1ነገ5፥3:5 “ቤተ መቅደስ” 8፥10 “ቤተመቅደስ”) ከ1ነገ3፥4፤ 8፥1-11 አንጻር ሲታይ ቤተ መቅደሱ አገልግሎቱን በይፋ ከመጀመሩ በፊት ኢየሩሳሌምም ተሳላሚዎች የሚሄዱባት ከተማ ነበረች ለማለት የሚያሳፍር ነገር የለም።

122፥2 *ከደጆችሽ፤* የከተማዪቱ ቅጥር በሮች ናቸው።

*122፥3-5፤* ኢየሩሳሌም ለታማኝ ሰዎች ያላትን ቦታ የሚገልጽ ክፍል ነው።

122፥3 *ተጠጋጋች፤* መኖሪያ ቤቶቿ እርስ በርስ ተያይዘው የተሠሩ መሆናቸውን የሚያመለክት ቃል ሊሆን ይችላል (መዝ 48 ይመ)። ወይም ደግሞ “እንደ አንድ ወጥ አድርገህ አያይዘው” በማለት በዘፀ26፥11 ላይ ስለ ምስክሩ ድንኳን አሠራር የተጻፈውን የሚያስታውስ ቃል ሊሆን ይችላል። ይህ አባባል ትክክል ሆኖ ከተገኘ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ማደሪያ እንደ ሆነች ተቈጥሮ ክብረ በዓል ሊደረግባት ይገባል (የ9፥11 ማብ ይመ፤ እንዲሁም ኢሳ4፥5 ይመ)።

122፥4 *ለማመስገን፤* ውዳሴ የሚቀርበው እግዚአብሔር በእስራኤል መካከል ስላደረገው የማዳን ሥራና በሕዝቦች ላይ ስላፈሰሰው በረከት ነው። *ስም፤* የ5፥11 ማብ ይመ። *ለእስራኤል በተሰጠው ሥርዐት፤* 81፥3-5፤ ዘዳ16፥1-17 ይመ።

122፥5 *በዚያም ... የዳዊት ቤት ዙፋኖች፤* ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ከተማና እርሱ ለመረጠው ሥርወ መንግሥት መናገሻ ናት፤ እግዚአብሔር ሕዝቦችን የሚያስተዳድረው ከዚህ ሥርወ መንግሥት በሚወጣው ንጉሥ ነው (2፥2:6-7፤ 89፥3-4:19-37፤ 110፤ 2ሳሙ7፥8-16 እና ማብ ይመ) ምንም እንኳ አሁን በመሲሓዊ ተስፋ ውስጥ ብትሆንም ከምርኮ በኋላ የዳዊት ከተማ እንደ ሆነች ቀጥላለች።

*122፥6-9፤* ስለ ኢየሩሳሌም ሰላም የቀረበ ጸሎት ነው።

*122፥6፤* በዕብራይስጡ ቅጅ ላይ “ጸሎት”፣ “ሰላም”፣ “ኢየሩሳሌም” እና “ዋትና ያላት” የሚሉት ቃላት ማራኪ በሆነ መንገድ እርስ በርስ ተሳስረዋል። *ሰላም፤* ቍ7-8 ይመ። ይህ

ጸልዩ፤
"የሚወዱሽ ይለምልሙ፤
7በቅጥርሽ ውስጥ ሰላም ይሁን፤
በምሽግሽም ውስጥ መረጋጋት
ይስፈን"።
8ስለ ወንድሞቼና ስለ ባልንጀሮቼ፣
"በውስጥሽ ሰላም ይስፈን" እላለሁ።
9ስለ ስምባካችን ስለ እግዚአብሔር ቤት፣
በጎነትሽን እሻለሁ።

## መዝሙር 123
### የተጨነቀ ሰው ጸሎት
*መዝሙረ መዓርግ*

1በሰማይ ዙፋን ላይ የተቀመጥህ ሆይ፤
ዐይኖቼን ወደ አንተ አነሣለሁ።
2የባሪያዎች ዐይን ወደ ጌታቸው እጅ፣
የባሪያዪቱም ዐይን ወደ እመቤቷ
እጅ እንደሚመለከት፣
ምሕረት እስኪያደርግልን ድረስ፣
የእኛም ዐይኖች ወደ ስምባካችን ወደ
*እግዚአብሔር* ይመለከታሉ።
3*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ንቀት
በዝቶብናልና፣
ማረን፣ እባክህ ማረን።
4ነፍሳችን የቅንጡዎች ስድብ፣
የትዕቢተኞችም ንቀት እጅግ በዝቶባታል።

122፥7 1ሳሙ25፥6፤መዝ48፥3
122፥9 መዝ128፥5
123፥1 መዝ68፥5፤ ኢሳ6፥1፤63፥15
123፥2 መዝ25፥15
124፥1 መዝ129፥1
124፥4 መዝ81፥4፤ 88፥17
124፥7 መዝ25፥15፤91፥3
124፥8 ዘፍ1፥1፤ 1ሳሙ17፥45፤መዝ 115፥15፤121፥2፤134፥3
125፥1 መዝ46፥5፤ 48፥2-5፡12፤ኢሳ 33፥20

## መዝሙር 124
### የእስራኤል አዳኝ
*የዳዊት መዝሙረ መዓርግ*

1እስራኤል እንዲህ ይበል:-
"*እግዚአብሔር* ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ፣
2ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ፣
*እግዚአብሔር* ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ፣
3ቍጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ፣
በቁመናችን በዋጡን ነበር፤
4ጐርፍ ባጥለቀለቀን፣
ፈረሰኛው ውሃ ባሰጠመን፣
5ደራሽ ውሃም
ጠራርጎ በወሰደን ነበር።
6በጥርሳቸው ከመዘንጠል የጠበቀን፣
*እግዚአብሔር* ይባረክ።
7ነፍሳችን እንደ ወፍ፣
ከአዳኝ ወጥመድ አመለጠች፤
ወጥመዱ ተሰበረ፤
እኛም አመለጥን።
8የሰማይና የምድር ፈጣሪ፣
የ*እግዚአብሔር* ስም ረዳታችን ነው።

## መዝሙር 125
### እግዚአብሔር የሚታመኑበትን ይጠብቃል
*መዝሙረ መዓርግ*

1*በእግዚአብሔር የሚታመኑ*፣
ሳትናወጥ ለዘላለም እንደምትኖር እንደ

---

ቃል ዋስትናንና ብልጽግናን ይይዛል። አንቺንም የሚወዱ፤ ይሀጠቹን ከተማ የሚወዱት መዝሙረኛው፣ በቍ1:8 ላይ የተጠቀሱትና ኢየሩሳሌምን የሚወዱ ሁሉ ናቸው፤ ምክንያቱም ለጌታና እርሱ ለመረጠው ንጉሥ የተገዙ ናቸው። ይህም እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ በአንድነት የሚያመልኩትን፣ አብረው የሚጸልዩትንና እርስ በርስ የሚተሳሰቡትን ያካትታል (መዝ133 ይመ)።

122፥7 *በቅጥርሽ ... በምሽግሽም፤* 48፥13 ይመ ("ግንቦቿን ... ምሽጎቿን")።

*122፥8-9 ስለ ... ስለ፤* ኢየሩሳሌም፣ እግዚአብሔርና ሕዝቡ ልዩ በሆነ አንድነት የሚገኙበት ከተማ በመሆኗ መዝሙረኛው ሰላም የሰፈነባት ከተማ እንድትሆን ከልብ ይመኛል።

*መዝ123፤* እግዚአብሔር ምሕረቱን እንዲያወርድላቸውና የእብሪተኞችን ንቀትና ድፍረት ዝም እንዲያሰኝላቸው ትሑታን የእግዚአብሔር ሕዝብ ያቀረቡት ጸሎት ነው። የመዝ124 መግቢያ ይመ። ባወቃቀር ደረጃ ሲታይ መዝሙሩ ባለ አንድ ቍጥር መግቢያና ባለ ሁለት ቤት ስንኝ ያለው ነው፤ ባለ ሁለት ቤት ስንኞች የየራሳቸውን ዋና ሐሳብ አጐልብተዋል።

123፥1 *በሰማይ ዙፋን ላይ፤* ዙፋኑ በሰማይ የሆነው አምላክ ምድራዊ ዙፋኑን በጽዮን ተራራ ላይ በሚገኘው ቤተ መቅደስ ውስጥ አድርጎታል (122፥5 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም 2፥4:9፡ 11፤ 11፥4፤ 80፥1፤ 99፥1፤ 113፥5፤ 132፥14 ይመ)።

123፥2 *የባሪያዎች ... የባሪያዪቱም፤* ንጽጽር ነው፤ በዚህ ዐይነት ታማኝ የእግዚአብሔር ሕዝቦች (ወንዶችም ሆኑ ሴቶች) የሚ ታመኑት በእግዚአብሔር ብቻ እንደ ሆነ ዐውቀው ራሳቸውን በትሕትና ለእርሱ እንደሚሰጡ ተገልጾአል።

123፥4 *የትዕቢተኞችን ... የእብሪተኞችን፤* በራሳቸው ብልጠትና ጕልበት የሚኖሩ ሰዎች (የ10፥2-11፤ 31፥23 ማብ ይመ) በእግዚአብሔር የሚታመኑትን ሰዎች ከፋኛ ይንቃሉ፤ በተለይ ደግሞ በእግዚአብሔር የሚታመኑ ሰዎች መከራ ሲደርስባቸው ወይም ብልጽግና ፊቱን ሲያዞርባቸው ንቀታቸውን በይፋ ያሳያሉ።

*መዝ124፤* እግዚአብሔር ከኀይለኛ ጠላቷ እጅ ስለታደጋት እስራኤል ያቀረበችለት ውዳሴ ነው። ከመዝ123 ተከትሎ መጻፉ ትክክል ነው። ከቍ1-5 ያለው ክፍል የሚናገረው ሌዋዊ ሲሆን ከቍ6-8 ያለውን ደግሞ ሕዝቡ በተሰጥዎ መልክ ይመልሳል። እንደ መዝ129 ሁሉ ይህም መዝሙር በሁለት አንጓ ይከፈላል።

124 ርእስ፤ *የምዕራግ፤* የመዝ120 ማብ ይመ። *የዳዊት፤* ሁሉም ጥንታዊ ቅጆች ይህን ቃል አይጠቅሱም፤ የመዝሙሩ ቋንቋና ዐቢይ ሐሳብ እንደሚያመለክቱት መዝሙሩ የተጻፈው ከምርኮ በኋላ ነው (የመዝ122 ርእስ ማብ ይመ)። መዝሙሩ ለዳዊት የተሰጠው የመዝ18፤ 69 ሐሳቦችን ስለሚያስ ተጋባ ሊሆን ይችላል።

*124፥1-5፤* ከመጥፋት ያዳናት እግዚአብሔር እንጂ ሌላ አለመሆኑን እስራኤል ልታውቅ ይገባል (20፥7፤94፥17 ይመ)።

124፥2 *ሰዎች በተነሡ ጊዜ፤* ትዕቢተኞችና እብሪተኞች ሰዎች (መዝ123፥4) ሊያጠቋት ቢነሱም እግዚአብሔር ግን የእስራኤል ረዳት ነው (ቍ8)።

124፥3 *በዋጡን ነበር፤* እንደ ሞት (የ49፥14 ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ 69፥15 ይመ።

124፥4-5 *ጐርፍ ... ፈረሰኛው ውሃ ... ደራሽ ውሃም፤* መዝ18፥16 ይመ፤ እንዲሁም 32፥6፤ 69፥1-2 እና ማብ ይመ።

*124፥6-8፤* እግዚአብሔር ላሳያቸው ማዳን የቀረበ ምስጋና ነው፤ ምስጋናው የቀረበው ምስል ከሳች በሆነ ቋንቋ ነው።

124፥6 *በጥርሳቸው ከመዘንጠል፤* የዱር አውሬዎች ያገኙትን ሁሉ ዘነጣጥለው እንደሚጥሉ ማለት ነው (የ7፥2 ማብ ይመ)።

124፥7 *እንደ ወፍ፣ ከአዳኝ ወጥመድ አመለጠች፤* እስራኤላውያን ከባቢሎን ምርኮ እንዴት ነጻ እንደወጡ የሚገልጽ ውብ አነጋገር ነው።

*124፥8፤* የእግዚአብሔር ሕዝብ አለኝታ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን የሚገልጽ ቃል ነው (121፥2 እና ማብ ይመ)።

*መዝ125፤* የእስራኤል ሰላም በምስክርነት፣ በጸሎትና በቡራኬ ተነገረ። መዝሙሩ የተጻፈው ከምርኮ በኋላ ሲሆን አንድ ሌዋዊ በተሰጥዎ ጊዜ የተናገረው ሳይሆን አይቀርም።

125 *ርእስ፤* የመዝ120 ማብ ይመ።

*125፥1-2፤* የእግዚአብሔር ሕዝብ ታላቅ ጥበቃ እንደሚደረግለት የሚያወሣ ክፍል ነው።

125፥1 *በእግዚአብሔር የሚታመኑ፤* እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር "ሕዝብ" (ቍ2) "ጻድቃን" (ቍ3) "ቸሮች" እና "ቅን ልብ ያላቸው" (ቍ4) ናቸው። ስለ "ጻድቃን" ተጨማሪ ገለጻ ለማግኘት 34፥8-14 እና ማብ ይመ። *እንደ ጽዮን ተራራ፤* ጽኑ መታመኛቸው ማን እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው (መዝ46፤ 48 ይመ)።

ጽዮን ተራራ ናቸው።
2 ተራሮች ኢየሩሳሌምን እንደ ከበቧት፣
ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም፣
እግዚአብሔር በሕዝቡ ዙሪያ ነው።
3 ጻድቃን እጃቸውን፣
ለክፋት እንዳያነሡ፣
የክፉዎች በትር፣
ለጻድቃን በተመደበች ምድር ላይ
አያርፍም።

4 እግዚአብሔር ሆይ፤ መልካም ለሆኑ፣
ልባቸውም ለቀና መልካም አድርግ።
5 ወደ ጠማማ መንገዳቸው የሚመለሱትን
ግን፣
እግዚአብሔር ከክፉ አድራጊዎች ጋር
ያስወግዳቸዋል።

በእስራኤል ላይ ሰላም ይውረድ።

## መዝሙር 126

### የስደት ተመላሾች መዝሙር

*መዝሙረ መዓርግ*

1 እግዚአብሔር የጽዮንን ምርኮ[ሖ] በመለሰ[ፐ]
ጊዜ፣
ሕልም እንጂ እውን አልመሰለንም።
2 በዚያን ጊዜ አፋችን በሣቅ፣
እንደበታችንም በእልልታ ተሞላ፤
በዚያን ጊዜም በሕዝቦች መካከል፣
"እግዚአብሔር ታላቅ ነገር
አደረገላቸው" ተባለ።
3 እግዚአብሔር ታላቅ ነገር አደረገልን፤
እኛም ደስ አለን።

4 እግዚአብሔር ሆይ፤ በኔጌቭ እንዳሉ ጅረቶች፣
ምርኳችንን መልስ።[ሀ]
5 በእንባ የሚዘሩ፣
በእልልታ ያጭዳሉ።
6 ዘር ቋጥረው፣
እያለቀሱ የተሰማሩ፣
ነዶአቸውን ተሸክመው፣
እልል እያሉ ይመለሳሉ።

## መዝሙር 127

### በእግዚአብሔር መታመን

*የሰሎሞን መዝሙረ መዓርግ*

1 እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፣
ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤
እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፣
ጠባቂ በከንቱ ይተጋል።

[ሖ]1 *ወይም እግዚአብሔር ሀብቷን ይመልሳል።*
[ፐ]1 *ወይም የሰዎቹ ጤንነት ይታደሳል።*
[ሀ]4 *ወይም ሀብታችንን መልስ*

125፥2 1ዜና21፥15፤ መዝ32፥10፤ዘካ2፥4-5
125፥3 1ሳሙ24፥10፤አስ4፥11፤መዝ89፥22፤ምሳ22፥8፤ኢሳ13፥11፤14፥5
125፥4 መዝ36፥10፤119፥65
125፥5 ኢዮ23፥11፤ መዝ92፥7፤128፥6፤ ምሳ2፥15፤17፥6፤ ኢሳ59፥8፤ገላ6፥16
126፥1 ዕዝ1፥1-3፤ መዝ85፥1፤ሆሴ6፥11
126፥2 ዘፍ21፥6፤ ዘዳ10፥21፤ኢዮ8፥21፤ መዝ65፥8፤71፥19፤ ሉቃ1፥49
126፥3 መዝ9፥2፤ 16፥11፤106፥21፤ኢል 2፥21፡26
126፥4 ዘዳ30፥3፤ መዝ107፥35፤ኢሳ 43፥19፤51፥3
126፥5 መዝ6፥6፤ 16፥11፤20፥5፤23፥6፤ 80፥5፤ኢሳ35፥10፤ 51፥11፤60፥15፤61፥7 ፤ኤር31፥6-7፡12፤ 50፥4፤ገላ6፥9
126፥6 ዘኍ25፥6፤ መዝ30፥5
127፥1 መዝ78፥69 ፤121፥4

125፥2 *ተራሮች ኢየሩሳሌምን እንደ ከበቧት፤* ምንም እንኳ ኢየሩሳሌም ዙሪያዋን በቀለበት ተራራ የተከበበች ባትሆንም ከተማዋ የተመሠረተችው የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች ተራራማ ክልል ብለው በሚጠሩት ስፍራ ነው። እግዚአብሔርም ሕዝቡን አሁንም ይከባቸዋል፤ እንዳይናወጡ፣ እንዳይበታተኑና እንዳይፈራርሱ ዙሪያቸውን ይከባቸዋል (2ነገ6፥17፤ ዘካ2፥5 ይመ)።

*125፥3፤* ክፉ ገዦች በተግባራቸውም ሆነ በጭቈናቸው ጻድቃንን ለመበከል ይሞክራሉ፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይህን ከመሰለው አስከፊ ብክላ ይጠብቃል። *የክፉዎች በትረ መን ግሥት፤* ምናልባት የፋርስን ገዦችና (ነህ9፥36-37 ይመ) ነህምያ አጥብቆ የተቃወማቸውን ታናናሽ ሹማምንት ሳይሆን አይቀርም (ነህ2፥19፤ 4፥1-3፡7-8፤6፥1-14፡17-19፤ 13፥7-8፡28 ይመ)። *ለጻድቃን በተመደበላቸው ምድር፤* የተስፋይቱን ምድር ነው (78፥5)።

*125፥4-5፤* ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መክፈል የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው (18፥25-27 ይመ)፤ ስለዚህ መዝሙረኛው ጸሎቱ እንደሚሰማና (ቍ 4) ለጸሎቱም መልስ እንዲያገኝ እርግጠኛ ነው (ቍ5)።

125፥4 *ልባቸውም፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

125፥5 *በእስራኤል ላይ ሰላም ይውረድ፤* ምናልባት እጥር ምጥን ባለ መልኩ የቀረበ የካህናት ቡራኬ ነው (ዘኍ6፥24-26)።

*መዝ126፤* ስለ ጽዮን እንደ ገና መታደስ የተዜመ የደስታ መዝሙር ነው። መዝሙሩ የተጻፈው ከባቢሎን ምርኮ ለተመለሱት ሰዎች (ዕዝራንና ነህምያን ይመ) አይደለም የሚባል ከሆነ (የምርኮው ቦታ አልተጠቀሰም) መዝሙሩ እንደ ገና የታደሰን ወይም የተጐበኘን አንድ ኅብረተሰብ ደስታ ለማስተጋባት አገልግሎአል (ከመዝ42-43፤ 84፤ 137 ጋር ያነጻጽሩ)። መዝሙሩ እያንዳንዳቸው አራት አራት ስንኞች ባሏቸው ሁለት አንጓዎች የተከፈለ ሲሆን የስንኞቹ መጀመሪያ መስመር የጋራ ዐቢይ ሐሳብ አላቸው። የስንኞቹ ዐቢይ ሐሳብ ተያያዥነት እንዳላቸው የሚያሳዩ ሌሎች ቃሎች አሉ ("እግዚአብሔር"፣ "የደስታ መዝሙር"፣ "ተሸከመው")። የመጀመሪያው አንጓ የተቀነበበው የእግዚአብሔር ሥራ በሚያወሣው ቃል ሲሆን (ቍ1፡3) ቍጥር 2 ደግሞ ሐሳቡን የበለጠ ያብራራል።

126፥1 *ርእስ፤* የመዝ120 ርእስ ማብ ይመ።

*126፥1-3፤* ከምርኮ በመመለሳቸው የተሰማቸውን ደስታ የሚገልጽ ክፍል ነው።

126፥1 *ምርኮ ... በመለሰ ጊዜ፤* የቍ4 ማብ ይመ። *ሕልም እንጂ፤* የተደረገላቸው ድንቅ ሥራ እጅግ የሚያስገርም ከመሆኑ የተነሣ ለእነርሱ እንደ ተደረገ ለማመን ተቸገሩ። በተስፋ በጕጕት ሲጠብቁት የነበረው ነገር እንዲሁ ሕልም ብቻ ሆኖ የሚቀር እንጂ እውን ሆኖ እናየዋለን ብለው አላሰቡም ነበር።

*126፥2፤* እግዚአብሔር በመካከላቸው ያደረገው ነገር ሁለት ውጤቶችን አስከትሎአል፤ አንደኛው ከምርኮ የተመለሱት የተሰማቸው ሐሴት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያገኘው ክብር ነው (የ46፥10 ማብ ይመ)።

*126፥4-6፤* ከምርኮ የመመለሳቸው ጕዳይ ይፈፀም ዘንድ የቀረበ ጸሎት ነው።

126፥4 *ምርኮአችንን... መልስ፤* ከምርኮ አገር ሕዝቦቻችንን ፈጽሞ መልስ ወይም የቀድሞውን ዘመን ሰላምና ብልጽግና መልስልን ማለት ነው። *በኔጌቭ ምድረ በዳ እንዳሉት ፈሳሾች፤* የክረምቱ ዝናብ መጥቶ እስኪሞላ ድረስ ክው ብለው የደረቁ ወንዞች ናቸው።

*126፥5-6፤* አሁን ያገኙትንና ወደፊት የሚያገኙትን ደስታ የሚገልጽ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። *በእንባ ... እያለቀሱ፤* ዘር የሚዘሩ በሐዘንና በመከራ ታጅበው ቢዘሩም በመከር ጊዜ ሐሴት ያደርጋሉ። ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ምሳሌያዊ አነጋገር በ20፥5 ላይ ይመ።

*መዝ127፤* ስለ ቤትና ስለ ንብረት እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው የተናገረው የጥበብ ቃል ነው። የመዝሙሩ ዐቢይ ሐሳብ ጊዜ የማይሽረውና የማይለወጠው አባባል ነው፤ መዝሙሩ ተሳላሚዎች ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ ሳሉ ሕይወታቸው ከክፉ ነገር የምትጠበቀውና በረከት የምታገኘው በእነርሱ ጥረት ሳይሆን፣ ከእግ ዚአብሔር ቸርነት የተነሣ መሆኑን ያሳስባቸዋል (ዘዳ 28፥1-14 ይመ)። ሁለት ተመጣጣኝ አንጓዎች ሁለት የተለያዩ ነገር ግን የእርስ በርስ ዝምድና ያላቸውን ዐቢይ ሐሳቦች ተከትለው ቀርበዋል።

127ርእስ፤ *መዓርግ፤* የመዝ120 ርእስ ማብ ይመ። *የሰሎሞን፤* የመዝሙሩ ጸሐፊ ሰሎሞን አይደለም የሚሉ ሰዎች ቢኖሩም (ሁሉም ጥንታዊ ቅጆች ሰሎሞን እንደ ሆነ አይናገሩም) አንዳንድ ሰዎች ግን የመዝሙሩ ጸሐፊ ሰሎሞን ነው ያሉበት ምክንያት ግልጽ ነው።

*127፥1-2፤* ለሰው መጠለያን፣ ሰላምንና የዕለት ምግብን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው።

127፥1 *ቤትን፤* የሰው መኖሪያ ነው። *ሠራተኞች፤* ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል ድምፅ በቍ3 ላይ "ወንዶች ልጆች" የሚለውን ለመግለጽ ከገባው የዕብራይስጥ ቃል ድምፅ ጋር ተመሳሳይ ነው። *ካልጠበቀ፤* 121፥3-8 ይመ። *ከተማ፤* ጠላት አገርን በሚወርበት ጊዜ የኀይል ማእከል ወይም መሸሸጊያ ነው። *ጠባቂ፤* 2ሳሙ13፥34፤18፥24-27፤ ማሕ3፥3፤ 5፥7 ይመ።

2የዕለት ጒርስ ለማግኘት በመጣር፣
ማልዳችሁ መነሣታችሁ፣
አምሽታችሁም መተኛታችሁ ከንቱ ነው፤
እርሱ ለሚወዳቸው እንቅልፍን ያድላልና።[a]
3እነሆ፤ ልጆች *የእግዚአብሔር* ስጦታ
ናቸው፤
የማሕፀንም ፍሬ ከቸርነቱ የሚገኝ ነው።
4በወጣትነት የተገኙ ወንዶች ልጆች፣
በጦረኛ እጅ እንዳሉ ፍላጻች ናቸው።
5ኩረጆዎቹ በእነዚህ የተሞሉ፣
የተባረከ ሰው ነው፤
ከጠላቶቻቸው ጋር በአደባባይ በሚሟ
ገቱበት ጊዜ፣
አይዋረዱም።

## መዝሙር 128
### የጻድቃን በረከት
*መዝሙረ መዓርግ*

1*እግዚአብሔርን* የሚፈሩ ሁሉ፣
በመንገዱም የሚሄዱ የተባረኩ ናቸው።
2የድካምህን ፍሬ ትበላለህ፤
ትባረካለህ፤ ይሳካልሃልም።
3ሚስትህ በቤትህ፣
እንደሚያፈራ ወይን ናት፤
ወንዶች ልጆችህ በማእድህ ዙሪያ፣
እንደ ወይራ ተክል ናቸው።
4እነሆ፤ *እግዚአብሔርን* የሚፈራ ሰው፣
እንዲህ ይባረካል።
5*እግዚአብሔር* ከጽዮን ይባርክህ፤
በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፣
የኢየሩሳሌምን ብልጽግና ያሳይህ፤
6የልጅ ልጅ ለማየትም ያብቃህ።
በእስራኤል ላይ ሰላም ይውረድ።

## መዝሙር 129
### በጽዮን ጠላቶች ላይ የቀረበ ጸሎት
*መዝሙረ መዓርግ*

1እስራኤል እንዲህ ይበል:-
"ከልጅነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ አስጨነቁኝ፤
2በእርግጥ ከልጅነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ
አስጨነቁኝ፤
ዳሩ ግን ድል አላደረጉኝም።
3ዐራሾች ጀርባዬን ዐረሱት፤
ትልማቸውንም አስረዘሙት።"
4*እግዚአብሔር* ግን ጻድቅ ነው፤

[a]2 ወይም *ተኝተው ሳሉ ምግብ ያዘጋጅላቸዋል።*

127፥2 ዘፍ3፥17፤ ዘኍ6፥26፤ዘጸ33፥12፤ ኢዮ11፥18፤መክ2፥25
127፥3 ዘፍ1፥28
127፥4 መዝ112፥2፤127፥5፤ዘፍ23፥10፤ 24፥60፤መዝ128፥2-3
127፥5 ዘፍ23፥10፤ 24፥60፤መዝ128፥2-3
128፥1 መዝ103፥11፤112፥1፤119፥1-3
128፥2 ዘፍ39፥3፤ መዝ58፥11፤109፥11፤ ምሳ10፥22፤ኢሳ3፥10
128፥3 ዘፍ49፥22፤ኢዮ29፥5፤መዝ 52፥8፤144፥12
128፥4 መዝ1፥1፤ 112፥1
128፥5 መዝ20፥2፤ 122፥9
128፥6 ዘፍ48፥11፤ መዝ125፥5
129፥1 ዘፀ1፥13፤ መዝ88፥15፤124፥1
129፥2 ኤር1፥19፤ 15፥20፤20፥11፤ማቴ 16፥18
129፥4 ዘፀ9፥27፤ መዝ37፥9፤140፥5

127፥2 … *እንቅልፍን ይሰጣል፤* መልካም ምርት የሚገኘው በግረትና በጥረት ሳይሆን ከእግዚአብሔር የሚገኝ በረከት ውጤት ነው (ምሳ10፥22፤ ማቴ6፥25-34፤ 1ጢሞ5፥7 ይመ)። *ለሚወዳቸው፤* በተለይ ዘጸ33፥12፤ ኤር11፥15 ይመ።

*127፥3-5፤* ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው፤ እንዲሁም በእርሱ ዘንድ ሞገስ ማግኘታችንን የሚገልጹ ምልክቶች ናቸው።

127፥3 *ልጆች፤* የቍ1 ማብ ይመ። ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ በሩካቤ ሥጋ የሚገኙ ብቻ አይደሉም (113፥9 እና ማብ፤ እንዲሁም ዘፍ30፥2 ይመ)። *ስጦታ፤* እዚህ ላይ ቃሉ የሚያመለክተው ስጦታን እንጂ ባለቤትነትን አይደለም። ይሁን እንጂ ቃሉ ከዚህም የላቀ መልእክት ሊኖረው ይችላል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጠው "ርስት" የተስፋዪቱን ምድር ሲሆን (ዘኍ26፥53፤ ኢሱ11፥23፤ መሳ2፥6) ይህም ምድር እስራኤላውያን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያላቸው ጽኑ "መኖሪያ" ነው (ኢሱ1፥13)። ነገር ግን ልጅ ከሌላቸው በምድሪቱ ውስጥ ርስት አይኖራቸውም (ዘኍ27፥8-11)፤ ስለዚህ ልጆች ትልቅ ስጦታ ናቸው ማለት ይቻላል። *በረከት ናቸው፤* እግዚአብሔር ታማኝ በመሆኑ በፊቱ ሞገስ ላገኙ ሁሉ የሚሰጠው በረከት ነው።

127፥5 *ከጠላቶቻቸው ጋር በአደባባይ በሚሟገቱበት ጊዜ፤* ብዙ ወንዶች ልጆች ያሉት ሰው በሐሰት ተከሶ ፍርድ ቤት በሚቀርብበት ጊዜ አብረውት የሚቆሙ በርካታ ተሟጋቾች አሉት። ከዚህም በላይ አንድ ሰው በእግዚአብሔር ቸርነት ብዙ ወንዶች ልጆች ካገኘ ይህ ነገር የሚያረጋግጠው በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ማግኘቱን ጭምር ነው (128፥3-4 ይመ)። *በአደባባይ፤* የከተማ መግቢያ በሮች እንደ ፍርድ አደባባይ ያገለግላሉ (ዘዳ 17፥5፤ 21፥19፤ 22፥15፡24፤ 25፥7፤ ሩት4፥1፤ ኢሳ29፥21 ይመ)።

*መዝ128፤* በእግዚአብሔር መንገድ የሚሄድ የእግዚአብሔር ሰው የተባረከ መሆኑን የሚገልጽ መዝሙር ነው፤ ስለ ቤትና ስለ ንብረት የሚናገር ሌላው የጥበብ ቃል ነው (መዝ127 ይመ)። የመዝሙሩ የመዝጊያ ቃል እንደሚያመለክተው መዝሙሩ በመጀመሪያ ያገለግል የነበረው ከየቤታቸው መጥተው በኢየሩሳሌም ለማምለክ ለተሰበሰቡ ሰዎች የቡራኬ ቃል በመሆን ነበር። የተጻፈውም ከምርኮ በፊት ሳይሆን አይቀርም። ባወቃቀር ረገድ ሲታይ በቍ 1-4 ዙሪያ የሚገኘው ቅንብብ ("እግዚአብሔርን የሚፈሩ") እነዚህን ቍጥሮች ከመዝሙሩ ዐቢይ ክፍል/ዋና አካል ይለዩታል።

128 *ርእስ፤* የመዝ120 ርእስ ማብ ይመ።

*128፥1-4፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚባርክ የሚያረጋግጥ ክፍል ነው።

128፥1 *የተባረኩ፤* የ1፥1 ማብ ይመ። *እግዚአብሔርን የሚፈሩ፤* የ34፥8-14 ማብ ይመ። *በመንገዱም፤* የ25፥4 ማብ ይመ።

*128፥2፤* እግዚአብሔር የድካምን ፍሬ ይባርካል።

*128፥3፤* ታማኝና ፍሬያም ናት። *ወይን፤* የፍሬያማነት ምሳሌ ነው (ዘፍ49፥22)፣ ማራኪ (ማሕ7፥8-12)፣ አስደሳች (መሳ 9፥13) መሆንን ይገልጻል። *በቤትህ፤* ይህች ሴት እንደማትታመነውና "እግሮቿም በቤቷ አይቀመጡም" (ምሳ7፥11) እንደ ተባለችው ሴት አይደለችም። *ወይራ ተክል፤* ምን ጊዜም ለምለም ዛፍ ሲሆን ይህም ረጅም ዘመን እንደሚኖርና ፍሬያማ እንደሚሆን ተስፋ የሚሰጥ ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የወይን ተክልና የወይራ ዛፍ አብዛኛውን ጊዜ በአንድነት ተጠቅሰዋል (ለምሳሌ በዘፀ 23፥11 ላይ እንደ ተጻፈው ማለት ነው)። እነዚህ ሁለት ተክሎች ብዙ ዘመን መኖር የሚችሉ ከመሆናቸውም በላይ የወይን ጠጅና የወይራ ዘይት ምርት የሚያስገኙ፣ በሕዝቡም የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ከፍ ያለ ሚና የሚጫወቱ ተክሎች ናቸው። *በማእድህ ዙሪያ፤* የእያንዳንዱ ቤተ ሰብ የዕለት ተለት ምግብ ወደ አንድ ታላቅ ቤተ ሰባዊ ደስታ ይለውጣል።

*128፥5-6፤* የቡራኬ ቃል ሲሆን ይህም እውነተኛ በረከት ምን ምን እንደሚያጠቃልል ይገልጻል፤ እውነተኛ በረከት የማያቋርጥ ብልጽግናን፣ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነትንና የጸና ሕልውናን (ኢየሩሳሌም የምትበለጽገው ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነትና የጸና ሕልውና ሲኖራት ነው) እንዲሁም ረጅም ዘመን መኖርን ያጠቃልላል።

128፥5 *ከጽዮን፤* 9-11 እና ማብ፤ እንዲሁም 20፥2፤ 135፥21 ይመ።

128፥6 *በእስራኤል ላይ ሰላም ይውረድ፤* 125፥5 እና ማብ ይመ።

*መዝ129፤* በየጊዜው የሚነሡባት ኀያላን ጠላቶቿ ሁሉ እንደ ቅጠል እንዲረግፉ እስራኤል በየጊዜው የምታቀርበው ጸሎት ነው። እግዚአብሔር ስለታደጋቸው ክብረ በዓል አድርገዋል (ቍ4)፤ ምናልባት እዚህ ላይ ክብረ በዓል ያደረጉት ከባቢሎን ምርኮ ስለታደጋቸው ሊሆን ይችላል። እንደ መዝ128 ሁሉ ይህም መዝሙር የተበጀው በተመጣጠኑ ሁለት አንጓዎች ነው።

129 *ርእስ፤* የመዝ120 ርእስ ማብ ይመ።

*129፥1-4፤* ክፉ ጨቋኞች ብርቱ እንደሆኑ አይኖሩም።

129፥1 *ከልጅነቴ ጀምሮ፤* እስራኤል በግብፅ በባርነት ሥር ከነበረችበት ጊዜ አንሥቶ በኀያላን ጠላቶቿ እጅ ብዙ ግፍና መከራ ደርሶባታል።

129፥2 *ድል አላደረጉኝም፤* እስራኤልን ፈጽመው ሊያጠፏት ወይም ለዘላለም ቀጥቅጠው በባርነት ሊገዟት አልቻሉም።

129፥4 *ጻድቅ፤* የ4፥1 ማብ ይመ።

የከፋዎችን ገመድ በጣጥሶ ጣለው።
5 ጽዮንን የሚጠሉ ሁሉ፣
ዐፍረው ወደ ኋላቸው ይመለሱ።
6 ገና ከመብቀሉ እንደሚደርቅ፣
በጣራ ላይ እንደ በቀለ ሣር ይሁኑ፤
7 ደግሞም ለዐጫጅ እጁን፣
ለነዶ ሰብሳቢ ዕቅፉን እንደማይሞላ
ይሁኑ።
8 መንገድ ዐላፊዎችም፣
"የእግዚአብሔር በረከት በእናንተ ላይ
ይሁን፤
በእግዚአብሔር ስም እንባርካችኋለን"
አይበሉ።

## መዝሙር 130

### ለርዳታ የቀረበ ጥሪ

*መዝሙረ መዓርግ*

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤
ከጥልቅ ወደ አንተ እጮኻለሁ።
2 ጌታ ሆይ፤ ድምፄን ስማ፤
ጆሮዎችህ የልመናዬን ቃል፣
የሚያዳምጡ ይሁኑ።
3 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ኀጢአትን ብትቈጣጠር፣
ጌታ ሆይ፤ ማን ሊቆም ይችላል?
4 ነገር ግን በአንተ ዘንድ ይቅርታ አለ፤
ስለዚህም ልትፈራ ይገባሃል።
5 *እግዚአብሔርን* ደጅ እጠናለሁ፤ ነፍሴም
በትዕግሥት ትጠብቀዋለች፤
በቃሉም ተስፋ አደርጋለሁ።
6 ዘብ ዐዳሪ ንጋትን ከሚጠባበቅ ይልቅ፣
አዎን፤ ዘብ ዐዳሪ ንጋትን ከሚጠባበቅ
ይልቅ፣
ነፍሴ ጌታን ትጠባበቃለች።
7 *በእግዚአብሔር* ዘንድ ምሕረት፣
በእርሱም ዘንድ ማዳን አለና፣
እስራኤል ሆይ፤ *በእግዚአብሔር*
ተስፋ አድርግ።
8 እርሱም እስራኤልን፣
ከኀጢአቱ ሁሉ ያድነዋል።

## መዝሙር 131

### በእግዚአብሔር መታመን

*የዳዊት መዝሙረ መዓርግ*

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ልቤ አልታበየም፤
ዐይኔ ከፍ ከፍ አላለም፤
ሐሳቤ ለዐጕል ትልቅነት አልተነሣሣም፤
ከዐቅሜም በላይ አልተንጠራራሁም።
2 ነገር ግን ነፍሴን ጸጥ፣ ዝም አሰኘኋት፤
ጡት የጣለ ልጅ ዐርፎ እናቱ ላይ
እንደሚቀመጥ፣
ነፍሴ ጡት እንዳስተዉት ሕፃን በውስጤ
ጸጥ አለች።
3 እስራኤል ሆይ፤ ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም፣
*በእግዚአብሔር* ተስፋ አድርግ።

129፥5 መዝ70፥2፤ ሚክ4፥11
129፥6 2ነገ19፥26፤ መዝ102፥11፤ ኢሳ 37፥27
129፥7 ዘዳ28፥38፤ መዝ79፥12
129፥8 መዝ118፥26
130፥1 ኢዮ30፥19፤ መዝ22፥2፤42፥7፤55፥17፤142፥5፤ሰቆ3፥55
130፥2 2ዜና6፥40፤መዝ27፥7፤28፥2፡6፤31፥22፤86፥6፤140፥6
130፥3 1ሳሙ6፥20፤ዕዝ9፥15፤መዝ143፥2፤ናሆ1፥6፤ራእ6፥17
130፥4 ዘፀ34፥7፤ 2ሳሙ24፥14፤1ነገ 8፥40፤ኤር31፥34
130፥5 መዝ5፥3፤ 27፥14፤119፥74፤ኢሳ 8፥17፤26፥8፤30፥18፤ 49፥23
130፥6 2ሳሙ23፥4፤መዝ63፥6
130፥7 1ዜና21፥13፤መዝ25፥5፤71፥14፤ 111፥9፤ሮሜ3፥24
130፥8 ዘፀ34፥7፤ ሉቃ1፥68፤ማቴ1፥21
131፥1 2ሳሙ22፥28፤ኢዮ5፥9፤41፥34፤ መዝ101፥5፤139፥6፤ ኢሳ2፥12፤ኤር45፥5፤ ሮሜ12፥16
131፥2 መዝ116፥7፤ማቴ18፥3፤1ቆሮ 13፥11፤14፥20 131፥3 መዝ25፥5፤113፥2፤119፥43፤130፥7

*129፥5-8፤* ጽዮንን የሚጠሉ ሁሉ እንደ ደረቀ ዛፍ ይሁኑ።

*129፥5፤* የ5፥10 ማብ ይመ።

129፥6 *በጣራ ላይ እንደ በቀለ ሣር ይሁኑ፤* የእስራኤልን ጀርባ በጅራፍ የሚተለትሉ (ቍ3)፣ ደረቱን ለፀሓይ በሰጠ ጣራ ላይ በቅሉ እንደደረቀ ሣር ይሁኑ፤ ማንም ዐርሶና አለስልሶ የሚዘራባቸውና ነዶ የሚሰበስብባቸው አይሁኑ (ቍ7)።

129፥8 *የሚያልፉ የሚያገድሙትም፤* በአጫጆቹ እርሻ ላይ የሚያልፉ የሚያገድሙ ሁሉ ከአጫጆች ጋር የደስታ ሰላምታ አይለዋወጡም (ሩት2፥4)፤ ምክንያቱም የአጫጆቹ እጅ ሥራ ይፈታል።

*መዝ130፤* ምንም እንኳ ኀጢአተኛ ቢሆንም ከጥልቅ ሆኖ የሚያሰማውን ጩኸት እግዚአብሔር እንደሚሰማው እርግጠኛ የሆነ ሰው ያቀረበው ምስክርነት ነው። የመዝሙሩ ቃላት እንደሚያመለክቱት መዝሙሩ የተጻፈው ከምርኮ በኋላ ነው። መዝሙሩ ከሰባቱ የንስሓ መዝሙሮች (የመዝ6 መግቢያ ይመ) ውስጥ ስድስተኛው ነው። መዝሙሩ በአራት ቤት የተዋቀረ ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው ሁለት ቤት ባላቸው ሁለት ክፍሎች ይከፈላል።

*130ርእስ፤* የመዝ120 ርእስ ማብ ይመ።

*130፥1-4፤* ምሕረትን ለማግኘት የቀረበ ጸሎት ነው፤ ምሕረትን እንደሚያገኝም እርግጠኛ ነው።

130፥1 *ከጥልቅ፤* 69፥2 ላይ እንደ ተጠቀሰው ነው (የ30፥1፤ 32፥6 ማብ ይመ)።

130፥4 *ይቅርታ … አለ፤* ይህን የተናገረው በዘፀ34፥6-7 ላይ ያሉትን ቃላት እያሰበ ስለ መሆኑ ምንም አያጠራጥርም። *ትፈራለህ፤* እውነተኛ አምላክ ተደርገህ ትከበራለህ፣ ትመለካለህ፣ ትታመናለህ፣ ትገለገላለህ ማለት ነው። እግዚአብሔር ይቅር ባይ አምላክ ባይሆን ኖሮ ሰዎች በፍርሀት ተይዘው ከእርሱ ይሸሹ ነበር።

*130፥5-8፤* በእግዚአብሔር የሚታመን መሆኑን የገለጸበት ክፍል ነው፤ የግል ምስክርነቱን በስፋት ሰጥቶአል (131፥3 ይመ)።

130፥5 *ደጅ እጠናለሁ፤* በተስፋ እጠባበቃለሁ ማለቱ ነው። *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ። *ቃሉ፤* በተለይም በቃል ኪዳኑ ላይ የተጠቀሱትን የተስፋ ቃሎች ማለት ነው (119፥25፡28፡37፡42፡ 49፡65፡74፡81፡107፡114፡147 ይመ)።

130፥6 *ዘብ፤* 127፥1፤ 2ሳሙ13፥34፤ 18፥24-27፤ ማሕ3፥3፤ 5፥7 ይመ። *ንጋት፤* የመዝ57 መግቢያ ይመ፤ የ59፥9 ማብ ይመ።

130፥7 *ምሕረት፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

130፥8 *ከኀጢአቱ ሁሉ፤* ኀጢአት ከሚያስከትለው መዘዝ ሁሉ ማለት ነው። ይህ ታላቅ ተስፋ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጽሞአል።

*መዝ131፤* በትሕትና በእግዚአብሔር ላይ የሚታመን ሰው የተናገረው ቃል ነው፤ ከመዝ130 ቀጥሎ በመቀመጡ አግባብነት አለው።

131ርእስ *የዳዊት የምዕራግ፤* የመዝ120 ርእስ ማብ ይመ።

131፥1 *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *አልታበየም … ከፍ ከፍ አላለም፤* ከምንም ነገር ይልቅ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያጣላው ትዕቢት ነው (የ31፥23 ማብ ይመ፤ ከ2ሳሙ6፥21-22 ጋር ያነጻጽሩ)። *ለትልቅነት አልተነሣሣም፤* በመካከላቸው አልገኝም፤ አልኖርም፤ ከእነር ሱም ጋር አልተባበርም ማለት ነው። *ከዐቅሜም በላይ፤* የእግዚአብሔርን ሥራ ከንቱ ለማስቀረት የተፈጸሙ ተግባራት ናቸው። እዚህ ላይ የተባለው ነገር የሚያተኩረው የእግዚአብሔርን ዐይነት ኀይል ማግኘት ላይ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ዐይነት ማስተዋል ማግኘት ላይ ነው።

131፥2 *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ። *ጡት የጣለ ልጅ፤* ከእናቱ አጠገብ እንደማይለይ የአራት ወይም የአምስት ዓመት ሕፃን ማለት ነው።

*131፥3፤* እንደ መዝሙረኛው ሁሉ የእስራኤልም ሕዝብ እግዚአብሔርን ዘወትር ተስፋ አድርጎ መኖር አለበት።

*መዝ132፤* የመዝሙሩ አወቃቀር እንደሚያሳየው በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጦ ለሚገዛው የዳዊት ልጅ እግዚአብሔር ሞገስ እንዲሆንለት የቀረበ ጸሎት ነው (የቍ10 ማብ ይመ)። የመዝሙሩ ቋንቋ እንደሚያመለክተው መዝሙሩ የተጻፈው በነገሥታት ዘመን ዋዜማ ላይ ነው። ይህ መዝሙር የተጻፈው በቤተ መቅደሱ ምረቃ በዓል ላይ እንዲዘመር ነው የሚለው አባባል ትክክል ሊሆን ይችላል (ከቍ8-10 ያለውን ከ2ዜና 6፥41-42 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ሆኖም በሥርዐተ ንግሥ ላይ እንዲዘመር ታስቦ የተደረሰ መዝሙር ነው የሚለው አባባልም ሊካድ አይችልም (ከመዝ 2፤72፤110 ጋር ያነጻጽሩ)። የዜና መጻሕፍት ደራሲ ይህን ጸሎት የጸለየው ራሱ ንጉሡ እንደሆነ አድርጎ አቅርቦታል። መዝሙሩ ሁለት አቤቱታዎች ያሉት ሲሆን (ቍ1፡10) ከሁለቱም አቤቱታዎች ቀጥሎ ሁለት ባለ አራት መስመር እንጓዎች

## መዝሙር 132

### የክብረ በዓል መዝሙር

132፥8-10 ተጓ ምብ-2ዜና 6፥41-42

*መዝሙረ መዓርግ*

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ዳዊትን፣
የታገሠውንም መከራ ሁሉ ዐስብ፤
2 እርሱ *ለእግዚአብሔር* ማለ፤
ለያዕቆብም ኀያል አምላክ እንዲህ ሲል
ተሳለ፤
3 "ወደ ቤቴ አልገባም፤
ዐልጋዬም ላይ አልወጣም፤
4 ለዐይኖቼ እንቅልፍን፣
ለሽፋሽፍቶቼም ሽለብታ አልሰጥም፤
5 *ለእግዚአብሔር* ስፍራን፣
ለያዕቆብም ኀያል አምላክ ማደሪያን
እስካገኝ ድረስ።"

6 እነሆ፤ በኤፍራታ ሰማነው፤
በቂርያት ይዓሪም* አገኘነው።
7 "ወደ ማደሪያው እንግባ፤
እግሮቹ በሚቆሙበት ቦታ እንስገድ።
8 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ተነሥ፤
አንተና የኀይልህ ታቦት ወደ ማረፊያህ
ስፍራ ሂዱ።
9 ካህናትህ ጽድቅን ይልበሱ፤
ቅዱሳንህም እልል ይበሉ።"

10 ስለ አገልጋይህ ስለ ዳዊት ስትል፣
የቀባኸውን ሰው አትተወው።

11 *እግዚአብሔር* ለዳዊት በእውነት ማለ፤
በማይታጠፍም ቃሉ እንዲህ አለ፤
"ከገዛ ራስህ ፍሬ፣
በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ።
12 ወንዶች ልጆችህ ኪዳኔን፣
የማስተምራቸውንም ምስክርነቴን ቢጠብቁ፣
ልጆቻቸው በዙፋንህ ላይ፣
ለዘላለም ይቀመጣሉ።

13 *እግዚአብሔር* ጽዮንን መርጦአታልና፣
ማደሪያውም ትሆን ዘንድ ወዶአልና
እንዲህ አለ፤
14 "ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት፤
ፈልጌአታለሁና በእርሷ እኖራለሁ።
15 እጅግ አትረፍርፌ እባርካታለሁ፤

*6 አንዳንዶቹ *ያዓር* ይላሉ።

132፥1 1ሳሙ 18፥11 ፤2ሳሙ 15፥14
132፥2 ዘፍ49፥24፤ ኢሳ49፥26፤60፥16
132፥3 2ሳሙ7፥2፡27
132፥5 1ነገ8፥17 ፤ሐሥ7፥46
132፥6 ኢሱ9፥17፤ 1ሳሙ7፥2፤17፥12
132፥7 2ሳሙ15፥25፤1ዜና28፥2፤ መዝ5፥7፤122፥1
132፥8 ዘኍ10፥35
132፥9 ኢዮ27፥6፤ መዝ16፥3፤30፥4፤149፥5 ፤ኢሳ61፥3፡10፤ዘካ3፥4 ፤ሚል3፥3፤ኤፌ6፥14
132፥11 1ዜና17፥11 -14፤መዝ89፥3-4፡35፤ ማቴ1፥1፤ሉቃ3፥31
132፥12 2ዜና6፥16 ፤መዝ25፥10፤ሉቃ 1፥32፤ሐሥ2፥30
132፥13 ዘዐ15፥17፤ 1ነገ8፥13፤መዝ48፥1-2 ፤68፥16
132፥14 ቍ8፤2ሳሙ 6፥2፤መዝ68፥6፤80፥1
132፥15 መዝ107፥9 ፤147፥14

ቀርበዋል፤ ሁሉም ተመሳሳይ ቅርጽ አላቸው። የጸሎቱ የመጨረሻ ባለ ሁለት ቤት ክፍል የጸሎቱ መደምደሚያ ነው። አራቱ አንጓዎች ከጸሎቱ የመጨረሻ ባለ ሁለት ቤት ክፍል ጋር በቍ1፡10 ላይ ለቀረበው ጸሎት መሠረት ናቸው። ቍ2-9 ዳዊት ለታቦቱ "ስፍራ" እንደሚያዘጋጅና ካለበትም ቦታ አምጥቶት "በማረፊያው ስፍራ" ላይ እንደሚያኖረው ለእግዚአብሔር የገባውን ቃለ መሐላ የሚናገር ሲሆን፣ ቍ11-18 ደግሞ እግዚአብሔር ጽዮንን የራሱ ማረፊያ አድርጎ እንደሚመርጥና ለዳዊት የገባውን ቃለ መሐላ ይናገራል (ነገር ግን የቍ10 ማብ ይመ)።

*132ርእስ፤* የመዝ120 ርእስ ማብ ይመ።

132፥1 *አስብ፤* 20፥3፤ 1ነገ11፥12-13፤ 15፥4-5 ይመ። *መከራ፤* በስእለቱ ላይ የተናገራቸው ናቸው (ቍ2-5፤ ራስን በመካድ የተነገረውን ተመሳሳይ ቃለ መሐላ በዘኍ20፥13 ላይ ይመ)።

132፥2 *ማለ፤* ይህ ለዳዊት ልጅ የተጸለየው ጸሎት በዳዊትና በእግዚአብሔር መካከል ባለው ልዩ አንድነት ላይ የተመሠረተ ነው፤ ይህም በመካከላቸው ባለው የጋራ ቃለ መሐላ በሚገባ ታይቶአል (ቍ11-12 ይመ)። እዚህ የተጠቀሰውን ታሪክ በሚያብራራው (2ሳሙ6-7) ክፍል ላይ የዳዊት ቃለ መሐላ አልተጠቀሰም። *ለያዕቆብም ኀያል አምላክ፤* ቍ5፤ ኢሳ 1፥24፤ እንዲሁም የ3፥7 ማብ ይመ። *ያዕቆብ፤* የእስራኤል ሌላው ስሙ ነው (ዘፍ32፥28 ይመ)።

132፥6 *ሰማነው ... አገኘነው፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። አብዛኛውን ጊዜ ታቦቱን የሚያመለክት ቃል ተደርጎ ቢወሰድም ቃሉ ግን የሚያመለክተው ለአምልኮ የተደረገውን ጥሪ ነው። *ኤፍራታ፤* የዳዊት መኖሪያ በሆነችው በቤተልሔም (ሩት 4፡11፤ ሚክ5፥2) አካባቢ የሚገኝ ስፍራ ነው። *በቂርያትይዓሪም፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ 2ሳሙ6፥2 ይመ። ለአምልኮ የተደረገው ጥሪ ከዳዊት ከተማና ከሳሙኤል ጊዜ ጀምሮ ታቦቱ እንዲቀመጥ ከተደረገበት ከተማ (1ሳሙ7፥1 ይመ) እንደ መጣ ተደርጎ ተገልጾአል። ጥሪው የመጣው ቤተ መቅደሱ ከተሠራ በኋላ ይመስላል።

132፥7 *በእግሩ መርገጫ፤* 99፥5 እና ማብ ይመ።

132፥8 *ተነሥ፤* ምንም እንኳ ዕብራይስጡ የመነሻ/የመግቢያ ቃል የሚገድፍ ቢሆንም (በዕብራይስጥ ግጥም ውስጥ የመነሻ ቃል ተገድፎ ማግኘት የተለመደ ነው)፣ በቍ8-9 ላይ የተጠቀሱት ቃላት በቤተ መቅደስ ለአምልኮ የመጡ ሰዎች የተናገሩት ሊሆን ይችላል። የመዝ24 ማብ ይመ። *ማረፊያህ ስፍራ፤* የተስፋ ዪቱ ምድር እስራኤል በምድረ በዳ ስትንከራተት ከቈየች በኋላ የእስራኤል ማረፊያ ስፍራ እንደ ሆነች ሁሉ (ዘኍ10፥33፤ ኢሱ 1፥13፤ ሚክ2፥10 ይመ) ቤተ መቅደሱም ታቦቱ በየድንኳኑ ሲንከራተት ከቈየ በኋላ ያረፈበት ስፍራ ነው (2ሳሙ7፥6፤ እንዲሁም 1ዜና28፥2 ይመ)። ቃሉ እንደሚያመለክተው ቤተ መቅደሱ የእግዚአብሔር ዙፋን መቀመጫ ቦታ ነው (ቍ14)። *የኀይልህ ታቦት፤* የ78፥61 ማብ ይመ።

132፥9 *(ጽድቅን) ይልበሱ፤* በቤተ መቅደስ ሲያገለግሉ ከሚለብሱት የዘወትር ልብስ በተጨማሪ አገልግሎታቸው ጽድቅን እንዲለብስ የሚያሳስብ ነው (ኢዮ29፥14፤ምሳ31፥25 ይመ)። *ጽድቅ፤* ከዚህ ቃል ጋር ተዛማጅ የሆነው ቃል በቍ16 ላይ "ድነትን" ተብሎ የተጠቀሰው ቃል በመሆኑ፣ የመጽሐፈ ዜና ጸሐፊ ይህንን ክፍል ጠቅሶ ሲጽፍ (2ዜና6፥4) ይሄንኑ ቃል ተጠቅሞአል፤ እነዚህ ሁለት ቃላት ማለትም "ጽድቅና ድነት" አብዛኛውን ጊዜ ተጓድነው የቀረቡ በመሆናቸው (40፥10፤ 51፥14፤ 71፥15፤ 98፥2፤ ኢሳ45፥8፤ 46፥13፤ 51፥5-6፤ 56፥1፤ 59፥17፤ 60፥17-18፤ 61፥10፤ 62፥1) እዚህ ላይ ቃሉ በግልጽ የሚያመለክተው ሕዝቡን የሚያድነውን የእግዚአብሔርን ጽድቅ ነው (የ4፥1 ማብ ይመ)። *ቅዱሳንህም፤* የ4፥3 ማብ ይመ።

*132፥10፤* ቍ1 ይመ። *አገልጋይህ፤* የመዝሙር 18 ርእስ ማብ ይመ። *አትተወው፤* አቤቱታውን ችላ አትበል ማለት ነው (በ1ነገ2፥16-17፡20 ላይ እንደ ተጠቀሰው 1ነገ8፥59፤ 2ዜና6፥41-42 ይመ)። አንዳንዶች እንደሚሉት በቍ1፡10 ላይ የተጠቀሱት አቤቱታዎች የመዝሙሩን የመጀመሪያ ክፍል የሚቀነብቡ ከሆነ የመዝሙሩ ሁለተኛ ክፍል ጸሎቱ መልስ እንደሚያገኝ ያረጋግጣል (ምናልባት አንድ ካህን ወይም ሌዋዊ ያቀረበው ጸሎት ሊሆን ይችላል)። ዳዊት ለልጆቹና ለእስራኤል ሕዝብ የጸሎት ማእከል እንዲሆን እግዚአብሔር የሚያድርበትን ቤት ለመሥራት የገባው ቃል (1ነገ8፥27-53፤ 9፥3፤ 2ዜና7፥15-16፤ ኢሳ56፥7 ይመ) ለአቤቱታውና እግዚአብሔር ለቀባው ሰው ጸሎት መልስ እንደሚሰጥ መሠረት ነው። *የቀባኸውን፤* የ2፥2 ማብ ይመ።

*132፥11-12፤* እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባው ቃል ኪዳን የጸሎቱ መሠረት ሆኖ ቀርቦአል። ይህ ክፍል እንዲሁም በቍ13-18 ላይ የሚገኘው ክፍል ከ1ነገ9፥1-5 ላይ ተወስዶ በግጥም መልክ የተጻፈ ነው (2ዜና 7፥11-18 ይመ)።

132፥11 *ማለ፤* ቍ2 እና ማብ ይመ። 2ሳሙ7 ስለ መሐላ የሚናገረው ምንም ነገር የለም፤ በሌላ ስፍራ ግን እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠው የተስፋ ቃል ኪዳን ተብሎአል (89፥3፡28፡34፡39፤ 2ሳሙ23፥5፤ ኢሳ55፥3)፤ ቃል ኪዳኖቹ በሙሉ የጸኑት በመሐላ ነው። *በማይታጠፍም፤* 110፥4 ይመ።

132፥12 *ኪዳኔን ... ምስክርነቴን፤* የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ እንዲጠብቁት በሲና የተሰጠውን ሕግ ያመለክታል (1ሳሙ 10፥25 እና ማብ፤ 1ነገ2፥3-4 ይመ)።

*132፥13-16፤* እግዚአብሔር ጽዮንን እንደ መረጠ የተናገረው ቃል የጸሎቱ መሠረት ሆኖ ቀርቦአል።

132፥13 *ማደሪያውም ትሆን ዘንድ ወዶአልና፤* የእግዚአብሔርና የዳዊት ምኞት አንድ መሆኑን ያሳያል (ዘዳ12፥5-14 ይመ)።

*132፥15፤* እግዚአብሔር በማረፊያው ስፍራ በዙፋኑ ላይ

ድኾቿን እንጀራ አጠግባለሁ።
16 ለካህናቷ ድነትን አለብሳለሁ፤
ቅዱሳኗም በደስታ ይዘምራሉ።

17 “በዚህም ለዳዊት ቀንድ[m] አበቅላለሁ፤
ለቀባሁትም ሰው መብራት አዘጋጃለሁ።
18 ጠላቶቹን ኀፍረት አከናንባቸዋለሁ፤
እርሱ ግን በራሱ ላይ የደፋው ዘውድ
ያበራል።

## መዝሙር 133

### የወንድማማች ፍቅር

የዳዊት መዝሙረ መዓርግ

1 ወንድሞች ተስማምተው በአንድነት
ሲኖሩ፣
እንዴት መልካም ነው! ምንኛስ ደስ
ያሰኛል!
2 በራስ ላይ ፈሶ፣
እስከ ጢም እንደሚዘልቅ፣
እስከ አሮን ጢም እንደሚወርድ፣
እስከ ልብሱም ዐንገትጌ እንደሚደርስ
ውድ ሽቱ ነው።
3 ደግሞም በጽዮን ተራራ ላይ
እንደሚወርድ፣
እንደ አርሞንዔም ጠል ነው፤
በዚያ እግዚአብሔር በረከቱን፣
ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዞአልና።

132፥16 2ዜና6፥41፤ኢዮ8፥21፤መዝ149፥5
132፥17 1ሳሙ2፥10፤1ነገ11፥36፤2ነገ8፥19፤2ዜና21፥7፤መዝ18፥28፤84፥9፤92፥10፤ሕዝ29፥21፤ሉቃ1፥69
132፥18 2ሳሙ12፥30፤ኢዮ8፥22
133፥1 ዘፍ13፥8፤ዮሐ17፥11፤ሮሜ12፥10
133፥2 ዘፀ29፥7
133፥3 ዘፀ15፥17፤ዘሌ25፥21፤ዘዳ3፥8፤4፥48፤ኢዮ29፥19፤መዝ2፥6፤21፥4፤74፥2፤ምሳ19፥12፤ኢሳ18፥4፤26፥19፤45፥8፤ሆሴ14፥5፤ሚክ5፥7
134፥1 ዘኍ16፥9፤1ዜና15፥2፤23፥30፤መዝ113፥1፤135፥1-2፤ራእ19፥5
134፥2 መዝ15፥1፤28፥2፤33፥2፤103፥1፤1ጢሞ2፥8
134፥3 ዘሌ25፥21፤መዝ20፥2፤መዝ124፥8
135፥1 ነሀ7፥73
135፥2 1ዜና15፥2፤መዝ116፥19፤ሉቃ2፥37

## መዝሙር 134

### የሡርክ መዝሙር

መዝሙረ መዓርግ

1 እናንት በሌሊት ቆማችሁ በእግዚአብሔር
ቤት የምታገለግሉ፣
የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁላችሁ፤ እግዚ
አብሔርን ባርኩ።
2 በመቅደሱ ውስጥ እጆቻችሁን አንሡ፤
እግዚአብሔርንም ባርኩ።
3 ሰማይንና ምድርን የሠራ እግዚአብሔር፣
ከጽዮን ይባርክህ።

## መዝሙር 135

### የምስጋና መዝሙር

135፥15-20 ተጓ ምብ-መዝ 115፥4-11

1 ሃሌ ሉያ።[w]

የእግዚአብሔርን ስም ወድሱ፤
እናንት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሆይ፤
አመስግኑት፤
2 በእግዚአብሔር ቤት፣
በአምላካችን ቤት አደባባይ የምትቆሙ
አመስግኑት።

[m]17 እዚህ ላይ ቀንድ የጥንካሬ ትእምርት ሲሆን ንጉሥን ያመለክታል።
[w]1 ቍ3 እና 21 ጭምር በአንዳንድ ትርጕሞች እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ።

ሲቀመጥ (ቍ8:14 ይመ) ምድሪቱ ትባረካለች፤ ለሕዝቡም የዕረፍት ስፍራ ትሆናለች (ዘዳ12፥9፤ኢሱ1፥13፤ 1ነገ5፥4 ይመ)።

*132፥16፤* የቍ9 ማብ ይመ።

*132፥17-18፤* በአቤቱታው ማብቂያ ላይ የተናገረው የእምነት ቃል ነው (ቍ1:10)።

132፥17 *ቀንድ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ እግዚአብሔር የቀባው ሰው ነው። *አበቅላለሁ፤* እንደ አትክልት ወይም ቅርንጫፍ ያብቅለዋል። *ለ ... መብራት አዘጋጃለሁ፤* የ1ነገ11፥36 ማብ ይመ።

132፥18 *ኀፍረት አከናንባቸዋለሁ፤* የቍ16 ተቃራኒ ነው። *የሚያንጸባርቅ ይሆናል፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ያብባል" ማለት ነው።

*መዝ133፤* በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያለውን ወንድማማችነት እያሰበ ያቀረበው የምስጋና መዝሙር ነው። የዚህ መዝሙር ጸሐፊ ዳዊት ከሆነ (ርእሱን ይመ) ይህን መዝሙር የጻፈው ከብዙ ዓመት ጦርነት በኋላ የእስራኤል ሕዝብ በኬብሮን ተሰብስቦ (2ሳሙ5፥1-3) ባነገሠው ጊዜ ነው። በዕብራይስጡ ትርጕም ላይ የመዝሙሩ የመጀመሪያና የመጨረሻ ቍጥሮች (1-3ለ) የመዝሙሩ ዐቢይ ሐሳብ ቀንብበውታል። በውስጥ በኩል የሚገኘው ቅንብብ (መስመር 2እና4) በሁለት ንጽጽሮች አማካይነት የመዝሙሩን መሪ ሐሳብ አጕልብቶታል። የመዝሙሩ እንብርት የሆነው ቍ2ለ ግን የመጀመሪያውን ንጽጽር ያብራራል።

133ርእስ *የዳዊት መዝሙረ መዓርግ፤* የመዝ120 ርእስ ማብ ይመ። *የዳዊት፤* ጥንታዊ ቅጆች ሁሉ ይህ መዝሙር በዳዊት መጻፉን አይገልጹም።

133፥1 *መልካም ... ደስ ያሰኛል፤* 135፥3፤ 147፥1 ይመ።

133፥2 *እስከ አሮን ጢም ... እስከ ልብሱም ዐንገትጌ ... ውድ ሽቱ፤* አሮን የሚቀባው ሽቱ (ዘፀ29፥7፤ ዘሌ 21፥10) የጢሙን ጠጕር ሁሉ አርሶ በክህነት ልብሱ ላይ ይፈሳል። ይህም አሮን ቅዱስ ለሆነ አገልግሎት መለየቱን ያመለክታል። ልክ እንዲሁ በወንድማማችነት ላይ የተመሠረተ ፍቅር የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይቀድሳል።

133፥3 *በጽዮን ተራራ ... እንደ አርሞንዔም ጠል፤* የአርሞንዔምን ተራራ የሚያረሰርሰው ጠል የጽዮንን ተራራ ያለመልማል (ዘፍ27፥28፤ ሐጌ1፥10፤ ዘካ8፥12 ይመ)። እንደዚሁም በወንድማማች ፍቅር ላይ የተመሠረተ አንድነት የእስራኤልን ሕዝብ አብዝቶ ይባርካል። እነዚህ ሁለት ንጽጽሮች (ቍ2-3) ትክክለኛ ንጽጽሮች ናቸው። ካህናት በቤተ መቅደስ በሚሰጡት አገልግሎት አማካይነት የእግዚአብሔር በረከት ለእስራኤል ሕዝብ ይፈሳል (ዘፀ29፥44-46፤ ዘሌ9፥22-24፤ ዘኍ6፥24-26)፤ ይህም የእግዚአብሔርን ምሕረት ያመለክታል። ከሰማይ በሚወርደው ጠል አማካይነት የምድር ፍጥረታት ሕይወት ያገኛሉ፤ ይህም የእግዚአብሔርን ቸርነት ይገልጻል። *ሕይወት፤* የቃል ኪዳኑ ታላቅ ስጦታ ነው (ዘዳ30፥15:19-20፤ 32፥47 ይመ)።

*መዝ134፤* ምእመናን የማታ አምልኮአቸውን ፈጽመው ወደ ቤታቸው ሊሄዱ ሲሉ ቤተ መቅደሱን እየጠበቁ ከሚያድሩት ሌዋውያን ጋር በመቀባበል የሚያዜሙት የውዳሴ መዝሙር ነው። መዝ117 የሃሌ ሉያ መዝሙሮች መደምደሚያ (መዝ111-117) እንደ ሆነ ሁሉ፣ ይህም መዝሙር የምዕራግ መዝሙሮች መደምደሚያ ነው። መዝሙሩ የተጻፈው ከምርኮ በኋላ ሳይሆን አይቀርም።

*134ርእስ፤* የመዝ120 ርእስ ማብ ይመ።

*134፥1-2፤* አምልኮአቸውን ፈጽመው ለመሄድ የተዘጋጁ ምዕመናን በቤተ መቅደስ የሚቀሩት ሌዋውያን ጌታን እያመሰገኑ እንዲያድሩ ያቀረቡት ጥሪ ነው (1ዜና9፥33 ይመ)።

134፥2 *እጆቻችሁን አንሡ፤* 63፥4 ይመ።

*134፥3፤* ከሌዋውያኑ አንዱ ለአምልኮ ለመጡት የሰጠው የቡራኬ ቃል ነው (የ121፥2 ማብ፤ እንዲሁም 124፥8፤128፥5 ይመ)።

*መዝ135፤* ለእውነተኛው አምላክ ለእግዚአብሔር ውዳሴ እንዲቀርብ የተደረገ ጥሪ ነው፤ እርሱ የፍጥረታት ሁሉ ጌታ ነው፤ የሕዝቦች ሁሉ ጌታ ነው፤ የእስራኤልም ታዳጊ ነው። መዝሙሩ የተጻፈው ከምርኮ በኋላ ስለ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፤ ምክንያቱም መዝሙሩ ከሌሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ላይ በርካታ ሐሳቦችን ወስዶአል። መዝሙሩ የተደረሰው በቤተ መቅደስ ውስጥ የተሰጥዎ መዝሙር እንዲሆን ታስቦ ነው። በሃሌ ሉያ መዝሙሮች ውስጥ ስላለው ስፍራ የመዝ120 ርእስ ማብ ይመ። መዝሙሩ የተቀነበበው ሃሌ ሉያ በሚለው ቃል ሲሆን (ከመዝ 146-150 ያሉትም የተቀነበቡት በዚሁ ጥሪ ነው) የመዝሙሩ የመጀመሪያና የመጨረሻ አንጓዎችም የምስጋና ጥሪ ያቀርባሉ። እግዚአብሔር እስራኤልን ለመቤዠት ሲል በግብፃውያንና በከነዓናውያን ላይ ያደረጋቸውን ታላላቅ ሥራዎች (ቍ8-12) እንደ ገና የሚያስታውስ ክፍል ሰባት አንጓዎች ያሉት ሲሆን የቀሩት አንጓዎች ደግሞ በመሪ ሐሳብና በቋንቋ ተሳስረዋል (ቍ3-4:13-14፤ ቍ5-7:15-18)።

*135፥1-2፤* ካህናቱና ሌዋውያኑ እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑ በመግቢያ ላይ (134፥1-2 ይመ) የቀረበ ጥሪ ነው።

135፥1:3:13 *ስም፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

*135፥3-4፤* እስራኤል እግዚአብሔርን የምታመሰግንበትን

[3]እግዚአብሔር ቸር ነውና እግዚአብሔርን
  አመስግኑ፤
 መልካም ነውና፣ ለስሙ ዘምሩ፤
[4]እግዚአብሔር ያዕቆብን ለራሱ፣
 እስራኤልንም ውድ ንብረቱ አድርጎ
  መርጦአልና።

[5]እግዚአብሔር ታላቅ እንደ ሆነ፣
 ጌታችንም ከአማልክት ሁሉ እንደሚበልጥ
  ዐውቃለሁና።

[6]በሰማይና በምድር፣
 በባሕርና በጥልቅ ሁሉ ውስጥ፣
 እግዚአብሔር ደስ ያሰኘውን ሁሉ
  ያደርጋል።
[7]እርሱ ደመናትን ከምድር ዳርቻ ያስነሣል፤
 መብረቅ ከዝናብ ጋር እንዲወርድ
  ያደርጋል፤
 ነፋሳትንም ከግምጃው ያወጣል።
[8]በኵር ሆኖ በግብፅ የተወለደውን፣
 ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ቀሠፈ።
[9]ግብፅ ሆይ፤ በፈርዖንና በአገልጋዮቹ ሁሉ
  ላይ፣
 በመካከልሽ ታምራትንና ድንቅን ሰደደ።
[10]ብዙ ሕዝቦችን መታ፤
 ኀያላን ነገሥታትንም ገደለ።
[11]የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን፣
 የባሳንን ንጉሥ ዐግን፣
 የከነዓንን ነገሥታት ሁሉ ገደለ፤
[12]ምድራቸውንም ርስት አድርጎ፣
 ለሕዝቡ ርስት እንዲሆን ለእስራኤል
  ሰጠ።

[13]እግዚአብሔር ሆይ፤ ስምህ ዘላለማዊ ነው፤
 እግዚአብሔር ሆይ፤ መታሰቢያህም

135፥3 1ዜና16፥34፤መዝ68፥4፤92፥1፤119፥68፤147፥1
135፥4 ዘፀ19፥5፤ዘዳ7፥6፤10፥15፤ሚል3፥17፤ቲቶ2፥14
135፥5 ዘፀ12፥12፤1ዜና16፥25፤ኢዮ21፥22፤መዝ48፥1፤145፥3
135፥6 መዝ115፥3፤ዳን4፥35፤ማቴ6፥10
135፥7 ዘዳ28፥12፤ኢዮ5፥10፤መዝ68፥9፤ኢሳ30፥23፤ኤር10፥13፤51፥16፤ኢል2፥23፤አሞ4፥13፤ዘካ10፥1
135፥8 ዘፀ4፥23፤12፥12
135፥9 ዘፀ7፥9፤መዝ136፥10-15
135፥10 ዘኍ21፥21-25፤ኢሉ24፥8-11፤መዝ44፥2፤78፥55፤136፥17-21
135፥11 ዘኍ21፥21፡26፡33፤ኢሉ12፥7-24፤24፥12
135፥12 ዘዳ29፥8
135፥13 ዘፀ3፥15፤መዝ102፥12
135፥14 ዘዳ32፥36፤1ሳሙ24፥15፤ዕብ10፥30
135፥15 መዝ96፥5፤ኢሳ2፥8፤31፥7፤37፥19፤40፥19፤ኤር1፥16፤10፥5፤ራእ9፥20
135፥16 1ነገ18፥26
135፥17 ኤር10፥14፤ዕን2፥19
135፥19 መዝ22፥23
135፥21 1ነገ8፥13፤2ዜና6፥2፤መዝ128፥5፤134፥3

 ከትውልድ እስከ ትውልድ ይኖራል።
[14]እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይፈርዳልና፣
 ለአገልጋዮቹም ይራራላቸዋል።

[15]የአሕዛብ ጣዖታት ከብርና ከወርቅ
  የተሠሩ፣
 የሰው እጅ ያበጃቸው ናቸው።
[16]አፍ አላቸው፤ አይናገሩም፤
 ዐይን አላቸው፤ አያዩም፤
[17]ጆሮ አላቸው፤ አይሰሙም፤
 በአፋቸውም እስትንፋስ የለም።
[18]እነዚህን የሚያበጁ፣
 የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ
  ይሁኑ።

[19]የእስራኤል ቤት ሆይ፤ እግዚአብሔርን
  ባርኩ፤
 የአሮን ቤት ሆይ፤ እግዚአብሔርን
  ባርኩ፤
[20]የሌዊ ቤት ሆይ፤ እግዚአብሔርን ባርኩ፤
 እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሆይ፤ እግዚ
  አብሔርን ባርኩ።
[21]በኢየሩሳሌም የሚኖር እግዚአብሔር፣
 ከጽዮን ይባረክ።

ሃሌ ሉያ።

## መዝሙር 136
### ምስጋና በቅብብሎሽ መዝሙር

[1]እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ቸር ነውና፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
[2]የአማልክትን አምላክ አመስግኑ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።

136፥1 ቍ2-26፤2ዜና5፥13፤ዕዝ3፥11፤መዝ100፥5፤105፥1፤106፥1፤118፥1-4፤145፥9፤ኤር33፥11፤ናሆ1፥7 136፥2 ዘዳ10፥17፤መዝ105፥1

ምክንያት የሚገልጽ ክፍል ነው (ቍ13-14 ይመ)።

135፥3 *መልካም ነውና፤* 133፥1 ይመ። ወይም "እግዚ አብሔር ውብ ስለ ሆነ" ማለት ነው (የ27፥4 ማብ ይመ)።

135፥4 *ያዕቆብን፤* እስራኤል ማለት ነው (ዘፍ32፥28 ይመ)። *ውድ ንብረቱ፤* ዘፀ19፥5 እና ማብ ይመ።

*135፥5-7፤* እግዚአብሔር ታላቅ ነው፤ ደግሞም መልካም አምላክ ነው (ቍ3)፤ በፍጥረት ሁሉ ላይ ፍጹም ገዥ እርሱ ብቻ ነው (ከቍ15-18 ጋር ያነጻጽሩ፤ ኤር10፥11-16፤ 115፥3፤ 96፥5፤ 97፥7 እና ማብ ይመ)።

135፥6 *ያሰኘውን ያደርጋል፤* አማልክት አንዳች ነገር ማድ ረግ አይችሉም (ቍ16-17) ምክንያቱም እነርሱ ራሳቸው በአምላ ኪዎቻቸው እጅ የተሠሩ አማልክት ናቸው (ቍ18)። *በሰማይና በምድር ... በባሕርና፤* በጥንት ሕዝቦች አመለካከት መሠረት በሥነ ፍጥረት ውስጥ የሚታዩ ሦስቱ ታላላቅ ክፍሎች ናቸው (ዘፍ1፥8-10 እና የመዝ104 መግቢያ ይመ)።

135፥7 *ደመናትን ... ያስነሣል፤* በኣል ወይም ሌላ አም ላክ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ራሱ ሕይወት የሚሰጠውን ዝናብ ያዘንባል (መዝ29 ይመ)። *ነፋሳትንም፤* 104፥4፤ 148፥8 ይመ። የአሕዛብ አማልክት በአፋቸው ውስጥ "ነፋስ" (እስትንፋስ) እንኳ የላቸውም (ቍ17)። *ከግምጃው፤* 33፥7 እና ማብ፤ ኢዮ38፥22 ይመ።

*135፥8-12፤* እግዚአብሔር በግብፅና በነገሥታት ላይ የተቀ ዳጀውን ድል የሚገልጽ ክፍል ሲሆን፣ በእስራኤል ርስት አድርጎ የሚሰጠውም የእነዚህን ሕዝቦች ምድር ነው፤ ከዘፀ7-14፤ ከዘኍ 21፥21-35፤ ከኢያሱ ላይ የተወሰደ ሐሳብ ነው።

*135፥13-14፤* ቍ፩-4 እና ማብ ይመ።

135፥14 *ይፈርዳልና፤* ሕዝቡን ከክፉ ኀይሎች ሁሉ ይጠብ ቃል፤ በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ሕዝቡ ሁሉ ምስክር ይሆናል። *ይራራላቸዋል፤* ዘፀ34፥6-7 ይመ። አገልጋዮቹ የቃል ኪዳን ሕዝቡ ማለት ነው።

*135፥15-18፤* የሐሰት አማልክትና በእነርሱ የሚታመኑ ሁሉ ከንቱ መሆናቸውን የሚገልጽ ክፍል ነው (ቍ5-7 እና ማብ፤ 115፥4-8 እና ማብ ይመ)።

*135፥19-21፤* ለአምልኮ በቤተ መቅደሱ ለተሰበሰቡት ሁሉ የቀረበ ጥሪ መደምደሚያ ነው (115፥9-11፤ 118፥2-4 ይመ)።

*መዝ136፤* እግዚአብሔር ፈጣሪና የእስራኤል ታዳጊ እንደ ሆነ የሚናገር የቅዳሴ መዝሙር ነው። መሪ ሐሳቡና ቍጥሮቹ ከመዝ135 ጋር ተጓዳኝ ናቸው። አንድ ሌዋዊ የመዝሙር መሪ የመዝሙሩን ዋና ቍጥር ሲናገር የሌዋውያን መዘምራን (1ዜና 16፥41፤ 2ዜና5፥13፤ ዕዝ3፥11) ወይም ለማምለክ የተሰበሰቡ ምዕ መናን (2ዜና7፥3፡6፤ 20፥21) አዝማቹን በመናገር መልስ ይሰጣሉ (106፥1፤ 107፥1፤ 118፥1-4፡29)። ይህ የቅዳሴ መዝሙር "የሃሌ ሉያ መዝሙሮች" መደምደሚያ ነው (የመዝ120 ርእስ ማብ ይመ)። ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዲቀርብ ከተደረገው ጥሪ (ቍ1-3) በኋላ ስድስት ቍጥሮች ስለ እግዚአብሔር ፈጣሪነት (ቍ4-9)፣ ስድስቱ እስራኤልን ከግብፅ ስለመታደጉ (ቍ10-15)፣ አንዱ ስለ ምድረ-በዳው ጕዞ (ቍ16)፣ ስድስቱ ደግሞ ከነዓንን ድል አድርገው ስለ መውረሳቸው ያናገራሉ (ቍ17-22)። በመዝሙሩ መደምደ ሚያ ላይ የሚገኙት አራት ቍጥሮች ከላይ የተጠቀሱትን ዐቢይ ሐሳቦች እንደ ገና ደግመው ያወሳሉ፤ ይኸውም፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሲል በታሪክ ውስጥ የፈጸማቸውን ተግባራት (ቍ23-24)፣ ለፍጥረት ሁሉ የሚያስፈልጋቸውን በመ ስጠት የሚያከናውናቸውን ተግባራት (ቍ25) እንዲሁም በመዝ ጊያ ላይ የቀረበውን ጥሪ (ቍ26) ያወሣሉ።

136፥1-3፡26 *አመስግኑ፤* ወይም "አወድሱ" ማለት ነው (የ7፥17 ማብ ይመ)።

136፥2 *የአማልክትን አምላክ፤* ዘዳ10፥17፤ 135፥5 ይመ።

3የጌቶችን ጌታ አመስግኑ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
4እርሱ ብቻውን ታላላቅ ታምራትን
 የሚያደርግ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
5ሰማያትን በብልኀት የሠራ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
6ምድርን በውሃ ላይ የዘረጋ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
7ታላላቅ ብርሃናትን የሠራ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
8ፀሐይ በቀን እንዲሠለጥን ያደረገ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
9ጨረቃና ከዋክብት በሌሊት
 እንዲሠለጥኑ ያደረገ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
10የግብፅን በኵር የመታ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
11እስራኤልን ከመካከላቸው ያወጣ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
12በኀያል እጅና በተዘረጋች ክንድ
 ይህን ያደረገ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
13የኤርትራን ባሕር[ሀ] ለሁለት የከፈለ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
14እስራኤልን በመካከሉ ያሳለፈ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
15ፈርዖንንና ሰራዊቱን በኤርትራ ባሕር
 ያሰጠመ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
16ሕዝቡን በምድረ በዳ የመራ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
17ታላላቅ ነገሥታትን የመታ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
18ኀያላን ነገሥታትን የገደለ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
19የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን የገደለ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
20የባሳንን ንጉሥ ዐግን የገደለ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
21ምድራቸውን ርስት አድርጎ የሰጠ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
22ለባሪያው ለእስራኤል ርስት አድርጎ የሰጠ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
23በውርደታችን ጊዜ ያሰበን፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
24ከጠላቶቻችን እጅ ያዳነን፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
25ለፍጡር ሁሉ ምግብን የሚሰጥ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
26የሰማይን አምላክ አመስግኑ፤
 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።

## መዝሙር 137

### የግዞተኞች ቅኔ

1በባቢሎን ወንዞች አጠገብ፣ በዚያ
 ተቀምጠን ሳለን፣
 ጽዮን ትዝ ባለችን ጊዜ አለቀስን።
2እዚያም በአኻያ ዛፎች ላይ፣
 በገናዎቻችንን ሰቀልን።
3የማረኩን በዚያ እንድንዘምርላቸው ጠየቁን፤
 የሚያሠቃዩን የደስታ ዜማ ፈለጉብን፤
 ደግሞም፣ "ከጽዮን መዝሙሮች አንዱን
 ዘምሩልን" አሉን።
4የእግዚአብሔርን ዝማሬ፣
 እንዴት በባዕድ ምድር እንዘምር!
5ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ብረሳሽ፣
 ቀኝ እጄ ትክዳኝ።
6ሳላስታውስሽ ብቀር፣
 ኢየሩሳሌምን የደስታዬ ቍንጮ ባላደርግ፣
 ምላሴ ከትናጋዬ ጋር ትጣበቅ።
7እግዚአብሔር ሆይ፤ ኢየሩሳሌም
 በወደቀችበት ቀን፣
 ኤዶማውያን እንዴት እንደ ዛቱ ዐስብ፤

136፥3 ዘዳ10፥17፤ መዝ105፥1፤1ጢሞ 6፥15
136፥4 ዘፀ3፥20፤ ኢዮ9፥10
136፥5 ዘፍ1፥1፤ ምሳ3፥19፤ኤር51፥15
136፥6 ዘፍ1፥1:6፤ ኢሳ42፥5፤ኤር10፥12 ፤33፥2
136፥7 ዘፍ1፥14:16፤ መዝ74፥16፤ያዕ1፥17
136፥8 ዘፍ1፥16
136፥10 ዘፀ4፥23፤ 12፥12
136፥11 ዘፀ6፥6፤ 13፥3፤105፥43
136፥12 ዘፀ3፥20፤ ዘዳ5፥15፤9፥29
136፥13 መዝ78፥13
136፥14 ዘፀ14፥22፤ መዝ106፥9
136፥15 ዘፀ14፥27
136፥16 ዘፀ13፥18፤ መዝ78፥52
136፥17 ዘኍ21፥23-25፤ኢያ24፥8-11፤ መዝ78፥55፤135፥9-12
136፥18 ዘዳ29፥7፤ ኢያ12፥7-24
136፥19 ዘኍ21፥21-25
136፥20 ዘኍ21፥33-35
136፥21 ዘዳ1፥38፤ ኢያ12፥1፤14፥1
136፥22 ዘዳ29፥8፤ መዝ78፥55፤ኢሳ 20፥3፤41፥8፤42፥19፤ 43፥10፤44፥1:21፤ 45፥4፤49፥5-7
136፥23 መዝ78፥39 ፤103፥14፤115፥12
136፥24 ዘዳ6፥19፤ ኢያ10፥14፤ነህ9፥28
136፥25 ዘፍ1፥30፤ ማቴ6፥26
136፥26 ዕዝ3፥11፤ መዝ105፥1፤115፥3
137፥1 ነህ1፥4፤ ኢሳ3፥26፤ሰቆ1፥4፤ ሕዝ 1፥1:3፤3፥15፤ 10፥15
137፥2 ዘሌ23፥40፤ ኢዮ30፥31፤ኢሳ24፥8፤ሕዝ26፥13፤አሞ6፥5 137፥3 ኢዮ30፥9፤መዝ 79፥1-4፤80፥6፤ሰቆ1፥5፤ሕዝ16፥57፤22፥4፤34፥29 137፥4 ነህ12፥46 137፥5 ኢሳ2፥3፤56፥7፤65፥11፤66፥20 137፥6 ዘዳ4፥29፤ነህ2፥3 ፤መዝ22፥15፤ኤር51፥50፤ሕዝ6፥9 137፥7 ዘፍ25፥30፤2ነገ25፥1-10፤2ዜና28፥17፤መዝ74፥8፤83፥6፤ሰቆ4፥21-22፤አብ1፥11

[ሀ]13 ዕብራይስጡ ያሙሱፍ የሚለው በቍ15 ከሚገኘው ጥምር የሸምበቆ ባሕር ይለዋል።

136፥5 *በብልኀት፤* ምሳሌ3፥19፤ ኤር10፥12 ይመ።
136፥6 *በውሃ ላይ፤* 24፥2 እና ማብ ይመ።
*136፥7-9፤* ከዘፍ1፥16 ላይ በቀጥታ የተወሰደ ክፍል ነው።
*136፥23-24፤* ምናልባት ቀደም ባሉት ቍጥሮች ላይ የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ማዳን ጠቅለል አድርጎ የሚያቀርብ ወይም ደግሞ በመሳፍንትና በዳዊት ዘመነ መንግሥት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን ማዳን የሚያወሳ ክፍል ነው።
136፥26 *የሰማይን አምላክ፤* የፋርስ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሰጡት መጠሪያ (የዳን2፥18 ማብ ይመ) በዕዝራ፣ በነህምያና በዳንኤል መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶአል። የሰማያት አምላክ የሚለው ስመ መለኮት በቍ2-3 ላይ በሌላ መንገድ ተገልጿል።
*መዝ137፤* በቅርቡ ከባቢሎን የተመለሰና በባዕድ አገር ሳለ በሕይወቱ ላይ የደረሰውን አሠቃቂ መከራና ግፍ ሲያስታውስ ቅፍፍ የሚለው አንድ በሐዘን የተመታ ሰው የዘመረው መዝሙር ነው። በመዝ42-43፤ 46፤ 48፤ 84፥ 122፤ 126 ላይ ስለ ጽዮን የተጠቀሰው ጥልቅ ፍቅር በዚህም ክፍል ተጠቅሶአል። በዕብራይስጡ ቅጅ ላይ አሥራ ሁለት መስመር ያለው ይህ መዝሙር እኩሉል በሆነና እያንዳንዳቸው አራት መስመር ባላቸው ሦስት አንጓዎች ተከፍሎአል፤ ቍ1-3 ሐዘንና መከራ፣ ቍ4-6 ለኢየሩሳሌም የተገባውን ቃል ቍ7-9 ደግሞ ኤዶምና ባቢሎን የእጃቸውን እንዲያገኙ የቀረበውን ጸሎት የሚያስታውሱ ናቸው።
137፥1 *ወንዞች፤* የጤግሮስና የኤፍራጥስ ወንዞች እንዲሁም ከእነርሱ ጋር የተያያዙ በርካታ ቦዮችን ያመለክታል። *ተቀምጠን፤* ከጽዮን መለየታቸውን ሲያስቡትና በባዕድም አገር መሆናቸውን ሲያስተውሉት ሐዘን አደቀቃቸው (ኢዮ2፥8:13፤ ሰቆ 2፥10 ይመ)።
137፥2 *በገናዎቻችንን ሰቀልን፤* "ደስተኛው በገና ዝም አለ" (ኢሳ24፥8)፤ ምክንያቱም ጨካኞቹ ባቢሎናውያን በሩቅ ባለችው በጽዮን መዝሙር ለመዝናናት ቢፈልጉም የምርኮኞቹ የሙዚቃ መሣሪያዎች ግን "የሐዘን መዝሙር ለመዘመር ተቃኝተዋል" (ኢዮ30፥31)።
*137፥4-6፤* ጌታንና ቅድስቲቷን ከተማ ኢየሩሳሌምን በልባቸው የካዱ ብቻ ናቸው፤ በባቢሎናውያን መድረክ ላይ የሚያዜሙት እኔ ግን ለዚያች ውድ ከተማ ታማኝ ሆኜ ባልገኝ ከዚህ በኋላ በገናም አልጫወት፣ መዝሙርም አልዘምር! የሚል ነበር።
*137፥7-9፤* ኢየሩሳሌም በባዕዳን መንግሥታት የፍርስራሽ ክምር በሆነች ጊዜ ኤዶማውያንና ባቢሎናውያን ያስተጋቡትን የደስታ ጩኸት እግዚአብሔር እንዲበቀል አንድ የከተማዋ ነዋሪ ልጅ ያቀረበው ጥሪ ነው (የ5፥10 ማብ ይመ)።
137፥7 *ኤዶማውያን፤* የያዕቆብ ወንድም የሆነው የዔሳው

ደግሞም፣ "አፍርሷት፤
ፈጽማችሁ አፈራርሷት!" አሉ።
8አንቺ አጥፊ የሆንሽ የባቢሎን ልጅ ሆይ፤
በእኛ ላይ ስለ ፈጸምሺው ድርጊት፣
የእጅሽን የሚሰጥሽ የተመሰገነ ነው፤
9ሕፃናትሽንም ይዞ፣
በዐለት ላይ የሚፈጠፍጥ የተመሰገነ
ነው።

## መዝሙር 138

### የምስጋና መዝሙር

የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ በፍጹም ልቤ
አመሰግንሃለሁ፤
በአማልክት ፊት በመዝሙር
እወድስሃለሁ።
2ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ፤
ስለ ምሕረትህና ስለ ታማኝነትህ፣
ለስምህ ምስጋና አቀርባለሁ፤
ስምህንና ቃልህን፣
ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አድርገሃልና።
3በጠራሁህ ቀን መልስ ሰጠኸኝ፤
ነፍሴን በማደፋፈርም ብርቱ አደረግኸኝ።
4እግዚአብሔር ሆይ፤ የአፍህን ቃል በሰሙ
ጊዜ፣
የምድር ነገሥታት ሁሉ ያመስግኑህ።
5የእግዚአብሔር ክብር ታላቅ ነውና፣
ስለ እግዚአብሔር መንገድ ይዘምሩ።
6እግዚአብሔር በከፍታ ስፍራ ቢሆንም፣
ዝቅ ያለውን ይመለከተዋል፤
ትዕቢተኛውን ከሩቅ ያውቀዋል።
7በመከራ መካከል ብሄድም፣
አንተ ሕይወቴን ትጠብቃታለህ፤
በጠላቶቼ ቍጣ ላይ እጅህን ትዘረጋለህ፤
በቀኝ እጅህም ታድነኛለህ።
8እግዚአብሔር በእኔ ላይ ያለውን ዐላማ
ይፈጽማል፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህ ለዘላለም
ነው።
የእጅህንም ሥራ ቸል አትበል።

## መዝሙር 139

### ሁሉን ዐዋቂ አምላክ

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ መረመርኸኝ፤
ደግሞም ዐወቅኸኝ።
2አንተ መቀመጤንና መነሣቴን ታውቃለህ፤
የልቤንም ሐሳብ ገና ከሩቁ

137፥8 ኢሳ13፥1፡19፤47፥1-15፤ኤር25፥12፡26፤50፥1፡2-51፡58
137፥9 2ነገ8፥12፤ ኢሳ13፥16፤ሉቃ 19፥44
138፥1 መዝ27፥6፤95፥3፤96፥4፤108፥1
138፥2 1ነገ8፥29፤ መዝ5፥7፤74፥21፤97፥12፤108፥4፤115፥1፤119፥9፤140፥13
138፥3 መዝ18፥6፤28፥7፤30፥2፤99፥6፤116፥4፤118፥5፤ምሳ 28፥1፤ሐሥ4፥29
138፥4 መዝ72፥11፤102፥15
138፥5 መዝ21፥5፤51፥14፤71፥16፤145፥7
138፥6 መዝ40፥4፤113፥6፤ማቴ23፥12
138፥7 ዘፀ7፥5፤ መዝ7፥6፡17፥7፡14፤20፥6፤23፥4፤41፥2፤60፥5፤108፥6
138፥8 ዕዝ3፥11፤ኢዮ 10፥3፡8፤መዝ51፥11፤100፥5፤ፊል1፥6
139፥1 መዝ17፥3፤44፥21፤ሮሜ8፥27
139፥2 2ነገ19፥27፤

ዘሮች የተጠሩበት ስም ሲሆን ኢየሩሳሌም በታላቅ ጥፋት ውስጥ ወድቃ ሳለ በውድቀቷ ደስ የተሰኙ ሕዝቦች ናቸው፤ ኤዶማውያን የእስራኤል የዘመናት ጠላቶች ናቸው። የመዝሙሩ ደራሲ ነቢያት በኤዶም ላይ የተነገረውን የፍርድ ቃል ኢሳ63፥1-4፤ ኤር 49፥7-22፤ ሕዝ25፥8፡12-14፤ 35፤ ትንቢተ አብድዩ ይመ) በትክክል ስለ ማወቁ ምንም አያጠራጥርም። *አፍርሷት፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ተርትሯት" ማለት ነው፤ ከተሞችን በአንስታይ ጾታ መጥራት በጥንቱ ዓለም የተለመደ ነው። በኢየሩሳሌም ላይ የደረሰው ጥፋት በኤዶምም ላይ እንደሚደርስ በሰቆ4፥21 ላይ ተገልጿል።

137፥8 *ልጅ፤* ባቢሎንና የባቢሎን ነዋሪዎች የተጠሩበት ሰውኛ አገላለጽ ነው። *የእጅሽን የሚሰጥሽ፤* በዚህች ጨካኝ አጥፊ መንግሥት ላይ እግዚአብሔር የተናገረውን ፍርድ ደራሲው የሚያውቅ ይመስላል (ኢሳ13፤ 21፥1-10፤ 47፤ ኤር50-51፤ዕን2፥4-20 ይመ)።

137፥9 *ሕፃናትሽንም፤* እንደ አሁኑ ዘመን ሁሉ ያኔም ጦርነት አስከፊ ነገር ነው፤ ሕፃናትና ሴቶች የጦርነት ሰለባ ከመሆን አያመልጡም (2ነገ8፥12፤ 15፥16፤ ኢሳ13፥16፡18፤ ሆሴ10፥14፤ 13፥16፤ አሞ1፥13፤ ናሆም3፥10 ይመ)። የእግዚአብሔር ከተማ ተቃዋሚ የሆነችው "ባቢሎን" አንድ ቀን እንደምትደመሰስ የተነገረውን ትንቢት በራእ18፥1-19፥4 ላይ ይመ።

*መዝ138፤* ከጨካኝ ጠላቶች እጅ እግዚአብሔር ስላዳነው ያቀረበው ውዳሴ ነው። ምንም እንኳ በይዘቱ አጭርና ቀጥተኛ ቢሆንም በብዙ መልኩ ከመዝ18 ጋር ይመሳሰላል። ሁለት ባለ አራት መስመር አንጓዎች (ቍ1-3፡6-8) የመዝሙሩን መሪ ሐሳብ ሲያጐለብቱ በመዝሙሩ እንብርት ላይ የሚገኘው ባለ ሁለት መስመር (ቍ4-5) አንጓ ደግሞ እግዚአብሔር በምድር ዙሪያ ሁሉ እንደሚመሰገን ይገልጻል።

*138ርእስ፤* ይህ መዝሙር "የዳዊት መዝሙር" በመባል ከሚታወቁት ስምንት መዝሙሮች መካከል የመጀመሪያው ነው (መዝ 138-145)። ስድስቱ መዝሙሮች የተቀነበቡት በምስጋና መዝሙር ነው።

*138፥1-3፤* እግዚአብሔር ታማኝ መሆኑን ለመዝሙረኛው ያሳየው፣ ጸሎቱን በመመለስ ነው፤ ስለዚህ መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ታማኝነት እያሰበ ምስጋናውን ያቀርባል።

138፥1 *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *አማልክት፤* ይህ ቃል የሚያመለክተው የአሕዛብ ነገሥታትን (ቍ4-5 ይመ) ወይም እነርሱ እንወክላቸዋለን የሚሏቸውን አማልክት ነው (የመዝ82 መግቢያ፤ የ82፥1 ማብ ይመ)።

138፥2 *ቅዱስ መቅደስህ፤* የዚህ መዝሙር ጸሓፊ በእርግጥ ዳዊት ከሆነ፣ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ቃል የሚያመለክተው ዳዊት ለእግዚአብሔር ታቦት ያዘጋጀውን ድንኳን ነው (2ሳሙ 6፥17)፤ ዳዊት እንደጻፋቸው የሚታመኑ ብዙ መዝሙሮች ስለ "ቤተ መቅደሱ" ይጠቅሳሉ (5፥7፤ 11፥4፤ 18፥6፤ 27፥4 እንዲሁም የመዝ30 ርእስ ይመ)። *ስምህንና፤* የ5፥11 ማብ ይመ። *ምሕረትህና ... ታማኝነትህ፤* የ36፥5 ማብ ይመ። *ምሕረትህና፤* ቍ8 ይመ፤ የ6፥4 ማብ ይመ። *ቃልህን፤* በተለይ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ነው። እግዚአብሔር የመዝሙረኛውን ጸሎት በመመለስ ፍቅሩንና ታማኝነቱን ስላሳየ (ቍ3 ይመ) ስሙና የተስፋ ቃሉ ይበልጥ ሊወደድ ችሎአል።

*138፥4-5፤* የመዝሙሩ እንብርት ነው (የ6፥6 ማብ ይመ)። የምድር ነገሥታት ሁሉ ከእርሱ ጋር ሆነው እግዚአብሔር እንዲያመስግኑ ይመኛል (የ9፥1 ማብ ይመ)።

138፥4 *የአፍህን ቃል፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ታላቅ ታማኝነት ይገልጻል።

138፥5 *ስለ እግዚአብሔር መንገድ፤* 25፥10 እና ማብ ይመ። የእግዚአብሔር ቃልና መንገድ እርስ በርስ የተያያዙ በመሆናቸው በአንድነት ክብሩን ይገልጻሉ (መዝ145 ይመ)።

*138፥6-8፤* መዝሙረኛው እግዚአብሔር ራሱን እንዴት ዝቅ እንዳደረገ፣ ታማኝነቱና ፍቅሩም እንዴት እንደ ሆነ ከገለጸ በኋላ በጸሎት ይጨርሳል።

*138፥6፤* 113፥4-9 እና ማብ ይመ። *ይመለከተዋል፤* ያስበዋል ማለት ነው። *ትዕቢተኛውን፤* የ31፥23፤ 101፥5፤ 131፥1 ማብ ይመ። *ከሩቅ ያውቀዋል፤* እግዚአብሔር የትዕቢተኞችን ልብ ከሩቅ ስለሚያይ "ፊቱን እንኳ እንዲያዩ" አይፈቅድላቸውም (የ11፥7 ማብ ይመ)።

138፥8 *በእኔ ላይ ያለውን ዐላማ ይፈጽማል፤* የ57፥2 ማብ ይመ። *የእጅህ ሥራ፤* ንጉሡ ራሱ የእግዚአብሔር ፍጥረት ነው።

*መዝ139፤* መዝሙረኛው እግዚአብሔር ልቡን እንዲመረምር፣ ለእርሱም ያለውን ታማኝነት እንዲፈትሽ ይጸልያል። እንደ ኢዮብ ሁሉ የዚህ መዝሙር ጸሓፊም ለእግዚአብሔር ያለውን ታማኝነት በጽኑ ይገልጻል። እግዚአብሔር ሕይወትን ብቻ ሳይሆን ነፍስንም ጭምር እንዲመረምር መጠየቅ እጅግ ታላቅ ነገር እንደ ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደዚህ ደራሲ የተረዳ ሰው (ከኢዮብ በስተቀር) የለም፤ ይህ ደራሲ እግዚአብሔር ሐሳቡን፣ ልቡንና ድርጊቱን ሁሉ እንደሚያውቅና እንዲያውም በእናቱ ማሕፀን ውስጥ ተገጣጥሞ ከመሠራቱ በፊት ሁለንተናውን እንደሚያስተውል ተረድቶአል። የመዝሙሩ ሐሳብ እያንዳንዳቸው ስድስት ስድስት ቍጥር ባላቸው አራት አንቀጾች እያደገ ሲሄድ (ቍ1-6፡7-12፡13-18፡19-24) እያንዳንዱ አንቀጽ የሚደመደመው የየአንቀጹን ዋና ሐሳብ በማስፋፋት ነው። መዝሙሩ የሚጀምረውም ሆነ የሚጨርሰው እግዚአብሔር እንዲመረምረው በመጠ

ታስተውላለህ::
3 መሄድ መተኛቴን አጥርተህ ታውቃለህ፤
መንገዶቼንም ሁሉ ተረድተሃቸዋል::
4 እግዚአብሔር ሆይ፤ ገና ቃል ከአንደበቴ
ሳይወጣ፣
እነሆ፤ አንተ ሁሉንም ታውቃለህ::
5 አንተ ከኋላም ከፊትም ዙሪያዬን
ከለልኸኝ፤
እጅህንም በላዬ አደረግህ::
6 እንዲህ ያለው ዕውቀት ለኔ ድንቅ ነው፤
ልደርስበትም የማልችል ከፍ ያለ ነው::
7 ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ?
ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?
8 ወደ ሰማይ ብወጣ፣ አንተ በዚያ አለህ፤
መኝታዬንም በሲኦል[a] ባደርግ በዚያ
ትገኛለህ::
9 በንጋት ክንፍ ተነሥቼ ብበር፣
እስከ ባሕሩ ዳርቻ መጨረሻ ብሄድ፣
10 በዚያም ቢሆን እጅህ ትመራኛለች፤
ቀኝ እጅህም አጥብቃ ትይዘኛለች::
11 እኔም፣ "ጨለማው በእርግጥ ይሰውረኛል፤
በዙሪያዬ ያለውም ብርሃን ሌሊት
ይሆናል" ብል፣
12 ጨለማ የአንተን ዐይን አይዝም፤
ሌሊቱም እንደ ቀን ያበራል፤
ጨለማም ብርሃንም ለአንተ አንድ
ናቸውና::
13 አንተ ውስጣዊ ሰውነቴን ፈጥረሃልና፤
በእናቴም ማሕፀን ውስጥ አበጃጅተህ
ሠራኸኝ::
14 ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና
አመሰግንሃለሁ፤
ሥራህ ድንቅ ነው፤
ነፍሴም ይህን በውል ተረድታለች::
15 እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፣
ዐጥንቶቼ ከአንተ አልተደበቁም፤
በምድር ጥልቀት ውስጥ በጥበብ
በተሠራሁ ጊዜ፣
16 ዐይኖችህ ገና ያልተበጀውን አካሌን
አዩ፤
ለእኔ የተወሰኑልኝም ዘመናት፣
ገና አንዳቸው ወደ መኖር ሳይመጡ፣
በመጽሐፍ ተመዘገቡ::
17 አምላክ ሆይ፤ ለእኔ ያለህ ሐሳብ እንዴት
ክቡር ነው!
ቍጥሩስ ምንኛ ብዙ ነው!
18 ልቍጠራቸው ብል፣
ከአሸዋ ይልቅ ይበዙ ነበር::
ተኛሁም ነቃሁም፣
ገና ከአንተው ጋር ነኝ::

መዝ94፥11፤ምሳ24፥12፤ኤር12፥3
139፥3 2ነገ19፥27፤ኢዮ31፥4
139፥4 ዕብ4፥13
139፥5 1ሳሙ25፥16፤መዝ32፥10፤34፥7፤125፥2
139፥6 መዝ131፥1፤ሮሜ11፥33
139፥7 ኤር23፥24፤ዮና1፥3
139፥8 ዘዳ30፥12-15፤ኢዮ17፥13፤አሞ9፥2-3
139፥10 መዝ23፥3፤108፥6፤ኢሳ41፥10
139፥12 ኢዮ34፥22፤ዳን2፥22
139፥13 ኢዮ10፥11፤መዝ119፥73፤ኢሳ44፥2፡24፤46፥3፤49፥5፤ኤር1፥5
139፥14 ኢዮ40፥19፤መዝ119፥164፤145፥10
139፥15 ኢዮ10፥11፤መዝ63፥9፤መክ11፥5
139፥16 ኢዮ33፥29፤መዝ90፥12
139፥17 ኢዮ5፥9፤መዝ92፥5
139፥18 ኢዮ29፥18፤መዝ3፥5፤40፥5

[a]8 አንዳንድ ትርጒሞች *በጥልቁ ውስጥ* ይላሉ::

የቅ ነው::

139ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 ርእስ ማብ ይመ:: *የዳዊት፤* የመዝ138 ርእስ ማብ ይመ::

*139፥1-6፤* መዝሙረኛው እርሱ ራሱን ከሚያውቀው በላይ እግዚአብሔር እንደሚያውቀው ይናገራል፤ እንዲህም ሲል ድርጊቴን ሁሉ (ቍ2)፣ አካሄዴን ሁሉ (ቍ3)፣ ሐሳቤን ሁሉ (ቍ3)፣ ምንም ነገር ከመናገሬ በፊት የማስበውን ሁሉ (ቍ2)፣ የምናገረውን ቃል ከመናገሬ በፊት (ቍ4) ታውቃለህ ማለቱ ነው::

139፥5 *ከለልኸኝ፤* ከከፉ ጠበቅኸኝ ማለት ነው:: *እጅህንም በላዬ አደረግህ፤* እንዳላመልጥህ ማለት ነው:: ሐሳቡም ከኢዮ 13፥27 ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም ምሳሌአዊ አነጋገሩ ግን ይለያል::

139፥6 *ለእኔ ድንቅ ነው፤* የአንተ እውቀት ከአእምሮዬ በላይ ነው፤ ልገምተውም ሆነ ልለካው ከቶ አልችልም ማለት ነው፤ የዕብራይስጡ ቃል አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ ያመለክታል (77፥11፡14 "ታምራት"፤ ዘፀ15፥11 ይመ)::

*139፥7-12፤* ከእግዚአብሔር ፊት መሰወሪያ ምንም ስፍራ እንደሌለ የሚናገር ክፍል ነው፤ ይህ ክፍል የሚናገረው እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የሚገኝ ስለ መሆኑ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ሸሽቶ መሰወር የማይችል ስለመሆኑ ነው (ኤር23፥23-24 ይመ)::

139፥7 *ከመንፈስህ ... ከፊትህስ፤* 51፥11፤ ኢሳ63፥9-10፤ ሕዝ 39፥29 ይመ::

139፥8 *ሰማይ ... በሲኦል፤* ሁለት ተቃራኒ ጫፎች ናቸው::

139፥9 *በንጋት ክንፍ ... ባሕሩ ዳርቻ፤* ባሕሩ ሜድትራኒያን ባሕር ነው፤ ሁለቱ ተቃራኒ ጫፎች ደግሞ ምሥራቅና ምዕራብ ናቸው:: የነገሩን ስፋትና ርዝመት የሚያሳይ ምሳሌያዊ አገላለጽ ነው፤ ቍ8-9 መሰወሪያ ሊሆኑ የሚችሉ ቦታዎችን ሁሉ ይጠቅሳል::

139፥10 *ትመራኛለች... አጥብቃ ትይዘኛለች፤* ምንም እንኳ ይህ ሐረግ በ73፥23-24 ላይ የእግዚአብሔርን ልዩ ክብካቤ ለመግለጽ ቢገባም፣ እዚህ ላይ ግን የሚያመለክተው ከቶ ልናመልጠው የማንችለውን የእግዚአብሔርን ቍጥጥር ነው፤ ሐሳቡ ከቍ5 የተለየ ነው::

*139፥11-12፤* ፍጥረት ሁሉ ሊሰውረን እንደማይችል ሁሉ (ቍ8-9) ጨለማም ሊሰውረን አይችልም::

*139፥13-16፤* ከመወለዴ አስቀድሞ በእናቴ ማሕፀን ውስጥ የገጣጠምኸኝ አንተ ራስህ ነህ፤ የሕይወቴንም ዘመን የምትወስን አንተ ነህ::

139፥13 *ፈጥረሃልና፤* ይህን ቃል/ግስ ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል በዘፍ1፥1:21:27 ላይ ከተጠቀሰው ጋር ሳይሆን በዘፍ 14፥19:22፤ ምሳ 8፥22 ላይ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ነው:: *ውስጣዊ ሰውነቴን፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ኵላሊቴን" ማለት ሲሆን በዕብራይስጥ ምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ ይህ ቃል የሚያመለክተው ውስጣዊ ስሜትንና ምግባራዊ አስተሳሰብን ነው፤ እግዚአብሔር ሰዎችን ሲፈትንና ሲመረምር የሚያመለክተው ይህንን ነው (የ7፥9 ማብ ይመ)::

139፥14 *ግሩምና ድንቅ ... ድንቅ፤* የፈጠርኸኝ አንተ ስለሆንህ በሚገባ ታውቀኛለህ (ቍ15-16 ይመ)፤ እኔ ግን አንተ የፈጠርኸውን ሰው በመገረምና በመደነቅ ከመመልከት በስተቀር ከቶ ሳስተውለው አልችልም (የቍ6 ማብ ይመ)፤ ስለዚህ አመሰግንሃለሁ ማለቱ ነው (መክ11፥5 ይመ)::

139፥15 *በስውር ... በምድር ጥልቀት፤* እንዲህ የሚለውን የእናቱን ማሕፀን ነው፤ በዚህ ቍጥር ላይ ማሕፀን "ስውር" ስፍራ የተባለው በእርግጥም ከዕይታ ስለሚሰውርና (2ሳሙ12፥12 ይመ) "ከምድር ጥልቅ" ጋር ስለሚመሳሰል ነው (የ30፥1 ማብ ይመ)፤ ማሕፀን ከጨለማ፣ ከርጥበትና ከዕይታ ከተሰወረ ነገር ጋር ተወራራሽ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሙታንን መኖሪያ ያመለክታሉ (63፥9፤ ኢዮ14፥13፤ ኢሳ44፥23፤ 45፥19)፤ ይኸውም በአንድ በኩል ማሕፀን ከሙታን መኖሪያ ጋር የተመሳሰለው፣ ሰው የተፈጠረው ከዐፈር በመሆኑና የሚመለሰውም ወደ ዐፈር በመሆኑ ነው (90፥3፤ ዘፍ3፥19፤ መክ3፥20፤ 12፥7)፤ በሌላ በኩል ደግሞ ማሕፀን ሰው የተሠራበት ስፍራ በመሆኑ እንደ "ጥልቍ ምድር" ነው (ኢሳ44፥2:24፤ 49፥5፤ ኤር1፥5 ይመ)::

139፥16 *የተወሰኑልኝም ዘመናት፤* የሰው የሕይወት ዘመን በእግዚአብሔር የተወሰነ ነው:: *በመጽሐፍ፤* የእግዚአብሔር ውሳኔዎች ሁሉ የተጻፉበት የሰማይ መዝገብ ነው (የ56፥8 ማብ ይመ)::

139፥17 *ለእኔ ያለህ ሐሳብ፤* ለእርሱ ያለውን ሐሳብ በተግባር ያሳየ ሲሆን፣ ይህም "ሐሳቤን" (ቍ2) ከሚለው ጋር ይነጻጸራል::

139፥18 *ተኛሁም ነቃሁም፤* የድካም እንቅልፍ ሰዎች የእግዚአብሔርን ውለታ እንዳይቈጥሩና ሥራውንም እንዳያስተውሉ ያደርጋል (63፥6፤ 119፥148 ይመ)፤ መንቃት ግን ነፍሳችን በእግዚአብሔር መገኘት ሐሴት እንድታደርግ ያስችላል::

*139፥19-22፤* ለእናንተ ያለኝ ቅንአት ከጠላቶችህ እንድለይ ያደርገኛል ማለቱ ነው::

[19]እምላክ ሆይ፣ ክፉዎችን ብትገድላቸው
ምናለበት!
ደም የተጠማችሁ ሰዎች ሆይ፤ ከእኔ ራቁ!
[20]ስለ አንተ በክፋት ይናገራሉና፤
ጠላቶችህም ስምህን በከንቱ ያነሣሉ።
[21]እግዚአብሔር ሆይ፤ የሚጠሉህን
አልጠላምን?
በአንተ ላይ የሚነሡትንስ አልጸየፍምን?
[22]በፍጹም ጥላቻ ጠልቻቸዋለሁ፤
ባላጋራዎቼም ሆነዋል።
[23]እግዚአብሔር ሆይ፤ መርምረኝ፤ ልቤንም
ዕወቅ፤
ፈትነኝ፤ ሐሳቤንም ዕወቅ፤
[24]የክፋት መንገድ በውስጤ ቢኖር እይ፤
በዘላለምም መንገድ ምራኝ።

## መዝሙር 140

### በክፉዎች ላይ የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ ከክፉ ሰዎች አድነኝ፤
ከዐመፀኞችም ሰዎች ጠብቀኝ፤
[2]እነርሱ በልባቸው ክፉ ነገር ያውጠነጥናሉ፤
በየዕለቱም ጦርነት ይጭራሉ።
[3]ምላሳቸውን እንደ እባብ ያሾላሉ፤
ከከንፈራቸውም በታች የእፉኝት
መርዝ አለ። ሴላ
[4]እግዚአብሔር ሆይ፤ ከክፉዎች እጅ
ጠብቀኝ፤
እግሮቼንም ለመጥለፍ ከሚያደቡ
ዐመፀኞች ሰውረኝ።
[5]ትዕቢተኞች ወጥመድ በስውር አስቀመጡብኝ፤
የመረባቸውን ገመድ ዘረጉብኝ፤
በመንገዴም ላይ አሽክላ አኖሩ። ሴላ
[6]እግዚአብሔር ሆይ፤ "አንተ አምላኬ ነህ"
እልሃለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ የልመና ጩኸቴን
ስማ።
[7]ብርቱ አዳኝ የሆንህ፣ ጌታ እግዚአብሔር
ሆይ፤
በጦርነት ዕለት የራስ ቍር ሆንኸኝ።
[8]እግዚአብሔር ሆይ፤ የክፉዎች ምኞት
አይፈጸም፤
በትዕቢትም እንዳይኵራሩ፣
ዕቅዳቸው አይሳካ። ሴላ
[9]ዙሪያዬን የከበቡኝ ሰዎች ራስ፣
የከንፈራቸው መዘዝ ይጠምጠምበት።
[10]የእሳት ፍም በላያቸው ይውረድ፤
ዳግመኛም እንዳይነሡ ወደ እሳት ይጣሉ፤
ማጥ ወዳለበት ጕድጓድ ይውደቁ።
[11]ምላሰኛ በምድሪቱ ጸንቶ አይኑር፤
ዐመፀኛውን ሰው ክፉት አሳዶ ያጥፋው።
[12]እግዚአብሔር ለድኻ ፍትሕን
እንደሚያስከብር፣
ለችግረኛውም ትክክለኛ ፍርድን
እንደሚሰጥ ዐውቃለሁ።
[13]ጻድቃን በእውነት ስምህን ያመሰግናሉ፤
ቅኖችም በፊትህ ይኖራሉ።

## መዝሙር 141

### የክፉዎችን ድሎት ለመመኘት የቀረበ ጸሎት

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ እጣራለሁ፤
ፈጥነህ ድረስልኝ፤

139፥19 መዝ5፥6፤ 6፥8፤59፥2፤ኢሳ11፥4
139፥20 ዘጸ5፥11፤ መዝ65፥7
139፥21 2ዜና19፥2 ፤መዝ26፥5፤31፥6፤ 119፥113
139፥22 ማቴ5፥43
139፥23፤ሳሙ16፥7 ፤1ዜና29፥17፤ኢዮ 31፥6፤መዝ7፥9፤ምሳ 17፥3፤ኤር11፥20፤ ራእ2፥23
139፥24 መዝ5፥8፤ 23፥2፤143፥10፤ኤር 25፥5፤36፥3
140፥1 ቍ11፤መዝ 17፥13፤25፥20፤59፥2 ፤71፥4፤86፥14፤142፥ 6፤143፥9
140፥2 መዝ36፥4፤ 52፥2፤68፥30፤ምሳ 6፥14፤16፥27፤ኢሳ 59፥4፤ሆሴ7፥15
140፥3 መዝ57፥4፤ 58፥4፤ሮሜ3፥13፤ ያዕ3፥8
140፥4 መዝ36፥ 11፤141፥9
140፥5 ኢዮ18፥8፡ 9፤34፥30፤መዝ31፥4፤ 38፥12፤119፥110
140፥6 መዝ16፥2፤ 28፥2፡6
140፥7 መዝ68፥20
140፥8 መዝ10፥2- 3፤66፥7
140፥9 ምሳ18፥7
140፥10 መዝ11፥6 ፤21፥9፤ማቴ3፥10፤ ሉቃ12፥49፤ራእ 20፥15
140፥11 መዝ34፥21
140፥12 1ነገ8፥45፤ መዝ35፥10፤82፥3
140፥13 መዝ11፥7 ፤16፥11፤138፥2
141፥1 መዝ4፥1፤ 5፥1-2፤22፥19፤27፥7፤143፥1

139፥19 *ብትገድላቸው፤* እግዚአብሔር ክፉዎችን እንደ ምን እንደታገሣቸው የተመለከተ ሰው በቅናት የተናገረው ንግግር ነው፤ አንድ ቀን ተጠራርገው እንደሚጠፉ የታወቀ ነው (ኢሳ 11፥4)። መዝሙረኛው ግን ሁሉን ለጌታ ይተዋል።

139፥20 *ስምህን በከንቱ ያነሣሉ፤* ምናልባት ታማኝ የእግዚአብሔር አገልጋይ ለመሆን በሚጥሩት ላይ ርግማን እንዲወርድ ስለ ለመኑ ይሆናል።

*139፥21-22፤* በጥንት መካከለኛው ምሥራቅ ይኖሩ የነበሩ ነገሥታት ከእነርሱ በታች ሆነው ከሚያስተዳድሩ አገረ ገዦች ጋር የሚገቡት ውል ነው (በ14ኛው ዓ.ቅ.ክ ላይ በሒታውያን ንጉሥ በዳግማዊ ሙርሲሊስና በቴቴ ዘኑሐሲ መካከል የተደረገው ውል ከዚህ የሚከተለውን ይመስላል፣ "ከወዳጄ ጋር ከወገንህ ወዳጄ ነህ፤ ከጠላቴ ጋር ከወገንህ ጠላቴ ነህ")።

139፥23-24 *መርምረኝ፤* ለአንተም ያለኝን ታማኝነት እይ፤ በእውነትም ምራኝ ማለቱ ነው (17፥3-5 እና ማብ ይመ)።

139፥23 *ልቤንም፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ሐሳቤንም ዕወቅ፤* 94፥19 ይመ። በእግዚአብሔር መመርመር ቀላል ነገር አይደለም።

139፥24 *በዘላለምም መንገድ፤* የ16፥9-11 ማብ ይመ።

*መዝ140፤* ከጨካኝ ጠላቶች ሤራ እግዚአብሔር እንዲታደገው ያቀረበው ጸሎት ነው። በመዝ58 እና 64 ላይ የተወሡ ነገሮችን የሚያስተጋባ መዝሙር ቢሆንም፣ በመዝሙሩ ውስጥ የተጠቀሱት በርካታ ቃላት በብሉይ ኪዳን የትም ስፍራ አይገኙም። መዝሙሩ እኩል መጠን ያላቸው አራት አንጓዎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ አንጓ የተደመደመው ሁለት ቍጥሮች ባሉት ስንኝ ነው። በመዝሙሩ ውስጥ ብዙ የአካል ክፍሎች ተጠቅሰዋል፤ እነርሱም ልብ፣ ራስ፣ ምላስ፣ ከንፈር፣ እጅ፣ እግር፣ ጆሮ እና ጥርስ ናቸው። መዝ141 ይመ።

140 ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 ርእስ ማብ ይመ። *የዳዊት፤* የመዝ138 ርእስ ማብ ይመ።

*140፥1-3፤* ከእነዚያ እፉኝቶች ታደገኝ ማለቱ ነው።

140፥2 *በልባቸው፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

140፥3 *ምላሳቸውን፤* የ5፥9 ማብ ይመ። *የእፉኝት መርዝ፤* 58፥4 እና ማብ ይመ።

*140፥4-5፤* ከትዕቢተኞችና ከዐመፀኞች ጠብቀኝ (10፥2-11 እና ማብ ይመ)።

140፥5 *ትዕቢተኞች፤* የ31፥23 ማብ ይመ።

*140፥6-8፤* ክፉዎች በእኔ ላይ ያሴሩትን ክፉ ሐሳብ አታሳካላቸው።

*140፥9-11፤* በእኔ ላይ ያሴሩት ክፉ ሐሳብ ሁሉ እነርሱን መልሶ ይያዛቸው (የ5፥10 ማብ ይመ)።

140፥10 *የእሳት ፍም፤* የ11፥6 ማብ ይመ። *እሳት ... ማጥ፤* እዚህ ላይ የተወሱትን ቃላት በኢዮ15፥30፤ 20፥26 ላይ ከተወሡት እሳትና ጨለማ ጋር በአንድነት ስናያቸው የእግዚአብሔር የፍርድ እሳት (21፥9፤ 97፥3፤ ኢሳ1፥31፤ 26፥11፤ 33፥14 ይመ)፣ የሙታንን መኖሪያ እንኳ ሊያጠፋ እንደሚችል ይጠቍማል (ኢዮ31፥12፤ የመዝ30፥1 ማብ ይመ)። *ዳግመኛ እንዳይነሡ፤* 36፥12፤ ኢሳ26፥14 ይመ።

140፥11 *አሳዶ፤* እኔን ሊያጠምዱ (ቍ4-5) የነበሩ ሁሉ እነርሱ ባጠመዱት ወጥመድ ይያዙ።

*140፥12-13፤* በእግዚአብሔር ቅን ፍርድ እንደሚተማመን የገለጸበት ክፍል ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)።

140፥12 *ለድኻ ... ለችግረኛውም፤* የ9፥18፤34፥6 ማብ ይመ።

140፥13 *ጻድቃን፤* የ1፥5 ማብ ይመ። *ያመሰግናሉ፤* የእግዚአብሔርን ቸርነት ስላዩ ያመሰግኑታል ማለት ነው (የ7፥17፤ 9፥1 ማብ ይመ)። *በፊትህ ይኖራሉ፤* ክፉዎች ግን ተጠራርገው ይጠፋሉ (ቍ10፤ የ11፥7፤ 16፥9-11 ማብ ይመ)።

*መዝ141፤* ከክፉዎችና ከክፉ ሤራቸው እግዚአብሔር እንዲታደገው ያቀረበው ጸሎት ነው። መዝሙሩ ሁለት አንጓዎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው አንጓ ሐሳብ በሁለተኛው አንጓ ላይ ተደግሞአል። በመዝሙሩ ዕንብርት ላይ የሚገኘው ባለ ሁለት

ወደ አንተ ስጣራም ድምፄን ስማ::
[2]ጸሎቴ በፊትህ እንደ ዕጣን ትቈጠርልኝ፤
እጄን ማንሣቴም እንደ ሠርክ መሥዋዕት
ትሁን::

[3]እግዚአብሔር ሆይ፤ ለአፌ ጠባቂ አድርግ፤
የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ::
[4]ከዐመፀኞች ጋር፣
በክፉ ሥራ እንዳልተባበር፣
ልቤን ወደ ክፉ አታዘንብል፤
ከድግሳቸውም አልቋደስ::

[5]ጻድቅ[*] ሰው ይቅጣኝ፤ ይህ በጎነት ነው፤
ይገሥጸኝም፤ በራሴ ላይ እንደሚፈስ
ዘይት ነው፤
ራሴም ይህን እንቢ አይልም::

ጸሎቴ ግን በክፉዎች ተግባር ላይ ነው፤
[6]ሹማምታቸው ከገደል አፋፍ ቍልቍል
ይወረወራሉ፣
ቃሌ የምታረካ ናትና፣ ይሰሟታል::
[7]ደግሞም፣ "ሰው ምድርን እንደሚያርስና
ዐፈሩን እንደሚፈረካክስ፣
እንዲሁ ዐጥንታችን በሲኦል[+] አፋፍ
ላይ ተበታተነ" ይላሉ::

[8]ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ ዐይኖቼ ግን ወደ
አንተ ይመለከታሉ፤
መጠጊያዬም አንተ ነህ፤ እንግዲህ
ነፍሴን አትተዋት::
[9]ከዘረጉብኝ ወጥመድ፣
ከክፉ አድራጊዎችም አሽክላ ጠብቀኝ::
[10]እኔ ብቻ በደህና ሳመልጥ፣
ክፉዎቹ በገዛ ወጥመዳቸው ይውደቁ::

141፥2 ዘፀ29፥39-41፤30፥8፤መዝ28፥2፤63፥4፤ሉቃ1፥9፤1ጢሞ2፥8፤ራእ5፥8፤8፥3
141፥3 መዝ12፥2፤34፥13፤ያዕ1፥26፤3፥8
141፥4 ኢሳ24፥23፤መዝ106፥29፤ምሳ23፥1-3
141፥5 ዘፀ29፥7፤መዝ23፥5፤ምሳ9፥8፤19፥25፤25፥12፤መክ7፥5
141፥6 2ዜና25፥12
141፥7 ዘኍ16፥30-32-33፤መዝ129፥3
141፥8 መዝ2፥12፤11፥1፤123፥2
141፥9 መዝ38፥12፤64፥5፤140፥4
141፥10 መዝ7፥15፤35፥8፤57፥6፤124፥7
142 ርእስ 1ሳሙ22፥1፤24፥3፤መዝ57 ርእስ
142፥1 1ነገ8፥52፤መዝ3፥4፤30፥8
142፥2 መዝ50፥15፤64፥1
142፥3 መዝ6፥2፤77፥3፤84፥2፤88፥4፤143፥4:7፤ኤር8፥18፤ሰቆ1፥22
142፥4 ኤር25፥35፤30፥17
142፥5 ዘዳ32፥9፤ኢዮ28፥13፤መዝ16፥5፤27፥13፤46፥1
142፥6 መዝ17፥1፤25፥20፤79፥8፤ኤር31፥11
142፥7 2ዜና6፥41፤መዝ7፥17፤9፥2፤66፥11

## መዝሙር 142
### የሚታደን ሰው ጸሎት

ዋሻ ውስጥ በነበረ ጊዜ፤ የዳዊት ትምህርት፤[°] ጸሎት

[1]ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ እግዚአብሔር
እጮኻለሁ፤
ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ እግዚአብሔር
ልመና አቀርባለሁ::
[2]ብሶቴን በፊቱ አፈስሳለሁ፤
ችግሬንም በፊቱ እናገራለሁ::

[3]መንፈሴ በውስጤ ሲዝል፣
መንገዴን የምታውቅ አንተ ነህ፤
በመተላለፊያ መንገዴ ላይ፤
ወጥመድ በስውር ዘርግተውብኛል::
[4]ወደ ቀኜ ተመልከት፤ እይም፤
ስለ እኔ የሚገደው የለም፤
ማምለጫም የለኝም፤
ስለ ነፍሴም ደንታ ያለው የለም::

[5]እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ እጮኻለሁ፤
ደግሞም፣ "አንተ መጠጊያዬ ነህ፤
በሕያዋንም ምድር ዕድል ፈንታዬ ነህ"
እላለሁ::
[6]እጅግ ተስፋ ቈርጫለሁና፣
ጩኸቴን ስማ፤
ከዐቅም በላይ ሆነውብኛልና፣
ከሚያሳድዱኝ አድነኝ::
[7]ስምህን አመሰግን ዘንድ፣
ነፍሴን ከወህኒ አውጣት፤

[*]5 ወይም ጻደቃ
[+]7 አንዳንድ ትርጕሞች መቃብር ይላሉ::
[°]ርእሱ ላይ ሥነ ጽሑፋዊ ወይም የዜማ ቃል ሊሆን ይችላል::

ቤት ስንኝ የመዝሙሩን ዐቢይ ሐሳብ ያጐለብታል (የቍ5 ማብ ይመ):: ይህ መዝሙር እንደ መዝ140 በርካታ የአካል ክፍሎችን ጠቅሶአል፤ እነርሱም እጅ፣ አፍ፣ ከንፈር፣ ልብ፣ ራስ፣ ዐጥንትና ዐይን ናቸው::

*141ርእስ፤* የመዝ138 ርእስ ማብ ይመ::

*141፥1-2፤* እግዚአብሔር ጸሎቱን እንዲሰማው በመግቢያ ላይ ያቀረበው ልመና ነው::

*141፥3-4፤* ክፉ ከመናገር ከመመኘትና ከማድረግ እግዚአብሔር እንዲጠብቀው ያቀረበው ጸሎት ነው::

141፥4 *ልቤን ... አታዘንብል፤* የክፉዎችን መንገድ ልቤ እንዳይፈልግ ጠብቀኝ (ምሳ1፥10-16 ይመ) ማለቱ ነው:: *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ:: *እንዳልተባበር፤* ክፉዎች አግባብ ባልሆነ መንገድ ባከማቹት ሀብት የተዘጋጀ የተትረፈረፈ ገበታ ነው፤ በእንዲህ ያለ መንገድ የሚዘጋጅ ገበታን እንዳይመኝ እግዚአብሔር ልቡን እንዲጠብቅ ያቀረበው ጸሎት ነው::

*141፥5፤* የግጥሙ ዕንብርት ነው (የ6፥6 ማብ ይመ):: *ጻድቅ ሰው ይቅጣኝ፤* የጻድቃን ቅጣትና ተግሣጽ እውነተኛ ፍቅርና ርኅራኄ የተሞላበት ነው (ምሳ27፥6፤ የ6፥4 ማብ ይመ):: *በራሴ ላይ እንደሚፈስ ዘይት፤* የ23፥5 ማብ ይመ:: *በራሴ ... ክፉዎች፤* ምናልባት "ራሴ የጻድቃንን ዘይት አልቀበም አይበል፤ ጸሎቴም ክፉ ሥራቸውን ይቃወም" ቢባል የተሻለ ይሆናል::

*141፥6-7፤* የክፉዎችን ዕድል ፈንታ የሚያመለክት ነው::

141፥6 *ቃሌ፤* በቍ3-5 ላይ እንዳመለከተው በጽድቅ ለመኖር ራሱን እንደሰጠ ያሳያሉ:: *የምትረካ ናትና፤* በግልጽና በቀጥታ ማለት ነው::

*141፥8-10፤* እግዚአብሔር ከዐመፀኞች ወጥመድ እንዲታደገው ያቀረበው ጸሎት ነው::

141፥8 *ነፍሴን አታውጣት፤* ክፉዎችን ለሞት አሳልፈህ እንደ ምትሰጥ ማለት ነው (ቍ7፤ 73፥18-20:23-26 እና ማብ ይመ)::

141፥9 *ወጥመድ ... አሽክላ፤* ጠላቶቹ እርሱን ለመጣል የሚሸርቡትን ሤራ ሊሆን ይችላል (38፥12፤ 64፥5፤ 91፥3፤ 140፥5፤ 143፥3 ይመ)፤ እዚህ ላይ ግን ዐመፀኞች በፊቱ የሚያኖሩትን ወጥመድ ያመለክታል (ዘፀ23፥33፤ ዘዳ7፥16፤ ኢያ23፥13፤ መሳ2፥3 ይመ)::

141፥10 *ክፉዎቹ ... ይወድቁ፤* የ5፥10 ማብ ይመ::

*መዝ142፤* መዝሙረኛው ደካማ፣ ብቸኛና መጠጊያ የሌለው በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ከብርቱ ጠላቶቹ እንዲያድነው ያቀረበው የምስኪን ሰው ጸሎት ነው:: ከመግቢያውና (ቍ1-2) ከመደምደሚያው (ቍ7) በስተቀር ጸሎቱ (በዕብራይስጡ ቅጅ ላይ እንደሚታየው) አራት ስንኝ ካላቸው ሁለት አንጓዎች የተዋቀረ ነው (ቍ3-7)::

142ርእስ፤ *ትምህርት፤* የመዝ32 ርእስ ማብ ይመ:: *የዳዊት፤* የመዝ138 ርእስ ማብ ይመ:: *ዋሻ ... በነበረ ጊዜ፤* የመዝ57 ርእስ ማብ ይመ:: *ጸሎት፤* የመዝ17 ርእስ ማብ ይመ::

*142፥1-2፤* የአቤቱታው መጀመሪያ ነው፤ መዝሙረኛው አቤቱታውን የሚያቀርበው በሦስተኛ መደብ ብቁ ቍጥር ነው ("እርስዎ"፤ ለነገሥታት የሚነገረው በዚህ መልክ ነው)፤ ይህም፣ "እግዚአብሔር ሆይ ወደ አንተ እጮኻለሁ" ከሚለው አነጋገር ጋር አንድ ነው::

*142፥3-4፤* ተስፋ መቍረጡን የሚገልጽ ነው (ቍ6)::

142፥3 *መንፈሴ በውስጤ ሲዝል፤* ያለበት ሁኔታ ያሸነፈው ይመስላል (22፥14-15 ይመ):: *የምታውቅ አንተ፤* የእኔ ጕዳይ ግድ ይልሃል ለማለት ነው (ከቍ4 ጋር ያነጻጽሩ)::

142፥4 *ወደ ቀኜ፤* ረዳቴና መከታዬ በሚቆምበት በቀኜ በኩል ማለት ነው (16፥8 እና ማብ ይመ):: *የሚገደው፤* በዕብራይስጡ ቃል "ማወቅ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው (ቍ3)፤ ሩት 2፥10:19 ይመ::

*142፥5-7፤* እግዚአብሔር እንዲታደገው ያቀረበው ጸሎት ነው::

142፥5 *ዕድል ፈንታዬ፤* ሕይወቴን የምታቈይና የምትጠብቅ አንተ ነህ ለማለት ነው (73፥26 እና ማብ ይመ)::

142፥7 *ከወህኒ፤* በመከራ መጠበሱን የሚገልጽ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው (የ18፥19 ማብ፤ ኢዮ36፥8 ይመ):: *አመሰግን ዘንድ፤*

ከምታደርግልኝም በጎ ነገር የተነሣ፣
ጻድቃን በዙሪያዬ ይሰበሰባሉ።

## መዝሙር 143

### ትሑት ልመና

የዳዊት መዝሙር

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
ልመናዬን አድምጥ፤
በታማኝነትህና በጽድቅህም፣
ስምተህ መልስልኝ።
2 ሰው ሆኖ በፊትህ ጻድቅ የለምና፣
ባሪያህን ወደ ፍርድ አታቅርበው።

3 ጠላት እስከ ሞት አሳዶኛል፤
ሕይወቴንም አድቅቆ ከዐፈር
ቀላቅሎአል፤
ቀደም ብለው እንደ ሞቱትም፣
በጨለማ ውስጥ አኑሮኛል።
4 ስለዚህ መንፈሴ በውስጤ ዝላለች፤
ልቤም በውስጤ ደንግጦአል።

5 የቀድሞውን ዘመን አስታወስሁ፤
ሥራህንም ሁሉ አሰላሰልሁ፤
የእጅህንም ሥራ አውጠነጠንሁ።
6 እጆቼን ወደ አንተ ዘረጋሁ፤
ነፍሴም እንደ ምድረ በዳ አንተን
ተጠማች። ሴላ

7 እግዚአብሔር ሆይ፤ ፈጥነህ መልስልኝ፤
መንፈሴ ደከመች፤
ወደ ጕድጓድ እንደሚወርዱት
እንዳልሆን፣
ፊትህን ከእኔ አትሰውር።
8 በአንተ ታምኛለሁና፣
በማለዳ ምሕረትህን አሰማኝ፤
ነፍሴን ወደ አንተ አንሥቻለሁና፣
የምሄድበትን መንገድ አሳየኝ።
9 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተን መሰወሪያ
አድርጌአለሁና፣
ከጠላቶቼ አድነኝ።
10 አንተ አምላኬ ነህና፣
ፈቃድህን እንድፈጽም አስተምረኝ፤
መልካሙ መንፈስህም፣
በቀናችው መንገድ ይምራኝ።

11 እግዚአብሔር ሆይ፤ ስለ ስምህ ሕያው
አድርገኝ፤
በጽድቅህም ነፍሴን ከመከራ አውጣት።
12 ጠላቶቼንም ለእኔ ስላለህ ምሕረት
ደምስሳቸው፤
እኔ ባሪያህ ነኝና፣
ነፍሴን የሚያስጨንቋትን ሁሉ
አጥፋቸው።

## መዝሙር 144

### የጦርነት መዝሙር

የዳዊት መዝሙር

1 እጆቼን ለጦርነት፣
ጣቶቼን ለውጊያ የሚያሠለጥን፣
እግዚአብሔር ዐለቴ ይባረክ።

143፥1 ዘፀ34፥6፤ መዝ28፥2፤71፥2፤ 89፥1-2፤130፥2፤ 141፥1
143፥2 መዝ14፥3፤ ሮሜ3፥10
143፥3 መዝ107፥ 10፤ሰቆ3፥6
143፥4 መዝ30፥7
143፥5 ዘዳ24፥63፤ መዝ77፥6
143፥6 ዘፀ9፥29፤ ኢዮ11፥13
143፥7 መዝ22፥24 ፤27፥9፤30፥7፤69፥17፤ 142፥3
143፥8 ዘፀ33፥13፤ ኢዮ34፥32፤መዝ6፥4 ፤25፥1-2፤27፥11፤ 32፥8፤86፥4፤90፥14
143፥9 መዝ18፥17 ፤31፥15፤140፥1
143፥10 ነህ9፥20፤ መዝ25፥4-5፤26፥12፤ 31፥14፤119፥12
143፥11 መዝ25፥11 ፤31፥1፤41፥2፤71፥2
143፥12 መዝ8፥2፤ 54፥5፤116፥16
144፥1 ዘዳ49፥24

የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ያወድሳል (የ7፥17 ማብ ይመ)። *ስምህን፤* የ5፥11 ማብ ይመ። *ጻድቃን፤* የ1፥5 ማብ ይመ። *በዙሪያዬ ይሰበሰባሉ፤* ከእንግዲህ ብቻውን አይሆንም። መደምደሚያው የእግዚአብሔርን ማዳን በተስፋ የሚጠባበቅ መሆኑን ይናገራል (የ3፥8 ማብ ይመ)።

*መዝ143፤* መዝሙረኛው እግዚአብሔር ከጠላት እጅ እንዲታደገውና ልዩ ምሪትም እንዲሰጠው ያቀረበው ጸሎት ነው። ይህ መዝሙር ከሰባቱ የንስሓ መዝሙሮች ውስጥ የመጨረሻው ነው (የመዝ6 መግቢያን ይመ)። በመጀመሪያው ክፍል (ቍ1-6) ያለበትን ሁኔታ በመግለጽ አቤቱታውን ያቀርባል፤ በሁለተኛው ክፍል (ቍ7-12) ግን ጸሎቱን ብቻ ያቀርባል። ጸሎቱ በእግዚአብሔር ጽድቅ መታመንን በሚገልጽና (ቍ1:11) ደራሲውም ራሱን "አገልጋይህን" (ቍ2:12) ብሎ በሚጠራበት የተቀነበበ ነው። ደራሲው የእግዚአብሔርን ታማኝነትና (ቍ1) የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ምሕረት (ቍ12) የአቤቱታው መሠረት አድርጎአል። ለተጨማሪ ማብራሪያ ቍ7 ማብ ይመ።

*143ርእስ፤* የመዝ138 ርእስ ማብ ይመ።

*143፥1-2፤* የልመናው መግቢያ ነው።

143፥1 *በጽድቅህም፤* የ4፥1 ማብ ይመ።

*143፥2፤* ጸሎቱን ሲጀምር እግዚአብሔር በባሪያው ላይ እንዳይፈርድ በጽኑ ይማጠናል (ውድቀቱን ያውቃል)፤ ሆኖም ፊቱን በጠላቶቹና በአሳዳጆቹ ላይ እንዲመልስ ይጠይቃል።

*143፥3-4፤* የደረሰበትን መከራና መዓት የሚገልጽ ነው።

*143፥3፤* የዚህ ቍጥር ግማሹ ክፍል በሰቆ3፥6 ላይ ቃል በቃል ተጠቅሶ ይገኛል። *በጨለማ፤* ከሕይወት ተለይቶ መወገድ ማለት ነው (ቍ7፤ የ27፥1፤ 30፥1 ማብ ይመ)።

143፥4 *መንፈሴ ... ዝላለች፤* የ142፥3 ማብ ይመ። *ልቤም፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*143፥5-6፤* ባለፉት ጊዜያት እግዚአብሔር በሕይወቱ ያደረጋቸው የማዳን ሥራዎች አሁን አቤቱታውን እንዲያሰማ ጕልበት ሆነውታል።

143፥6 *እጆቼን ... ዘረጋሁ፤* ለጸሎት ማለት ነው (44፥20፤ 88፥9፤ ዘፀ9፥29 ይመ)። *ነፍሴም፤* ቍ8፤ የ6፥3 ማብ ይመ። *ተጠማች፤* የ63፥1 ማብ ይመ።

*143፥7-10፤* የጸሎቱ ክፍል ነው።

143፥7 *መንፈሴ ደከመች፤* ወይም ደግሞ ምናልባት "መንፈሴ ደከማለች" ማለት ነው። ትርጕሙ ከመዝ119፥81 ጋር ተጓዳኝ ነው፤ ሆኖም ቀጥሉ ካለው ስንኝ ጋር ሲስተያይ ግን ሐሳቡ ከመዝ104፥29 ጋር የሚቀራረብ ይመስላል። ደራሲው "መንፈሱ ብትዝልም" የአምላኩ "መልካም መንፈስ" በደኅና ትመራዋለች (ቍ10)፤ እነዚህ ሁለት ሐሳቦች ጸሎቱን ለመቀንበቢያ ያገለግላሉ። *ፊትህን ... አትሰውር፤* የ13፥1 ማብ ይመ። *ጕድጓድ፤* ቍ3 እና የ30፥1 ማብ ይመ።

143፥8 *በማለዳ፤* አሁን ካለበት "ጨለማ" የሚያድነው ነው (ቍ3፤ የመዝ57 መግቢያ ይመ)። *ምሕረትህን፤* ቍ12፤ የ6፥4 ማብ ይመ። *መንገድ አሳየኝ፤* ቍ10 ይመ። ከጠላቶቹ ሰይፍ መዳን ብቻውን በቂው አይደለም፤ መንገዱን እንዲያሳየውና በዚያም መንገድ እንዲመራው ያስፈልጋል።

143፥10 *በቀናችው መንገድ፤* የ26፥12 ማብ ይመ።

*143፥11-12፤* የጸሎቱ አጠቃላይ መደምደሚያ ነው (መግቢያውን ይመ)።

143፥11 *ስለ ስምህ፤* የ23፥3 ማብ ይመ።

143፥12 *ጠላቶቼንም ደምስሳቸው፤* የ5፥10 ማብ ይመ።

*መዝ144፤* በጨካኝ ጠላቶቹ ላይ ድልን ለመቀዳጀት የሚፈልግ አንድ ንጉሥ ያቀረበው ጸሎት ነው (ነገር ግን የቍ12-15 ማብ ይመ)። ቍ1-10 ከመዝ18 ጋር ብዙ ተመሳሳይነት እንዳለው ያሳያል። ይህ ክፍል በአጀማመሩና በአጨራረሱ ከመዝ18 ጋር አንድ ነው። ከቍ5-7 ያለው ሐሳብ በዚያ መዝሙር ውስጥ ዐልፎ ዐልፎ ይገኛል። የቀረው የዚህ መዝሙር ክፍል ከሌሎች መዝሙሮች ጋር ተመሳሳይ ሐሳብ ያለው ሲሆን፣ የዚህ መዝሙር ደራሲ ከእነዚህ መዝሙሮች በቀጥታ ሳይወስድ አልቀረም። የመዝሙሩ ዋና ክፍል (ቍ1-10) የመዝሙረኛው የተለመደ ጸሎት ሲሆን መደምደሚያው ግን (ቍ12-15) በጣም የተለየ ነው። ቍ11 መሸጋገሪያ ይመስላል።

*144ርእስ፤* የመዝ138 ርእስ ማብ ይመ።

*144፥1-2፤* ለእግዚአብሔር የቀረበ ምስጋና ነው። የጸሎቱ መክፈቻ እንደ መሆኑ የአቤቱታው መጀመሪያና (143፥1-2) ጸሎቱም እንደሚሰማ ያለውን እምነት የገለጸበት ነው። በዚህ ክፍል ለእግዚአብሔር የተሰጡት ማዕረጎች በመዝ18 ላይ እንደሚገኙ ልብ በል።

2 እርሱ አፍቃሪ አምላኬና ጽኑ ዐምባዬ
ነው፤
ምሽጌና ታዳጊዬ፣
የምከለልበትም ጋሻዬ ነው፤
ሕዝቤን የሚያስገዛልኝም+ እርሱ ነው።
3 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ይህን ያህል በልብህ
ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድን
ነው?
ታስበውስ ዘንድ የሰው ልጅ እስከዚህ
ምንድን ነው?
4 ሰው እንደ እስትንፋስ ነው፤
ዘመኑም ፈጥኖ እንደሚያልፍ ጥላ ነው።
5 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ሰማያትህን ሰንጥቀህ
ውረድ፤
ይጤሱም ዘንድ ተራሮችን ዳስስ።
6 የመብረቅ ብልጭታ ልከህ በትናቸው፤
ፍላጻህን ሰደህ ግራ አጋባቸው።
7 እጅህን ከላይ ዘርጋ፤
ከኀይለኛ ውሃ፣
ከባዕዳንም እጅ፣
ታደገኝ፤ አድነኝም፤
8 አንደበታቸው ሐሰትን ይናገራል፤
ቀኝ እጃቸውም የቅጥፈት ቀኝ እጅ
ናት።
9 አምላክ ሆይ፤ አዲስ ቅኔ እቀኝልሃለሁ፤
ዐሥር አውታር ባለው በገና
እዘምርልሃለሁ።
10 ነገሥታትን ድል የሚያጐናጽፍ፣
ባሪያውን ዳዊትን ከሚጐዳ ሰይፍ
የሚያድነው እርሱ ነው።
11 አንደበታቸው ሐሰትን ከሚናገር፣
ቀኝ እጃቸው የቅጥፈት ቀኝ እጅ
ከሆነችው፣
ከባዕዳን እጅ፣
ታደገኝ፤ አድነኝም።

144፥2 ዘፍ15፥1፤ መሳ4፥23፤መዝ18፥2፤ 39፥27፥1፤37፥39፤ 43፥2፤59፥9፤91፥2
144፥3 ዕብ2፥6
144፥4 1ዜና29፥15 ፤ኢዮ7፥7፤14፥2፤27፥3 ፤ኢሳ2፥22፤ያዕ4፥14
144፥5 ዘፍ11፥5፤ መዝ18፥9፤57፥3፤ 104፥32፤ኢሳ64፥1
144፥6 መዝ7፥12-13፤18፥14፤59፥11፤ 68፥1፤ዕን3፥11፤ ዘካ9፥14
144፥7 2ሳሙ22፥17 ፤መዝ3፥7፤18፥44፤ 57፥3፤69፥2
144፥8 ዘፍ14፥22፤ ዘዳ32፥40፤መዝ12፥2፤ 36፥3፤41፥6
144፥9 መዝ28፥7፤ 33፥2-3፤71፥22፤96፥1
144፥10 2ሳሙ8፥14 ፤ኢዮ5፥20፤መዝ 18፥50
144፥11 መዝ3፥7፤ 12፥2፤18፥44፤25፥20 ፤36፥3፤41፥6-7፤ 106፥26፤ኢሳ44፥20
144፥12 መዝ92፥12 -14፤128፥3፤መሓ4፥4 ፤7፥4
144፥13 ምሳ3፥10
144፥14 2ነገ25፥11 ፤ምሳ14፥4፤ኢሳ24፥ 11፤ ኤር14፥2-3
144፥15 ዘዳ28፥3
145፥1 መዝ2፥6፤ 5፥2፤30፥1፤34፥1፤ 54፥6
145፥2 መዝ34፥1፤ 71፥6፤ኢሳ25፥1፤ 26፥8
145፥3 2ሳሙ22፥4 ፤ኢዮ5፥9፤መዝ95፥3 ፤96፥4፤

12 ወንዶች ልጆቻችን በወጣትነታቸው፣
የተሟላ ዕድገት እንዳገኙ ተክል፣
ሴቶች ልጆቻችንም ቤተ መንግሥት
ለማስጌጥ፣
እንደ ተቀረጹ የማእዘን ዐምዶች ይሁኑ።
13 ጐተራዎቻችን በተለያየ የእህል ዐይነት፣
የተሞሉ ይሁኑ፤
በጎቻችን እስከ ሺህ ይውለዱ፤
በመስኮቻችንም እስከ ዐሥር ሺህ ይባዙ።
14 ከብቶቻችን ይክበዱ፤*
አይጨንግፉ፤ አይጥፉም።
እኛም በምርኮ አንወሰድ፤
በአደባባዮቻችንም ዋይታ አይሰማ።
15 ይህ ባርኮት ገንዘቡ የሆነ ሕዝብ ምስጉን
ነው፤
*እግዚአብሔር* አምላኩ የሆነ ሕዝብ
ምስጉን ነው።

## መዝሙር 145[1]

## ምስጋና ለንጉሡ ለእግዚአብሔር

የዳዊት የምስጋና መዝሙር

1 አምላኬና ንጉሤ ሆይ፤ ከፍ ከፍ
አደርግሃለሁ፤
ስምህን ከዘላለም እስከ ዘላለም
እባርካለሁ።
2 በየቀኑ እባርክሃለሁ፤
ስምህንም ከዘላለም እስከ ዘላለም
አመሰግናለሁ።
3 *እግዚአብሔር* ታላቅ ነው፤ እጅግ
ሊመሰገንም ይገባዋል፤
ታላቅነቱም አይመረመርም።

+2 አንዳንዶች ሕዝቦችን የሚያስገዛልኝ ይላሉ።
*14 ወይም *መሪዎቻችን ይጠነክራሉ*።
[1] መ145 ይህ መዝሙር ተከታታይ በሆኑ የዕብራይስጥ ፊደላት የሚጀምር ሲሆን (ከቍ13 ጭምር) መነሻዎቹ ወይም መነሻዎቹና መድረሻዎቹ ሆህያት ቍልቍል ሲነበቡ ትርጕም ያላቸውን ቃላት የሚፈጥሩ ናቸው።

144፥2 *አፍቃሪ አምላኬና፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ዘላለማዊ ፍቅሬ" ማለት ነው (የ6፥4 ማብ ይመ)። መዝሙረኛው እግዚአብሔርን እንዲህ በማለት የጠራው እግዚአብሔር የፍቅር ምንጭ ስለሆነለት ነው፤ እግዚአብሔር የድነት ምንጭ በመሆኑ "አዳኜ" ተብሎ እንደሚጠራ ነው (27፥1፤35፥3፤62፥2 ይመ)።

*144፥3-4፤* የሰው ልጅ ከምንም የማይቈጠርና ይልቁንም የእግዚአብሔርን ርዳታ የሚሻ ፍጡር መሆኑን የሚገልጽ ነው።

*144፥3፤* ከ8፥4 ጋር ተመሳሳይ ነው።

*144፥4፤* 39፥4-6 እና ማብ ይመ።

*144፥5-8፤* እግዚአብሔር ነጻ እንዲያወጣው ያቀረበው ጸሎት ነው።

*144፥5፤* 18፥9 እና የ18፥7-15 ማብ ይመ።

*144፥6፤* 18፥14 እና ማብ ይመ።

*144፥7፤* 18፥16-17 እና የ32፥6 ማብ ይመ። *ባዕዳን፤* ተዋሳኝ መንግሥታት ናቸው።

144፥8 *አንደበታቸው፤* የ5፥9 ማብ ይመ። *ቀኝ እጃቸውም፤* ቃል ለመግባት ወይም ራስን ለመስጠት ሲፈለግ እጅ ወደ ላይ ይነሣል (106፥26፤ ዘፀ6፥8፤ ዘዳ32፥40 ይመ)።

*144፥9-10፤* መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ለማመስገን ቃል ይገባል (የ7፥17 ማብ ይመ)።

144፥9 *አዲስ ቅኔ፤* የ33፥3 ማብ ይመ።

144፥10 *ባሪያውን ዳዊትን፤* የመዝ18ርእስ ማብ ይመ።

*144፥11፤* በቍ7-8 ላይ የቀረበው ጸሎት እዚህም ላይ ተደግሞአል፤ ይህም ለሚቀጥለው ሐሳብ እንደ መሸጋገሪያ ያገለግላል። እግዚአብሔር ባሪያውን ዳዊትን ነጻ ካወጣ መንግሥቱ ያብባል፤ ደግሞም ዋስትና ያገኛል።

*144፥12-15፤* እዚህ ላይ የቀረበው ጸሎት ከቍ1-11 ጋር ምንም ግንኙነት የለውም የሚሉ ሊቃውንት አሉ፤ ሆኖም ቍ11 እንደ መሸጋገሪያ በመሆን ይህን ክፍል ከላይኛው ክፍል ያያይዛል።

144፥12 *ሴቶች ልጆቻችንም ... እንደ ተቀረጹ ... ዐምዶች፤* በሴቶች አምሳል የሚቀረጹ የቤተ መቅደስ ዐምዶችን ማየት ያልተለመደ አይደለም (በግሪክ እንዲህ ያለ ቅርጽ ያላቸውን ዐምዶች በብዛት ማግኘት ይቻላል)።

144፥14 *ከብቶቻችን ይክበዱ፤* ወይም "በሬዎቻችን ይወፍራሉ" ወይም "በሬዎቻችን ይከብዳሉ" ማለት ነው፤ አማራጭ ትርጕሙን ይመ።

144፥15 *ምስጉን፤* የ1፥1 ማብ ይመ።

*መዝ145፤* ድንቅ ሥራውና ታማኝነቱ የንጉሣዊ አገዛዙ ክብር ለሆነው፣ ለታላቁ ንጉሥ ለእግዚአብሔር የተዘመረ መዝሙር ነው። ሁለት መስመር መግቢያና (ቍ1-2) አንድ መስመር መደምደሚያ (ቍ21) ያለው ይህ መዝሙር በርካታ ፍሬ ሐሳቦችን በየደረጃው የሚያሳድጉ አራት አንቀጾች አሉት (ቍ3፡8፡ 13ለ፡17 ይመ)።

145ርእስ *የምስጋና መዝሙር፤* በዕብራይስጥ ቴሂላ ይባላል፤ ርእስ ሆኖ የተጠቀሰውም በዚህ ቦታ ብቻ ነው፤ ሆኖም የመዝሙረኛው ስም "ቴሂሊም" ከሚለው ብዙ ቍጥር የመጣ ነው። *የዳዊት፤* የመዝ 138 ርእስ ማብ ይመ።

*145፥1-2፤* እግዚአብሔርን ለማመስገን ቃል የገባበት ቦታ ነው። *ስምህን፤* ቍ21 ይመ። መዝሙሩም የተቀነበበው በዚሁ ነው (የ5፥11 ማብ ይመ)።

*145፥3-7፤* ታላቅነቱን (ቍ 3) እና መልካምነቱን (ቍ 7)

[4]ሥራህን አንዱ ትውልድ ለሌላው
ትውልድ ያስተጋባል፤
ብርቱ ሥራህን ያውጃል።
[5]ስለ ግርማህ ውበትና ክብር ይናገራሉ፤
ስለ ድንቅ ሥራህም[ʼ] ያወራሉ።
[6]ስለ ድንቅ ሥራህ ብርታት ይነጋገራሉ፤
እኔም ስለ ታላቅነትህ አውጃለሁ።
[7]የበጎነትህን ብዛት በደስታ ያወሳሉ፤
ስለ ጽድቅህም በእልልታ ይዘምራሉ።
[8]*እግዚአብሔር* ቸር ነው፤ ርኅሩኅም ነው፤
ለቍጣ የዘገየ፣ ምሕረቱ የበዛ።
[9]*እግዚአብሔር* ለሁሉ ቸር ነው፤
ምሕረቱም በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ነው።
[10]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ፍጥረትህ ሁሉ
ያመሰግንሃል፤
ቅዱሳንህም ይባርኩሃል።
[11]ስለ መንግሥትህ ክብር ይናገራሉ፤
ስለ ኀይልህም ይነጋገራሉ፤
[12]በዚህም ብርቱ ሥራህን፣
የመንግሥትህንም ግርማ ክብር
ያስታውቃሉ።
[13]መንግሥትህ የዘላለም መንግሥት ናት፤
ግዛትህም ለትውልድ ሁሉ ጸንቶ
ይኖራል።

*እግዚአብሔር* ቃሉን ሁሉ ይጠብቃል፤
በሥራውም[ᵀ] ሁሉ ቸር ነው።
[14]*እግዚአብሔር* የሚንገዳገዱትን ሁሉ
ይደግፋል፤
የወደቁትንም ሁሉ ያነሣል።
[15]የሁሉ ዐይን አንተን በተስፋ ይጠብቃል፤
አንተም ምግባቸውን በወቅቱ
ትሰጣቸዋለህ።
[16]አንተ እጅህን ትዘረጋለህ፤
የሕያዋን ፍጥረታትንም ሁሉ ፍላጎት
ታረካለህ።

[17]*እግዚአብሔር* በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ፣
በሥራውም ሁሉ ቸር ነው።
[18]*እግዚአብሔር* ለሚጠሩት ሁሉ፣
በእውነት ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው።
[19]ለሚፈሩት ፍላጎታቸውን ይፈጽማል፤
ጩኸታቸውን ይሰማል፤ ያድናቸዋልም።
[20]*እግዚአብሔር* የሚወዱትን ሁሉ
ይጠብቃል፤
ክፉዎችን ሁሉ ግን ያጠፋል።

[21]አፌ *የእግዚአብሔርን* ምስጋና ይናገራል፤
ፍጡር ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም፣
ቅዱስ ስሙን ይባርክ።

## መዝሙር 146

### ለረድኤት አምላክ ምስጋና

[1]ሃሌ ሉያ።[ʌ]
ነፍሴ ሆይ፤ *እግዚአብሔርን* ባርኪ።
[2]በምኖርበት ዘመን ሁሉ *እግዚአብሔርን*
አመሰግናለሁ፤
በሕይወትም እስካለሁ ለአምላኬ
እዘምራለሁ።
[3]በገዦች አትታመኑ፤
ማዳን በማይችሉ ሥጋ ለባሾችም
አትመኩ።
[4]መንፈሳቸው ትወጣለች፤ ወደ
መሬታቸውም ይመለሳሉ፤
ያን ጊዜም ዕቅዳቸው እንዳልነበር
ይሆናል።

[5]ረዳቱ የያዕቆብ አምላክ የሆነ፣
ተስፋውንም በአምላኩ *በእግዚአብሔር*
ላይ የጣለ ሰው ምስጉን ነው፤

145፥4 ዘጸ11፥19፤ መዝ22፥30፤71፥16
145፥5 መዝ75፥1፤ 96፥6፤148፥13
145፥6 ዘጸ32፥3፤ መዝ66፥3፤75፥1፤78፥4፤106፥22
145፥7 ዘፀ18፥9፤ መዝ5፥11፤27፥13፤101፥1፤138፥5
145፥8 መዝ86፥5፡15፤103፥8
145፥9 1ዜና16፥34 1መዝ103፥13-14፤ 136፥1፤ማቴ19፥17፤ ማር10፥18
145፥10 መዝ8፥6፤ 30፥4፤103፥22፤115፥17-18፤139፥14፤ 148፥14፤149፥9
145፥11 ቍ12-13፤ ዘፀ15፥2፤መዝ21፥13፤ ማቴ6፥33
145፥12 ቍ11፤መዝ 75፥1፤103፥19፤105፥1፤ኢሳ2፥10፡19፡21
145፥13 ዘፀ15፥18፤ ዘጸ7፥9፤ኢሱ23፥14፤ 1ቆሮ1፥9፤1ጢሞ 1፥17፤2ጴጥ1፥11፤ ራእ11፥15
145፥14 1ሳሙ2፥8 1መዝ37፥17፤38፥6፤ 146፥8
145፥15 ዘፍ1፥30፤ ኢዮ28፥5፤መዝ 37፥25፤ማቴ6፥26
145፥16 መዝ90፥14 ፤104፥28
145፥17 ቍ13፤ዘፀ 9፥27፤ዕዝ9፥15
145፥18 ዘኍ23፥21 1መዝ18፥6፤46፥1፤ 80፥18፤ፊል4፥5
145፥19 1ሳሙ10፥19፤ኢዮ22፥28፤መዝ 7፥10፤20፥4፤31፥22፤ 34፥18፤40፥1
145፥20 መዝ1፥6፤ 31፥23፤91፥14፤94፥2 3፤97፥10
145፥21 ዘፀ3፥15፤ መዝ30፥4፤65፥2፤71፥8፤99፥3፤150፥6
146፥1 መዝ103፥1፤104፥1
146፥2 መዝ63፥4፤104፥33፤105፥2
146፥3 መዝ 60፥11፤ 108፥12፤118፥9፤ኢሳ2፥22
146፥4 ዘፍ3፥19፤ኢዮ7፥21፤መዝ33፥10፤ 103፥14፤መክ12፥7፤1ቆሮ2፥6
146፥5 መዝ33፥18፤37፥9፤ 70፥5፤71፥5፤119፥43፤121፥2፤144፥15፤ኤር17፥7

ʼ5 የሙት ባሕር ጥቅልሉች እና ሱርስት (የሰብዓ ሊቃናትን ትርጒም ይመ) *ስለግርማህ ታላቅነትና ክብር፣ ዕፁብ ድንቅ ሥራህን አሰላስላለሁ* ይላሉ።
ᵀ13 አንድ የማሶሬቲክ ቅጅ፣ የሙት ባሕር ጥቅልሉች እና ሱርስት (የሰብዓ ሊቃናትን ትርጒም ይመ) እንዲሁም አብዛኛው የማሶሬቲክ ቅጆች የቍ13 ሁለት ስንኞች የሏቸውም።
ʌ1 አንዳንዶች ከ10 *ጭምር እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።

የሚገልጸውን የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ያወድሳል፤ ደራሲውም ሐሳቡን ያዋቀረው በእነዚህ ቃላት ነው። ተመሳሳይ ሐሳብ ለማግኘት 86፥10፡17፤ 135፥3፡5 ይመ።

145፥4 *ያስተጋባል ... ያውጃል፤* ቍ5-7፡10-12፡21 እንዲሁም የ9፥1 ማብ ይመ። *ሥራህን፤* በፍጥረት ጊዜ ያከናወነውን እንዲሁም ሕዝቡን ማዳኑንና ለሕዝቡም የሚያስፈልገውን ክብካቤ ማድረጉን ያመለክታል።

145፥7 *ጽድቅህም፤* ቍ17 እንዲሁም የ4፥1 ማብ ይመ።

*145፥8-13፤* ፍጥረት ሁሉ የመንግሥቱን ክብር እንዲያወራ የሚያደርገውን የእግዚአብሔርን በጎነት የሚያወድስ ክፍል ነው።

*145፥8፤* ዘፀ34፥6-7 እና ማብ ይመ።

145፥10 *ፍጥረትህ ሁሉ ያመሰግንሃል፤* ቍ21 እና የ65፥13 ማብ ይመ። *ቅዱሳንህም፤* የ4፥3 ማብ ይመ።

*145፥13-16፤* የእግዚአብሔርን ታማኝነት የሚያወድስ ክፍል ነው።

145፥13-17 *የሚወድ፤* የ6፥4 ማብ ይመ። የእግዚአብሔር ታማኝነትና ፍቅር በአንድነት ተጣምረው የቀረቡበትን ለማየት የ36፥5 ማብ ይመ።

*145፥17-20፤* የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚያወድስ ክፍል ነው።

145፥18 *በእውነት፤* በታማኝነት ለማለት ነው።

*145፥21፤* ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ምስጋና ሁልጊዜ ይቀጥላል፤ ፍጥረትም ሁሉ ለዘላለም ያመሰግነዋል። *ፍጡር ሁሉ፤* ወይም ምናልባት "ሰው ሁሉ" ለማለት ነው (ቃል በቃል ሲተረጒም "ሥጋ ለባሽ ሁሉ"፤ 65፥2 ይመ "ሰው ሁሉ" እንዲሁም 150፥6 ይመ)።

*መዝ146፤* ሰዎች የጽዮን ንጉሥ በሆነው ጌታ እንዲታመኑ የተሰጠ ምክር ነው። መዝሙረኛው መጽሐፉን ለመዝጋት ከተጠቀመበት አምስት የሃሌሉያ (የምስጋና) መዝሙሮች ውስጥ አንዱ ነው፤ የተጻፈውም ከምርኮ በኋላ ሳይሆን አይቀርም። ይህ መዝሙርና ከዚህ በኋላ ያሉት አራት መዝሙሮች ሃሌሉያ በሚል ቃል የተቀነበቡ ሲሆን ይህም መዝሙሩን በመጨረሻ ባረሙት ሰዎች የተጨመረ ሊሆን ይችላል (መዝ105-106፤ 111-117 ይመ)።

*146፥1-2፤* በሕይወት እስካለ ድረስ እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግን ቃል የገባበት ቦታ ነው (145፥21 ይመ)።

146፥1 *ነፍሴ ሆይ፣ እግዚአብሔርን ባርኪ፤* በመዝ103-104 ዙሪያ ያሉ ቅንብቦችን ይመ። *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ።

*146፥3-4፤* ሕዝቦች በእግዚአብሔር እንዲታመኑ የቀረበ ጥሪ ነው (ቍ5-9 ይመ)፤ በእግዚአብሔር መታመንና በሌሎች ማናቸውም ነገሮች መታመን ተነጻጽረው ቀርበዋል።

*146፥5-9፤* የያዕቆብ አምላክ በሆነው በእግዚአብሔር እንዲታመኑ የተሰጠ ምክር ነው (የ14፥7 ማብ ይመ)። እርሱ ፈጣሪ በመሆኑ የሁሉ ጌታ ነው፤ ታማኝ በመሆኑ የምስኪኑ ዳኛ፣ ለድሃ አደጉም መጋቢ ነው፤ ጻድቅ በመሆኑም ለጻድቃን ይፈርዳል፤ የክፉዎችን አካሄድ ግን አንድ በአንድ ይመዝናል።

[6]እርሱ ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም፣
በእነዚህም ውስጥ ያለውን ሁሉ የፈጠረ፣
ታማኝነቱንም ለዘላለም የሚጠብቅ ነው፤
[7]ለተበደሉት የሚፈርድ፣
ለተራቡት ምግብን የሚሰጥ እርሱ ነው፤
እግዚአብሔር እስረኞችን ከእስራት
ያወጣል፤
[8]እግዚአብሔር የዕውራንን ዐይን ያበራል፤
እግዚአብሔር የተዋረዱትን ከፍ
ያደርጋል፤
እግዚአብሔር ጻድቃንን ይወዳል፤
[9]እግዚአብሔር ስደተኞችን ይጠብቃል፤
ድኻ አደጎችንና መበለቶችን ይደግፋል፤
የክፉዎችን መንገድ ግን ያጠፋል።
[10]እግዚአብሔር ለዘላለም ይነግሣል፤
ጽዮን ሆይ፤ አምላክሽ ለትውልድ ሁሉ
ንጉሥ ነው።
ሃሌ ሉያ።

## መዝሙር 147

### መዝሙር ለሁሉን ቻይ አምላክ

[1]ሃሌ ሉያ።[h]
አምላካችንን በመዝሙር ማወደስ እንዴት
መልካም ነው፤
እርሱን ማመስገን ደስ ያሰኛል፤ ይህ
ተገቢም ነው።
[2]እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን መልሶ
ይሠራታል፤
ከእስራኤል የተበተኑትን ይሰበስባል።
[3]ልባቸው የተሰበረውን ይፈውሳል፤
ቍስላቸውንም ይጠግናል።
[4]የከዋክብትን ብዛት ያውቃል፤
እያንዳንዱንም በስሙ ይጠራዋል።
[5]ጌታችን ታላቅ ነው፤ እጅግ ኀያልም ነው፤
ለጥበቡም ወሰን የለውም።
[6]እግዚአብሔር የተናቁትን ከፍ ያደርጋል፤
ክፉዎችን ግን ወደ ምድር ይጥላል።
[7]ለእግዚአብሔር በምስጋና ዘምሩ፤
ለአምላካችንም በመሰንቆ ምስጋና አቅርቡ።
[8]ሰማይን በደመናት የሚሸፍን እርሱ ነው፤
ለምድርም ዝናብን ይሰጣል፤
በተራሮችም ላይ ሣር ያበቅላል።
[9]ለእንስሳት ምግባቸውን፣
የቍራ ጫጩቶችም ሲንጫጩ
የሚበሉትን ይሰጣቸዋል።
[10]እርሱ በፈረስ ኀይል አይደሰትም፤
በሰዎችም ብርታት ላይ ደስታውን
አያደርግም።
[11]ነገር ግን እግዚአብሔር በሚፈሩት፣
በምሕረቱ በሚታመኑትም ይደሰታል።
[12]ኢየሩሳሌም ሆይ፤ እግዚአብሔርን
አመስግኚ፤
ጽዮን ሆይ፤ አምላክሽን አወድሺ፤
[13]እርሱ የደጆችሽን መወርወሪያ
አጽንቶአልና፤
ልጆችሽንም በውስጥሽ ባርኮአል።
[14]በድንበርሽ ውስጥ ሰላም ያሰፍናል፤
ማለፊያ ስንዴም ያጠግብሻል።
[15]ትእዛዙን ወደ ምድር ይልካል፤
ቃሉም እጅግ በፍጥነት ይሮጣል።
[16]ዐመዳዩን እንደ በርኖስ ይዘረጋል፤
ውርጩን እንደ ዐመድ ይነሰንሳል።
[17]የበረዶውን ድንጋይ ቍልቍል ይለቃል
ይወረውረዋል፤
በውሽንፍሩስ ቅዝቃዜ ፊት ማን ሊቆም
ይችላል?
[18]ቃሉን ልኮ፤ ያቀልጣቸዋል፤
ነፋሱን ያነፍሳል፤ ውሆችንም ያፈሳል።

146፥6 ዘጸ7፥9፤2ዜና 2፥12፤መዝ18፥25፤ 108፥4፤115፥15፤117፥2 ፤ሐሥ14፥15፤ራእ10፥6
146፥7 መዝ37፥17፤ 66፥11፤68፥6፤103፥6 ፤107፥9፤145፥15
146፥8 ዘዳ4፥11፤ዘዳ 7፥13፤ኢዮ23፥10፤ መዝ38፥6፤ምሳ20፥12፤ ኢሳ29፥18፤32፥3፤ 35፥5፤42፥7፥18-19፤ 43፥8፤ማቴ11፥5
146፥9 ዘፀ22፥22፤ ዘሌ19፥34፤መዝ10፥18 ፤ያዕ1፥27
146፥10 ዘፍ21፥33፤ 1ዜና16፥31፤መዝ93፥1 ፤99፥1፤ራእ11፥15
147፥1 መዝ33፥1፤ 135፥3
147፥2 መዝ51፥18 ፤106፥47
147፥3 ዘኍ12፥13 ፤ኢዮ5፥18፤መዝ34፥ 18፤ኢሳ1፥6፤ሕዝ 34፥16
147፥4 ዘፍ15፥5
147፥5 ዘፀ14፥31፤ መዝ48፥1፤145፥3፤ ኢሳ40፥28
147፥6 2ዜና33፥23 ፤መዝ37፥9-10፤ 145፥20፤146፥8-9
147፥7 መዝ27፥6፤ 30፥4፤33፥3፤42፥4፤ 98፥5
147፥8 ዘዳ11፥14፤ 32፥2፤2ሳሙ1፥21፤ ኢዮ5፥10፤26፥8፤28፥ 26፤መዝ104፥14
147፥9 ዘፍ1፥30፤ 8፥7፤መዝ104፥27-28 ፤ማቴ6፥26
147፥10 1ሳሙ16፥7 ፤ኢዮ39፥11፤መዝ33፥ 16-17
147፥11 መዝ6፥4፤ 33፥18፤35፥27፤103፥ 11፤119፥43
147፥12 መዝ48፥1
147፥13 ዘዳ33፥25 ፤ዘሌ25፥21፤መዝ128፥5፤134፥3
147፥14 ዘሌ26፥6፤ ዘዳ32፥14፤2ሳሙ7፥10፤መዝ132፥15፤ኢሳ48፥18
147፥15 ኢዮ37፥12 ፤መዝ33፥9፤148፥5፤ኢሳ 55፥1
147፥16 መዝ148፥8፤ኢዮ37፥12፤38፥29
147፥17 ዘፀ9፥22-23፤ ኢዮ38፥22፤መዝ78፥47
147፥18 ቍ15፤ መዝ 33፥9፤50፥3፤107፥20

[h]1 አንዳንዶች ከቍ20 ጭምር እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ።

146፥6 *ሰማይንና ምድርን ... የፈጠረ፤* የ121፥2 ማብ ይመ።

146፥8 *ጻድቃንን፤* የ1፥5 ማብ ይመ።

*146፥10፤* በእግዚአብሔር ንጉሣዊ ከተማ ለሚኖሩ ዜጎች የተሰጠ ታላቅ የመደምደሚያ ምስክርነት ነው። *ጽዮን፤* የ9፥11 ማብ ይመ።

*መዝ147፤* ለእስራኤል ሕዝብ የተለየ ምሕረቱን ሳደረገ አምላክና ፈጣሪ የተዘጋጀ መዝሙር ነው፤ የኢየሩሳሌም ቅጥር ተሠርቶ በተመረቀበት የደስታ ቀን ሌዋዊ መዘምራን እንዲዘምሩት የተዘጋጀ ሳይሆን አይቀርም (ነህ12፥27-43 ይመ)። የሰብዐ ሊቃናት ትርጕም (ወደ ግሪክ የተመለሰው የብሉይ ኪዳን ትርጕም) ይህን መዝሙር ሁለት ቦታ ይከፍለዋል (1-11፤12-20)፤ በእርግጥ ግን መዝሙሩ ሦስት ክፍል ያለው (1-6፤7-11፤12-20) ሲሆን፣ ክፍሎቹም እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን ልዩ ክብካቤ በሚገልጹ ጥቅሶች (ቍ2-3፤19-20) የተቀነበቡ ናቸው። የመዝ146 መግቢያ ይመ።

*147፥1፤* የ135፥3 ማብ ይመ።

147፥2 *ይሠራታል ... ይሰበስባል፤* ከምርኮ በኋላ የሚሆነውን የኢየሩሳሌምንና የእስራኤልን ተመልሶ መታደስ የሚያሳስብ ነው።

147፥3 *ልባቸው የተሰበረውን፤* በምርኮ የነበሩትንና (መዝ 137 ይመ፤ ከመዝ126 ጋር ያነጻጽሩ) የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደ ገና ሲሠሩ ታቃውሞ የገጠማቸውን (ነህ2፥17-20፤ 4፥1-23) ሁሉ የሚያመለክት ነው።

*147፥4-6፤* የከዋክብትን ብዛት መወሰንና (ወይም ብዛታቸውን መቍጠርና) እያንዳንዳቸውንም በስማቸው መጥራት የሚችለው ኀያልና ብርቱ ጌታ የእርሱ የሆኑትን ይጠብቃል፤ ክፉዎችን ግን ያዋርዳል (20፥8፤ 146፥9፤ ኢሳ40፥26-29 ይመ)።

147፥6 *የተናቁትን፤* አንዳች መመኪያ እንደሌላቸው የተገነዘቡትን ለማለት ነው (149፥4 ይመ)። *ምድር፤* ምናልባት መቃብርን ሳያመለክት አይቀርም (የ61፥2 ማብ ይመ)።

*147፥7-11፤* ዝናብን እንደወደደ የሚያዘንበውና ለምድር አራዊትና እንስሳት ምግብን የሚሰጠው አምላክ የሰው ልጅ በራሱ ችሎታ በመደገፉ ወይም በዙሪያው ባሉ እንስሳት (ወይም በሰውቀቱ በሠራቸው ዘመናዊ መሣሪያዎች) በመታመኑ ደስ አልተሰኘም፤ እግዚአብሔር ደስ የሚሰኘው ሰዎች ሲያገለግሉትና እርሱን ብቻ ተስፋ ሲያደርጉት ነው።

147፥11 *በሚፈሩት፤* የ34፥8-14 ማብ ይመ። *ምሕረቱ፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

*147፥12-18፤* የፍጥረት ሁሉ ጌታ የሆነው የጽዮን አምላክ የሕዝቡን ጸጥታና ሰላም እንዲሁም ሀብትና የተትረፈረፈ ምርት ሁሉ ነቅቶ ይጠብቃል። መዝሙሩ እያንዳንዱን የአየር ንብረት ዘርዝሮአል:- ደመናና ዝናብ (ቍ8)፣ በረዶ፣ ዐመዳይና ውርጭ (ቍ16-17)፣ የበረዶ ውሽንፍርና ነፋስ (ቍ17-18)።

147፥15 *ትእዛዙን ... ቃሉም፤* የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም እንደ ተላኩ ሰዎች በሰውኛ አገላለጽ ተመስለው ቀርበዋል (የ23፥6፤ 33፥4፤ 104፥4 ማብ ይመ)።

19 ቃሉን ለያዕቆብ፣
ሥርዐቱንና ፍርዱን ለእስራኤል
ይገልጣል።
20 ይህን ለማንኛውም ሌላ ሕዝብ
አላደረገም፤
እነርሱም ፍርዱን አላወቁም።

ሃሌ ሉያ።

## መዝሙር 148

### ፍጥረተ ዓለም ሁሉ ያመስግን

1 ሃሌ ሉያ።[ሀ]

*እግዚአብሔርን* ከሰማያት አመስግኑት፤
በላይ በአርያም አመስግኑት።
2 መላእክቱ ሁሉ አመስግኑት፤
ሰራዊቱ ሁሉ አመስግኑት፤
3 ፀሐይና ጨረቃ አመስግኑት፤
የምታበሩ ከዋክብት ሁሉ አመስግኑት።
4 ሰማየ ሰማያት አመስግኑት፤
ከሰማያትም በላይ ያላችሁ ውሆች
አወድሱት።
5 እርሱ ስላዘዘ ተፈጥረዋልና፣
*የእግዚአብሔርን* ስም ያመስግኑት።
6 ከዘላለም እስከ ዘላለም አጸናቸው፤
የማይሻርም ሕግ ደነገገላቸው።

7 የባሕር ውስጥ ግዙፍ ፍጥረትና ጥልቅ
ውሆች ሁሉ፣
*እግዚአብሔርን* ከምድር አመስግኑት።
8 እሳትና በረዶ፣ ዐመዳይና ጭጋግ፣
ትእዛዙንም የሚፈጽም ዐውሎ ነፋስ፣
9 ተራሮችና ኮረብቶች ሁሉ፣
የፍሬ ዛፎችና ዝግባዎች ሁሉ፣
10 የዱር አራዊትና የቤት እንስሳት ሁሉ፣
በምድር የሚሳቡ ፍጥረታትና የሚበሩ
ወፎችም፣
11 የምድር ነገሥታትና ሕዝቦች ሁሉ፣
መሳፍንትና የምድር ገዦች ሁሉ፣
12 ወጣት ወንዶችና ደናግል፣
አረጋውያንና ልጆች ያመስግኑት።
13 ስሙ ብቻውን ከፍ ያለ ነውና፣
ክብሩም ከምድርና ከሰማይ በላይ ነውና፣
እነዚህ ሁሉ *የእግዚአብሔርን* ስም
ያመስግኑ።
14 እርሱ ለሕዝቡ ቀንድን[ለ] አስነሥቶአል፤
ለቅዱሳኑ ሁሉ ምስጋና፣
እጅግ ቅርቡ ለሆነው ሕዝቡ፣ ለእስራኤል
ልጆች።

ሃሌ ሉያ።

## መዝሙር 149

### የድል መዝሙር

1 ሃሌ ሉያ።[ሐ]

*ለእግዚአብሔር* አዲስ ቅኔ ተቀኙ፤
ምስጋናውንም በቅዱሳን ጉባኤ ዘምሩ።

147፥19 ዘፀ20፥1፤ ዘዳ33፥4፤ ኢሱ1፥8፤ 2ነገ22፥8፤ መዝ78፥5፤ ሚል4፥4፤ ሮሜ3፥2፤ 9፥4
147፥20 ዘዳ4፥7-8 ፡32-34፤ መዝ33፥2፤ 79፥6፤ 103፥1
148፥1 መዝ19፥1፤ 33፥2፤ 69፥34፤ 103፥1 ፤ 150፥1
148፥2 1ነገ22፥19፤ መዝ103፥20
148፥3 መዝ19፥1
148፥4 ዘፍ1፥7፤ ዘዳ10፥14
148፥5 መዝ145፥21 ፤ 147፥15
148፥6 ኤር31፥35-36፤ 33፥25
148፥7 ዘፍ1፥21፤ ዘዳ33፥13፤ መዝ33፥2፤ 74፥13-14
148፥8 ዘፀ9፥18፤ ኢሱ10፥11፤ ኢዮ37፥11-12፤ መዝ103፥20፤ 147፥15-18
148፥9 ኢሳ44፥23፤ 49፥13፤ 55፥12
148፥10 ኢሳ43፥20 ፤ ሆሴ2፥18
148፥11 መዝ102፥15
148፥13 መዝ8፥1፤ 113፥2፤ 138፥4፤ 145፥5
148፥14 ዘፀ15፥2፤ ዘዳ26፥19፤ 1ሳሙ2፥1 ፤ መዝ22፥3፤ 145፥10
149፥1 መዝ1፥5፤

ሀ1 አንዳንዶች ከቍ14 ጭምር *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።
ለ14 ቀንድ የጥንካሬ ትእምርት ሲሆን *ንጉሥን* ያመለክታል።
ሐ1 አንዳንዶች ከቍ9 ጭምር *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።

*147፥19-20፤* እግዚአብሔር ለእስራኤል ያበረከተውን ልዩ ስጦታ የሚገልጽ ነው፤ ይህም ስጦታ የማዳን ሥራውንና የተቀደሰ ፈቃዱን የሚያስታውቅበት ልዩና የሚዋጅ ቃል ነው።

*መዝ148፤* በየትም ያሉ ፍጥረታት እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ የቀረበ ጥሪ ነው። መዝሙሩ በመጀመሪያ የተዘጋጀው ለምንም ይሁን ለምን በዚህ ቦታ መገኘቱ ግን መዝሙረኛው በመጨረሻ ላይ ያቀረበውን የምስጋና ጥሪ የተሟላ ያደርገዋል። መዝሙሩ እያንዳንዳቸው ስድስት ቍጥር ያላቸውን ሁለት እኩል አንጓዎች የያዘ ሲሆን እያንዳንዱም አንዳ ሁለት ቍጥር ያሉት መደምደሚያ አለው። የመጀመሪያው አንጓ (ቍ1-6) በሰማይ ላሉ ፍጥረታት የተደረገውን ጥሪ የያዘ ሲሆን ሁለተኛው አንጓ ደግሞ (ቍ7-12) ከሰማይ በታች ላሉ ፍጥረታት የቀረበውን ጥሪ ይዞአል (103፥20-22 ይመ)። መደምደሚያው ደግሞ (ቍ13-14) ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚቀርብበትን ምክንያት ያወሳል፤ የመዝ146 መግቢያን ይመ።

*148፥1-6፤* በሰማያት ያሉ ፍጥረታት ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ያሳስባል።

148፥3 *ፀሐይና ጨረቃ ... የምታበሩ ከዋክብት፤* የ65፥13 ማብ ይመ።

148፥4 *ከሰማያትም በላይ ያላችሁ ውሆች፤* ከሰማይ ወይም ከጠፈር በላይ ያለ "ጥልቅ" ለማለት ነው ዘፍ1፥7 ይመ ("የውቅያኖስ ጥልቆች" (ቍ7) ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ፤ የ42፥7 ማብ ይመ)።

148፥5 *የእግዚአብሔርን ስም፤* ቍ13 እንዲሁም የ5፥11 ማብ ይመ። እግዚአብሔር ስለ ፈጠራቸውና ህልውናቸውንም ስላጸና እርሱን ማመስገን አለባቸው።

*148፥7-12፤* በምድር ያሉ ፍጥረታት ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ጥሪ ያደርጋል ("ሰማይና ምድር" የፍጥረት ድምር ናቸው፤ ቍ13፤ 89፥11፤ 113፥6፤ 136፥5-6፤ ዘፍ2፥1፡4 ይመ)።

148፥7 *የባሕር ፍጥረትና ... ጥልቅ ውሆች፤* በዘፍጥረት ም1 ላይ ያለውን የፍጥረት ታሪክ የሚያስታውስ ሲሆን (ዘፍ1፥7፡10፡21 ይመ) ጥሪው ከፍጥረታት ይጀምርና ወደ ሰው ያልፋል፤ ግዑዛንም ሆኑ ሕያዋን ፍጥረታት እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ጥሪ ቀርቦላቸዋል።

148፥8 *ትእዛዙንም፤* ቃሉን ለማለት ነው (147፥15 እና ማብ ይመ)።

*148፥13-14፤* ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚቀርብበትን ምክንያት የያዘ መደምደሚያ ነው።

148፥13 *ስሙ ... ክብሩም፤* ክብሩ ለፍጥረታት በሰጠው ህልውና ታይቶአል። *በላይ ነውና፤* የፈጣሪ ክብር ከፍጥረታት ክብር የላቀ ነው።

148፥14 *ቀንድን፤* በእግዚአብሔር የተቀባውን ንጉሥ ያመለክታል (የ2፥2፤ የመዝ18 ርእስ ማብ ይመ)። በዚህ ቦታ ግን "ቀንድ" የሚለው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጥንካሬና ብርታት ሳያመለክት አይቀርም (92፥10፤ ኢሳ2፥1፤ ኤር48፥25፤ ሰቆ2፥17 ይመ)። በዚያም ሆነ በዚህ ቃሉ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን የማዳን ሥራ ያመለክታል፤ እግዚአብሔር ፈጣሪና አዳኝ በመሆኑ ምስጋና ውዳሴ ይገባዋል (የ65፥6-7 ማብ ይመ)። *ምስጋና፤* 22፥3 እና ማብ ይመ።

*መዝ149፤* በሕዝቡ ላይ ስለፈሰሰው በረከት ለእግዚአብሔር የቀረበ ምስጋና ነው። መዝሙሩ ከምርኮ በኋላ ስለመጻፉ (ድኅረ-ምርኮ ስለ መሆኑ) ምንም ጥርጥር የለውም። ለእስራኤል የፈሰሰው በረከት ሁለት መልክ አለው፤ እስራኤል የእግዚአብሔርን ድነት እንድትቀበልና (በተግባርና በቃል ኪዳን) የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማፈራረስ ታጥቀው በተነሡ የዓለም ኀይሎች ላይ የእግዚአብሔርን የፍርድ ሰይፍ እንድትይዝና ፍርዱንም እንድታስፈጽም ተደርጓል፤ ምክንያቱም እስራኤል የሰማዩን ንጉሥ ሰራዊት በዚህ ምድር ወክላ ታገለግላለች (68፥17 እና ማብ፤ እንዲሁም ኢሱ 5፥14፤ 2ሳሙ5፥23-24፤ 2ዜና20፥15-17፡22፤ ዕንባ3፥3-15 ይመ)። ይህም ከመጨረሻው መዝሙር ቀጥሎ ያለው ይህ መዝሙር ለብሉይ ኪዳኗ እስራኤል የጸሎት (እንዲሁም የምስጋና) መጽሐፍ መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ከመግቢያው ቍጥር ቀጥሎ ሁለት መሪ ፍሬ ሐሳቦች እያንዳንዳቸው አራት አራት ቍጥር ባላቸው ሁለት አንጓዎች አድገው እናገኛለን። መዝሙሩ "ቅዱሳን" በሚለው ቃል ተቀንብቦአል (ቍ5 ይመ)። "ክብር" የሚለው ቃል ሁለቱን አንጓዎች በጥሩ ሁኔታ ያስተሳስራል (ቍ5) (8፥5 እና 21፥5 ላይ "ክብር ... ግርማ"፣ 104፥1፡31 ላይ "ክብር ... ግርማ" እና 145፥5፡12 ላይ "ክብር ... ግርማ" የሚሉትን ይመ)።

149፥1 *አዲስ ቅኔ፤* የ33፥3 ማብ ይመ። *በቅዱሳን ጉባኤ፤*

2 እስራኤል በፈጣሪው ደስ ይበለው፤
የጽዮንም ልጆች በንጉሣቸው ሐሤት
ያድርጉ።
3 ስሙን በሽብሸባ ያመስግኑ፤
በከበሮና በመሰንቆ ይዘምሩለት።
4 እግዚአብሔር በሕዝቡ ደስ ይለዋልና፤
የዋሃንንም በማዳኑ ውበት ያጐናጽፋል።
5 ቅዱሳን በዚህ ክብር ይጓደዱ፤
በመኝታቸውም ላይ እልል እያሉ ይዘምሩ።
6 የአምላክ ውዳሴ በአንደበታቸው፣
ባለ ሁለት ልሳን ሰይፍም በእጃቸው
ይሁን፤
7 በዚህ ሕዝቦችን ይበቀላሉ፤
ሰዎችንም ይቀጣሉ፤
8 ነገሥታታቸውን በሰንሰለት፣
መኳንንታቸውንም በእግር ብረት
ያስራሉ፤
9 ይህም በእነርሱ ላይ የተጻፈውን ፍርድ
ለመፈጸም ነው።
ለቅዱሳኑም ሁሉ ይህች ክብር ናት።

ሃሌ ሉያ።

28፥7፤33፥2፤96፥1፤
103፥1፤ራእ5፥9
149፥2 ኢዮ10፥3፤
መዝ10፥16፤47፥6፤
95፥6፤ኢሳ13፥3፤32፥1፤
44፥2፤45፥11፤54፥5፤
ኤር51፥48፤ዘካ9፥9
149፥3 ዘፀ15፥20፤
57፥8
149፥4 መዝ35፥27
፤132፥16፤147፥11
149፥5 ኢዮ35፥10፤
42፥8፤132፥16
149፥6 ነህ4፥17፤መዝ
66፥17፤ዕብ4፥12፤ራእ
1፥16
149፥7 ዘኍ31፥3፤
ዘዳ32፥41፤መዝ81፥15
149፥8 2ሳሙ3፥34
፤2ዜና33፥11፤ኢሳ
14፥1-2
149፥9 ዘዳ7፥1፤
መዝ145፥10፤ሕዝ
28፥26
150፥1 መዝ68፥24-
26፤73፥17፤102፥19፤
112፥1፤148፥1
150፥2 ዘፀ15፥7፤
ዘዳ3፥24
150፥3 ዘኍ10፥2፤
መዝ57፥8

## መዝሙር 150

### የምስጋና መዝሙር

1 ሃሌ ሉያ።[1]

እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት፤
በታላቅ ጠፈሩ አወድሱት።
2 ስለ ብርቱ ሥራው አመስግኑት፤
እጅግ ታላቅ ነውና ወድሱት።
3 በመለከት ድምፅ አመስግኑት፤
በበገናና በመሰንቆ ወድሱት።
4 በከበሮና በሽብሸባ አመስግኑት፤
በባለ አውታር መሣሪያና በእምቢልታ
አወድሱት።
5 ተርገብጋቢ ድምፅ ባለው ጸናጽል
አመስግኑት፤
ድምፀ መልካም በሆነ ጸናጽል ወድሱት።
6 እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን
ያመስግን።

ሃሌ ሉያ።

150፥4 ዘፍ4፥21፤ ዘፀ15፥20፤መዝ45፥8
150፥5 2ሳሙ6፥5 150፥6 መዝ103፥22

[1] አንዳንዶች ከቍ6 ጭምር እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ።

የ9፥1 ማብ ይመ። *በቅዱሳን፤* ቍ5:9፤ የ4፥3 ማብ ይመ።

*149፥2-5፤* እስራኤል ሁሉ ቤዛነቱን ባቀዳጃቸውና በንጉሣቸው በእግዚአብሔር ደስ ይበላቸው።

149፥3 *ስሙን፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

149፥4 *ውበት፤* ታላቅ ሞገስ ያለብሳቸዋል (ኢሳ55፥5፤ 60፥9፤ 61፥3 ይመ)። *የዋሃንንም፤* አንዳች መመኪያ እንደሌላቸው የተረዱ ናቸው (147፥6 ይመ)።

149፥5 *በመኝታቸውም ላይ፤* ቀን በተግባር ያዩት የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ (ቍ4) ሌሊት በሐሴት ተሞልተው እንዲዘምሩ ያደርጋቸዋል (42፥8፤ 63፥6፤ 77፥6 ይመ)።

*149፥6-9፤* እስራኤል ሁሉ ስለታም ሰይፍ የያዙ የእግዚአብሔር ሰራዊት እንዲሆኑ ክብር ስለተሰጣቸው አምላካቸውን ያመስግኑ።

149፥7 *ይበቀላሉ፤* መንግሥቱን ለማጥቃት በተነሡ ጠላቶች ላይ የተሰጠ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ ነው፤ እንዲህ ስለመሰለው የመለኮት ቅን ፍርድ ብሉይ ኪዳን በተደጋጋሚ ይናገራል (58፥10፤ 79፥10፤ 94፥1፤ ዘኍ31፥2፤ ዘዳ32፥35:41:43፤ 2ነገ9፥7፤ ኢሳ34፥8፤ 35፥4፤ 47፥3፤ 59፥17፤ 61፥2፤ 63፥4፤ ኤር46፥10፤ 50፥15:28፤ 51፥6:11:36፤ ሕዝ25፥14:17፤ ሚክ 5፥15፤ ናሆ1፥2 ይመ)። በአዲስ ኪዳን ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ በእግዚአብሔር መንግ ሥት ላይ የተነሣውን ጠላት "በመንፈስ ሰይፍ" እንዲዋጋ ነው (2ቆሮ 6፥7፤ 10፥4፤ ኤፌ 6፥12:17፤ ዕብ 4፥12 ይመ)። እግዚአብሔር በዓለም ላይ ሲፈርድ ከእርሱ ጋር በመሆን የሚፈርዱት ግን በመጨረሻው የፍርድ ቀን ነው (1ቆሮ 6:2፥3 ይመ)።

149፥9 *የተጻፈውን … ፍርድ፤* የእግዚአብሔር ፍርድ ነው (139፥16 እና ማብ ይመ)።

*መዝ150፤* የመጨረሻው ታላቅ ውዳሴ ሲሆን ምናልባትም የመጽሐፉ መደምደሚያ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ መዝሙር ነው። የአራቱን መጻሕፍት መደምደሚያ ይመ (41፥13፤ 72፥18-19፤ 89፥52፤ 106፥48) ይህ የመጨረሻ የምስጋና ጥሪ እግዚአብሔር ካለበት ቦታ በመጀመር እግዚአብሔር ወዳደረገው ድንቅ ሥራ፣ ከዚያም እግዚአብሔርን ለማመስገን ከተዘጋጁበት መሣሪያዎች ወደ ሕያዋን ፍጥረታት ብርቱ በሆነ እንቅስቃሴ ይሸጋገራል፤ እያንዳንዱም ደረጃ በሃሌሉያ ተቀንብቦአል (የመዝ146 መግቢያ ይመ)።

*150፥1፤* እግዚአብሔር የሚወደስበት ስፍራ ነው። *በመቅደሱ፤* በኢየሩሳሌም ከተማ ማለት ነው። *በኀያል ሰማያቱ፤* ቃል በቃል ሲተረጉም "የኀይሉ ስፋት" ማለት ነው (19፥1፤ ዘፍ1፥6 ይመ)፤ ይህም የኀይሉን መጠን ወይም የኀይሉን መኖሪያ ያመለክታል። አብዛኛውን ጊዜ ሰማያዊውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ የሚያመለክት ሲሆን (11፥4 ይመ) በዐይን የምናየውንና እንደ ቤት ጣራ የተንጣለለውን ሰማይ እንደ ቤተ መቅደስ በመቍጠር እርሱን ሊያመለክት ይችላል።

*150፥2፤* እግዚአብሔር የሚወደስበትን (የሚመሰገንበትን) ምክንያት ይናገራል። *ስለ ብርቱ ሥራው፤* በሥነ-ፍጥረትና በማዳን ሥራው ተገልጾአል።

*150፥3-5፤* እግዚአብሔር እንዴት መወደስ (መመስገን) እንዳለበት ይናገራል፤ በልዩ ልዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች (በዋሽንት፣ በበገና፣ በመለከት)።

*150፥6፤* እግዚአብሔርን ማወደስ (ማመስገን) የሚገባው ማን እንደሆነ ይናገራል፤ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና አእምሮንም የሚያልፈውን የማዳን ሥራውን ፍጥረት ሁሉ ሊያመሰግን ይገባል።